# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

# የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች

በ

ብሌን መንግስቱ

ነሐሴ፤ 2016 ዓ.ም

አዲስአበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

# የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች

በ

ብሌን መንግስቱ

በአማርኛ ቋንቋሥነ-ፅሁፍ እና  ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የኤም.ኤ. ዲግሪማሟያየቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

አማካሪ፡- የወንድወሰን አውላቸው(ዶ/ር)

ነሐሴ፤ 2016 ዓ.ም

አዲስአበባ

**ማረጋገጫ**

*ይህጥናት (ቴሲስ)*
*የእኔመሆኑንናየተገለገልኳቸውንምንጮችምበአግባቡመጥቀሴንበፊርማዬአረጋግጣለሁ፡፡*

*ስም፡- ----------------------*

*ፊርማ፡----------------------*

*ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም*

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች

በ

ብሌን መንግስቱ

በአማረኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር መርሃ ግብር ትምህርት ክፍል

የኤም.ኤዲግሪማሟያየቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

## የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም፡- ፊርማ፡- ...........

የውስጥ ፈታኝ ስም፡- ፊርማ፡- ...........

የውጭ ፈታኝ ስም፡- ፊርማ፡- ..........

# ምስጋና

ለረዳኸኝ እና እድሜን ጨምረህ ለዚህ ላበቃኸኝ አምላኬ አመሰግናለሁ፡፡

የጥናት ስራው እስኪ ጠናቀቅ ድረስ ከጎኔ በመሆን በቅንንት ለረዳኸኝ መምህሬ እና አማካሪዬ ዶ/ር የወንድወሰን አውላቸው ላደረክልኝ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በዚህ ቅንነትህ እድሜ እየቸረ ያኑርህ፡፡

ይህን ጥናት በሚካሂድበት ጊዜ የገንዘብ ወጭዬን ለመቀነስ በጽሁፍ፣ በሃሳብ የደገፍሽኝ እስከዳር እቢያለው አመሰግናለሁ፡፡ ክብረት ይስጥልኝ፡፡ የልጆችሽ እናት ያድርግሽ

ለውድ ባለቤቴ ላሳየኸኝ እና ጥናቱ እዲጠናቀቅ ያደረከው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበርና አመሰግናለሁኝ፡፡

ልጄ ምንአልባት ለአንተ አርአያ ለመሆን የተውኩትን ስራ እንድሰራ ምክንያት ሆነኸኛልና ተባረክልኝ፡፡

# ማውጫ


ምስጋና ........ i

ማውጫ ........ ii

አጠቃሎ ........ v

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 4

1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 4

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 4

1.4. የምርምር ጥያቄዎች ........ 4

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች ........ 5

1.8 የጥናቱ ዘዴዎች ........ 5

1.8.1 የጥናቱንድፍ ........ 6

1.8.2 የጥናቱአቀራረብ ........ 6

1.8.3 የመረጃምንጭ ........ 6

1.8.4 የመረጃመሰብሰቢያዘዴ ........ 6

1.8.5 የናሙናአመራረጥ ........ 7

1.8.6 የመተንተኛስልት ........ 7

1.9 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 7

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

2 ክለሳ ድርሳናት .......... 8
2.1 የጽንሰ ሀሳብ .......... 8
2.1.1 የህይወት ታሪክ ምንነት ፦ .......... 8
2.1.2 ግለ ታሪክ (Auto biography)ምንድን ነው? .......... 9
2.1.3 የህይወት ታሪክ ርዕሰ ጉዳዮች .......... 10
2.1.4 በስነ-ጽሑፍ ውስጥ የህይወት ታሪክ ዓይነቶች .......... 11
2.2 በስነ-ጽሑፍ ውስጥ የግለ ታሪክ የአጻፃፍ ዓይነቶችና ምድቦች .......... 12
2.3 ታሪከ ግል ሲፃፍ ሊተኩርባቸው የሚገባ ነጥቦች .......... 14
2.4 ሕይወት ታሪክ ጽሑፎች መርሆዎች .......... 15
2.5 የእንስትነት (ሴትነት) (Feminism Theory) ንድፈ ሀሳብ .......... 16
2.5.1 ባህላዊ እንስትነት /Cultural Feminism/ .......... 17
2.5.2 ኤኮፌምኒዝም /Eco-feminism/ .......... 17
2.5.3 ግላዊነት ወይም ሊብራቴሪያን እንስትነት /Individualist or Libritarian/ .... 17
2.5.4 ቁሳዊ እንስትነት /Material Feminism/ .......... 18
2.5.5 ለዘብተኛ እንስትነት /Moderate Feminism/ .......... 18
2.5.6 ብሔራዊ የሴቶች ተቋማት /National Women's Organizations/ .......... 18
2.6 የሴትነትግል(የሴትነት ግዱ ትግል) ፅንሰ-ሀሳብቁልፍጽንሰ-ሐሳቦች .......... 19
2.6.1 ፓትርያርክ (አባዊ ሥርአት) .......... 19
2.6.2 ኢንተርሴክሽንሊቲ .......... 20
2.6.3 የሥርዓተ-ፆታአፈፃፀም .......... 21
2.6.4 የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታ .......... 22
2.6.5 የወንድእይታ(The malegaze)ጽንሰ-ሐሳብ .......... 24
2.7 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት .......... 24
ምዕራፍ ሶስት .......... 26

3 የመረጃ ትንተና ....................................................................................................26
3.1. ውልደት፣ እድገትና ትምህርት ..........................................................................26
3.2. የግለ ታሪኮቹ የትዳር ሕይወት ሁኔታ...............................................................33
3.3. ማህበራዊ ተሳትፎ እስከ ሙያዊ አበርክቶ..........................................................38
3.4. ሴትነት ያጋጠማቸው ተግዳሮት.......................................................................43
3.5. የወላጅ ፍላጎት በልጆች ላይ ..........................................................................51
3.6. ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ቅርርብ ..................................................................53
3.7 እናትነት በግለ ታሪኮች ውስጥ.........................................................................58
3.8 ግለታ ሪኮች ከእንስታዊ ወይም ሴትነት ግዴ ትግል አንፃር ፍተሻ.....................63
ምዕራፍ አራት.............................................................................................................75
4 ማጠቃለያ እና ይሁንታ ........................................................................................75
4.1 ማጠቃለያ.............................................................................................................75
4.2 ይሁንታ ................................................................................................................76
ዋቢ ጹሑፎች..............................................................................................................77

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተመረጡ የሴቶች ተሞክሮ በአማርኛ ግለ ታሪክ ፍተሻ ነው፡፡ ጥናቱ ንድፍ አይነታዊ ገላጭ የጥናት ንድፍ የተከተለ ነው፡፡ የመረጃ ምንጮች ሁለተኛ ደረጃ (ዳህራይ) የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ ይህም ማለት በግለሰቦች በግላቸው የተፃፉ የአማረኛ ግለ ታሪኮች ትሙት ግድ የለም በዶ/ር ትግስት ግርማ ፣የፀሐይ ጉዞ ወ/ሮ ፀሐይ ይትባረክ የውብ የውብ ድንበር እውተኛ ታሪክ በወ/ሮ ውብ ድንበር ነጋሽ የተፃፈ የአማረኛ ግለ ታሪክ መጽሀፍት መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ የናሙና አመራረጥ አላማ ተኮር ነው፡፡ የተመረጡ የአማረኛ ግለ ታሪክ መፅሀፍት በዓላማ በራሱ አነሳሽነት በቀላሉ በገበያ ላይ የሚገኙ የቅርብ የታተሙ መጽሀፍት በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ የመረጃው ትንተና ዘዴ ይዘት ትንተና ላይ አተኩሯል፡፡ ማለትም በመጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች አንፃር ተተንትኗል፡፡ በዚህ ባሻገር ግለ ታሪኮች በእንስታዊ (ሴትነት ግዴ ትግል) አንፃር በአምስት ቁልፍ ርእሰ ጉዳዮች ማለትም ፓትሪያሊክ(አባዊ) ሥርአት ኢንተርሴክሽናሊቲ ፣የሥርአት ፆታ አፈጻፀም፣ ማህበራዊ ግንባታና የወንድ ዕይታ በሚሉ ርእሰ ጉዳዮች አንፃር ፍተሸ ተደርጋል፡፡ በመሆኑም ግለ ታሪክ አፃፃፍ ላይ የሚመለከተው ክፍል ትኩረት ቢያደርግ የሕይወት ተሞክሮ ማህራዊ ግንኙነት እና የፆታ እኩልነት እዲሁም ጥበብና ትምህርትን በማስፋት ከጾታ ጋር ተያያዞ የሚፈጠሩ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ መፍትሔ ለማበጀት ይረዳል፡፡*

*ቁልፍ ቃላት ፡- የሴቶች ተሞክሮ፣ ግለ ታሪክ አማርኛ እንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሥነጽሑፍየገሃዱንወይምየምናባዊውንአለምሁነቶችንበጽሑፍወይምሥነቃልበጥበብመግለጽማለትነው፡፡ሥነጽሑፍልቦለድ፣ሥነግጥም፣የተውኔትጽሁፍእናኢ-ልቦለድበሚልበአራትዘርፎችይከፈላል፡፡ምናባዊትርክት (Imaginative Literature) ልቦለድ፣ሥነግጥምእናየተውኔትድርሰትያካትታል፡፡በኢ-ልቦለድ (Non-fiction) ዘርፍየሚካተቱየሥነጽሁፍውጤቶችየዜናዘገባ (News Reports)፣የዳሰሳጽሁፍ (feature article)፣የግለታሪክ (biography)፣የታሪክዘገባ (historical accounts) ሊሆኑ ይችላሉ (ሀብታሙ ግርማ፣ 2008)፡፡

በሥነ ጽሁፍ የሚካተተው ግለ ታሪክ በሀገራችን በጽሁፍ ሰፍሮ ለአንባቢ ማቅረብ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ለዚህም ማሳያነት በየመጽሀፍ ቤቱ የሚሸጡ መጽሀፍት እና የህትመት ውጤቶችን መመልከት አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ግለታሪክ በሁለት መንገድ የሚቀርብ ሲሆን የራስን ታሪክ በራስ አንደበትና ብዕር ከትቦ ሲቀርብ አውቶባዮግራፊ (Autobiogrephy) ሲሆን የአተራረክ መደቡ አንደኛ መደብ የሚከተል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግለ ታሪክ ወይም (biography) የአንድን ግለሰብ ታሪክ በሌላ ሰው በሶስተኛ መደብ የሚጻፍ ነው፡፡ (ዘሪሁን ፣2013)

ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) የፀሐፊውን ማንነት የሚወክል የጽሁፍ ዘር ነው፡፡(encyclopaedia Americana,1995)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግለ ታሪክ በባለ ታሪኩ የሚፃፍ የኢ ልቦለድ አይነት ነው(ዘሪሁን፣2013)፡፡ በማህበራዊ እና በሥነ ጽሁፍ ሙያ ዘርፍ ከሚጻፉ መጣጣፎች መካከል ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) በጣም ተወዳጅ የሥነ ጽሁፍ አይነት ነው፡፡ ግለ ታሪክ ለስነ-ጽሁፍ ሂስ አድራጊዎች፣ ለፍልስፍና ሰዎች፣ ለተመራማሪዎች እና ለስነ -ልቦና አዋቂዎች ህይወት እንዴት እንደተኖረ ማሳያ ብቻ ሳይሆን ራስን መሆን ምን ማለት እንደሆነ የሚያስረዱበት ነው፡፡ (ዘሪሁን፣ 2013)፡፡ በመሆኑም ግለ ታሪክ ስያሜው እና አጻጻፍ እንዴት ተጀመረ? ግለ ታሪክ(Autobiogrephy) ዛሬ የደረሰበትን ቅርጽ ለመያዝ

“autograhy”“autothanatography”“autobigrafiction”“autofiction” በሚሉ እና የተለያዩ ትርጉም ባላቸው ዲቃላ ቃላት እየታጀበ የመጣ ነው፡፡

ግለ ታሪክ ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) ቃላት ጥንተ አመጣጥ ከሦስት የግሪክ ቃላት ቅንጅት የተገኘ ሲሆንAuto(The individual himself ) ግለሰቡን ሕይወት ተሞክሮ(ገጽታ) የሚያሳይ Bios (individual human life) ደግሞ ግለሰቡንGraph (description)መግለጽ ወይም ማተት ነው፡፡ ግለታሪክ (Autobiogrephy) በዘመኑ በጽሁፍ ሥራ ሲውል በአብዛኛው በታዋቂ ሰዎች ሕይወትና ገድል ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ጽሑፉም የባለታሪኩን ባህሪና ሥራውን የሚቃኝ ነበር፡፡ ከሜዲትራኒያኑ ዓለም ሥልጣኔ ጋር ብቅ ያለው ሥነ ጽሑፍ፣ ታሪካዊ እሴቶችና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ግለ ታሪክ ተጀመረ፡፡ ለምሳሌ የአይሁድ ባህልና ሥነ ጽሑፍም ይህንኑ የሜዲትራኒያኑ የሥነ ጽሁፍ ባህል ተጋሪ በመሆን ከሌሎች የሥነ ጽሁፍ ተዋሽ ሆኖ ሊቀረጽ ችሏል፡፡ ለምሳሌ ጆሴፈስ የተባለው አይሁዳዊ የታሪክ ሊቅ፣ ለግሪክ አንባቢያን ስለጥንቱ እሥራኤል በዘመናዊ መልኩ ለመፃፍ ሞክሯል፡፡ ዘመኑን የሚመስል ዘመናዊ ቅርጽ ሰጥቶል፡፡ በዚህም ሙከራው የንጉሥ ሳኦልንና የንጉሥ ሰለሞንን ታሪክ፣ ለአንባቢያን አቅርቧል፡፡ ሌላኛው አይሁዳዊ ፈላስፋ ፊሎ፤ የሙሴን የሕይወት ታሪክ እንደ ንጉሥ፣ ሕግ ሰጪ፤ ሊቀካህናትና ነቢይ አድርጎ ለመፃፍ ሞክሯል (George Misich,1950)፡፡

ወደ ዘመናዊው የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ስንመጣ፣እንደ(catherine) እንደሚሉት፤ የዚህ ዘውግ ዘመናዊ ገጽታ የተወለደው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ሲሆን ቀድሞ የነበረው የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ማለትም ገድል ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኖ መቀጠል አልቻለም፡፡ የጦርነቱ ተዋናዮች፣ ከጦር ሜዳው መልስ ፍርሀትና ስቃዩን ሲናገሩ ጉብዝና ብቻ ሳይሆን ፍርሀትና ድንጋጤ የመኖሩ ግልጥነት ተሰማ፡፡ ይህ አንዱ ለውጥ ሆነ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባለታሪኩን ታሪክና ገድል ብቻ ሳይሆን የበቀለበትን ቤተሰብና አካባቢ፣ ልጅነቱንም ጭምር በሚገባ በማካተት የተሻለ ቀለም ይዞ ብቅ አለ፡፡ ይህንን አፃፃፍ ዛሬም የሰለጠኑት ዓለማት ፀሐፍት ይጠቀሙበታል፡፡ በእኛም ሀገር በሚፃፉት መጽሐፎች ላይ ማስተዋል ይቻላል፡፡

ግለ ታሪክ (Autobiogrephy)ለምን ይጻፋል ስንል እንደ ዘሪሁን አገላለጽ ግል ታሪክ የሚፃፈው ለሕይወት ትርጓሜ ለመስጠት ለቤተሰብ፣ ለልጆች አርአያ ለመሆን፣ ወይም ደግሞ በበጎ ተግባራት ለአገር ለወገን ጠቃሚ ስራዎችን በመስራት የነበረን ታዋቂነት በማሳየት አርአያነት ለማስተላለፍ፣ እንዲሁም የዘመንን ታሪክ ለመተረክ ሊሆን ይችላል፡፡(ዘሪሁን፣2013)

ከዚህ አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳብ እና አላማውን በመነሳት ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) የራስን ታሪክ በራስ መፃፍ መግለጽ ጥሩ ወይም ደካማ ጎኖች ሊኖሩት ይችላል፡፡ የታሪክ ሁነቶቹን ማድበስበስ፣ የራስን አሳፋሪ ገበና በጽድቅ መለበጥ እውነት ናቸው ተብለው ሲታመንባቸው የቆዩ ጉዳዮችን በሐሰት መሸፋፈን በተደጋጋሚ የሚታዩ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ውስጣዊ ማንነት በታማኝነት መግለጽ ለሌሎች ምሳሌ ከመሆን አልፎ የታሪክ ሂደትን እንዳያዛባ የራሱን እንዳይዛባ ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ ያንን እውነት በጽሁፍ መድፈር ለብዙዎች ይከብዳል፡፡ የውስጥ ጨለማን አደባባይ ማስጣት ያስፈራል፡፡ ከላይ ከጠቀስነው ሀሳብ በመነሳት ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) ማንበብ የተጻፈውን ፊደል ብቻ ሳይሆን ሰውየውን የማንበብ ያህል ነው ልቆ የሚሄደው፡፡ የመለከካከት አቅጣጫን፣ቤተሰባዊ ሕይወትን የፖለቲካ አዝማሚያ ወገናዊነትን ሚዛናዊነትን ግልጽነትን ሌሎችንም መሰል የስዕብና ነፀብራቆች ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) ውስጥ ፈልፍሎ ማግኘት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የጽሑፉን ስልቱና በውስጡ የሚነሱ ተንዳኝ መረጃዎች ለጥበብና ለታሪክ የሚሰጡት አበርክቶ ሰፊ ጠቀሜታን አስገኝቷል፡፡በመሆኑም በሀገራችን የሚፃፍ ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) የባለ ታሪኮቹን ውጣ ውረዶች ከማሳየት አልፈው ዘመንን ለመተረክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ከዚህ መነሻነት በዚህ ጥናት እስካሁን እምብዛም የጥናት ጽሁፎች ያላያቸውን ነገር ግን ቢጠኑ ለሥነ- ጽሁፍ እድገት የራሳቸው ሚና ይኖራዋል ብዩ ያሰብኳቸው በአማረኛ ቋንቋ ከቀረቡት ታሪከ ግሎች በሴቶችና በወንዶች የሚጻፉ ግለ ታሪክ (Autobiogrephy) የትኩረት አቅጣጫቸው ምንድን ነው? ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ እንዴት ይገልፃሉ? የሚሉትን ለመመለስ በዚህ የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች በሚለው የጥናቴ ርዕስ በንጽጽር በመተንተን ሥነ ጽሁፋዊ ፋይዳቸውንለማቅረብ ጥረት አደርጋለሁ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የስነ

ጽሑፍፋይዳበየዘመኑየህዝብንአኗኗር፣አስተሳሰብ፣ባህልናወግ፣በአጠቃላይየማህበረፖለቲካእንዲሁ ምኢኮኖሚያዊሁነቶችን ለትውልድየሚያስተላልፍየታሪክማህደርጭምር ነው፡፡በአጠቃላይሥነጽሑፍህዝብንከማሳወቅናከማንቃትየማይተካሚናአለው፡፡ከዚህም መካከል ግለ ታሪክ አንዱ በስነ ፅሁፍ ዘርፍ ውስጥ ተጠቃሽ ነው ፡፡ ከዚህአንጻርህዝብየመጻፍናየማንበብክህሎትብቻሳይሆንልምድምጭምርእንዲያዳብርምቹሁኔታዎች መፈጠር ተገቢ ነው፡፡ህዝብእንዲያውቅናእንዲነቃማድረግ በርካታ ጠቀሜታ አለው፡፡

በተለያዩመስኮች የግለሰብ ሕይወት ታሪክ (ተሞክሮ) ሊወሳ፣ገድላቸውሊነገር እና ሲፃፍ ለአገርናህዝብባለውለታዎችመካከል እነማን ነበሩ የሚለውን የሕይወት ተሞክሮ እና ሕዝብን አስተማሪ የሆኑ የኢትዮጵያዊያንጸሀፍትዋነኞቹ ማወቅ ያስችላል፡፡ በመሆኑምበርዕሰ ጉዳዩ ላይ እንዳጠና ያነሳሳኝ ምክንያት ከ2005ዓ/ም ጀምሮ የግለታሪክ(ባዮግራፊ) መጽሐፍት እየታተሙ ነው፤ ሌላውአሁን እየታተሙ የሚወጡ ግለታሪኮችን ስንመለከት አንዳዶች መልከዐ ባለታሪኩ ሥም ተጠቅሶ ይፃፋል፤ ሌላው የባለታሪኩ ሥም ተጠቅሶና ሕይወቱ እና ሥራዎቹ ይቀርባል፤ የባለታሪኮቹ ስም ከድርጊት አመላካች ጋር እንዲሁም ባለታሪኮቹ ባጋጠማቸው የሕይወት ትግል ውጣውረድ ይገልጥልኛል በሚሉ ቃላት ወይም ሀረጋት፣ የመጽሀፍ ስያሜ በመስጠት ሲታተሙ እናያለን፡፡ ይህ በመሆኑም እኔም እነዚህ ግለ ታሪክ መጽሀፍት ይዘታቸውና አቀራረባቸው ምን ይመስላል? የሚለው ነገር ለማወቅ ፍላጎት አደረብኝ፡፡ ከዚህበተጨማሪበአዲስአበባዩኒቨርስቲየተጠኑጥናቶችንስመለከትበዚህመስክላይ የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች ከእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ አንፃርየተሠራጥናትናምርምር በእኔ ፍተሻ አነስተኛ በመሆኑ ጥናቱ ለማጥናት አነሳሽ ምክንያት ሆነኝ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

በዚህ የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች ንጽጽር ላይ በሚያተኩረው ርዕስ ስር የጥናቱ ዓላማ እና ንዑሳን ዓላማዎች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮችይዘትን በንጽጽር መተንተን ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በግለ ታሪክ ጽሁፉ ውስጥ የተካተቱትን ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፡፡
- ሴቶችያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች እና እድሎች በቤተሰብ፣ በትምህርት፣ በስራ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ውስጥ በማወዳደር መተንተን፡፡
- የህይወት ታሪኮች በእንስታዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ፍተሻ ማድረግ

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡-

- በግለ ታሪክ ጽሁፉ ውስጥ የተካተቱትን ርዕሰ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

- በቤተሰብ፣ በትምህርት፣ በስራ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ውስጥ ሴቶች ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች እና እድሎች ምንድን ናቸው?
- የህይወት ታሪኮችእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህጥናትጠቀሜታበግለ ታሪክ ላይጥናት ትላንት የነበሩበትን ተግባራቸው ማህበራዊ ግንኙነታው ለዛሬ መሰረት የጣሉ ፈር ቀዳጅ ግለሰቦች የሕይወት ታሪክ መፈተሽ እና የግለ ታሪክ ወይም ኢ- ልቦለድ አፃፃፍ ላይ እንደመሰረት የሚያገለግል እና የባለ ግለ ታሪኩ የሥራ ሕይወት ሊያስተምሩ የሚችሉ በርካታ ፍሬ ነገሮች የመለየት እውቀትና ክህሎት እንዲሁም የደራሲያኑን ሥራዎች ይዘትና ጥልቀት እንዲሁም የሕይወት ጉዞ በስፋት ለማጥናት ወይም ለመዳሰስ ለሚፈልጉ ሌሎች አጥኚዎች ምን አልባት እንደ መነሻ ይሆናል፡፤

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በተመረጡ የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች ይዘትን በንጽጽር መተንተን ነው፡፡ የመረጥኩት ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም የታተሙ ግለ ታሪክ (autobiography) ስንመለከት "የፀሐይ ጉዞ" በፀሐይ ይትባረክ፣"የውብ ድንበር እውተኛ ታሪክ" በየውብ ድንበር እና "ትሙት ግድ የለም" በዶ/ር ትስግስት ግርማ በራሳቸው ፀሀፊያን ለንባብ ያቀረቡልንን ግለ ታሪክ ፍተሻ የጥናቱ ወሰን ነው፡፡

## 1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች

ይህ ጥናት በተመረጡ የወንዶችና የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮችይዘትበንጽጽርየተካሄደ ቢሆንም በጥናቴ ወቅት አንዳንድ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሴቶችግለ ታሪክ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች (autobiography) በብዛት በመጽሀፍ ጥራዝ መልክ ታትሞ አለመገኘት፡፡ ችግሮችን ለመፍታት አጥኚዋ የተለያዩ የመጽሀፍት መደብር መጽሀፍት ሻጮች ተደራሲያን እና ሌሎች ግለሰቦች መረጃን በመጠየቅ ከ2010 እስከ 2012 ዓመተ ምህረት ድረስ የታተሙትን የሴቶች ግለ ታሪክ መጽሀፍት ማግኘትና ከገበያ አፈላልጎ በጥናቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 1.8 የጥናቱ ዘዴዎች

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ስራ የሚውሉ መረጃዎች በምን መልኩ እንደተሰበሰቡ፣ናሙናዎች እንዴት እንደተመረጡና መረጃዎች በምን መልኩ እንዴት ትንታኔ እንደተሰጠ በአጠቃላይ የምርምር

ጥያቄዎችን አስተማማኝና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ለመመለስ የሚያስችሉጉዳዮችና የጥናቱ አካሄዱ ምን እንደሚመስል የሚታይበት ይሆናል፡፡

### 1.8.1 የጥናቱንድፍ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተመረጡበሴት ተሞክሮ በሴት ግለ ታሪክ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን እርሰ ጉዳይ ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተው ገላጭ የምርምር ንድፍ ነው፡፡ ለጥናቱም የሴትነት(ፌሚኒዝም) ንድፈ ሀሳብ በግለ ታሪክ ውስጥየተካተቱትን ርእሰ ጉዳዮች ለመፈተሽ ሀሳቦች በማጠንጠኛነት ጥቅም ላይ ይውሏል፡፡

### 1.8.2 የጥናቱአቀራረብ

በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋለው አይነታዊ የጥናት አቀራረብ ነው፡፡ ይህም ማለት የሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች ላይ በጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ርእሰ ጉዳዮች ስር የተመረጡትን ግለታሪኮች አውዳዊ ንባብ በማድረግ በአይነታዊ (Qualitative) ማለትም የጥናቱ ርእሰ ጉዳዮች በአረፍተ ነገር አማካኝነት የሚተነተንበት የጥናት አቀራረብ ተከተሏል፡፡

### 1.8.3 የመረጃምንጭ

ጥናቱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በመሆኑም ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ጥናቱ የተሰራባቸው የግለ ታሪክ መጽሀፍት ሲሆኑ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ደግሞ ለጥናቱ የሚጠቅሙ የተለያዩ መጻህፍት፣ መጽሄቶችናጋዜጦች ፣መጽሀፍት፣እንዲሁም ሌሎች የህትመት ውጤቶችን እንደ ማጣቀሻ ተወስዷል፡፡

### 1.8.4 የመረጃመሰብሰቢያዘዴ

የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የመዛግብት ፍተሻ ነው፡፡ የመዛግብት ፍተሻ በፅሁፍ ያሉ መረጃዎችን በመርመርና በመፈተሽ ተመራጭ ዘዴ መሆኑን (ያለው፣ 2009) ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡትበተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍት ፍተሻ ሲሆን መረጃዎቹ የሚገኙት የሴቶች ተሞክሮ ግለታሪኮች በመሆኑ በነዚህ መፃህፍት ላይ ጥልቅ ንባብ በማድረግ ለጥናቱ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 1.8.5 የናሙናአመራረጥ

የዚህጥናት ዓላማየሴቶች ተሞክሮ ግለታሪኮች ንጽጽራዊ ትንተና እና ፍተሻ ማካሄድ ነው፡፡ የሶስት ግለሰብ ግለታሪክ የመረጥኂቸው በዓላማ ተኮር የናሙና መምረጫ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ማለት ጥናቱዓላማ ተኮር ናሙና (purposeful, purposive, judgment or judgmental sampling) ዘዴን ተከትሏል ፡፡ በዚህ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው ማንን እና ምን መውሰድ እንዳለበት የሚወስነው ራሱ ነው፡፡ እነዚህ በጥናቴ ውስጥ ቢካተቱ የዳበረ፣ የጠለቀና ሰፊ መረጃ ይሰጡኛል ከሚል ግላዊ ግምገማ በመነሳት ይመርጣቸዋል ፡፡ (ያለው፣2009)፡፡

ይኸውም አጥኝው መረጃየ ሚያገኝበትን ሁኔታ ካረጋገጠ ዓላማውን ዳር ሊያደርሱ የሚችሉትን ለማሳያ ያህል በዓላማ ተኮር ሊመርጥ ይችላል፡፡ ይህን ዘዴ መጠቀም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሁነኛ ዘዴ እንደሆነ ይታመናል፡፡

### 1.8.6 የመተንተኛስልት

ይህየሴቶች ተሞክሮ በተመረጡ የአማርኛ ግለታሪኮች በሚል ርዕስ የተጠናው ጥናት በዓይነታዊ (Qualitative) የጥናትዘዴ የተካሄደ ነው፡፡ አይነታዊ(Qualitative) የመረጃ መተንተና ስልት ስር የተለያዩ መተንተኛ ስልቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት ውስጥ በተመረጡ የአማረኛ ግለታሪኮች ግምት ውስጥ በማስገባት ወይም እርሰ ጉዳይ በማድረግ በይዘት ትንተና ስልት በመጠቀም የመረጃው ትንተና የጥናቱ ክፍል ተካቷል፡፡

## 1.9 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን አደረጃጀቱም እንደሚከተለው ነው፡፡ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ሲሆን በዋነኝነት የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱን ጠቀሜታ፣ የጥናቱን ወሰን እና ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን አካቷል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የጽንሰ ሀሳብ፣ የንድፈ ሀሳብ ቅኝቶች እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ያካተተነው፡፡ምዕራፍሦስት የመረጃ ትንተና የያዘ ምዕራፍ ነው፡፡ ምዕራፍ አራት ማጠቃለያና ይሁንታ ወይም ምክረ ሀሳቦች የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2 ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍየጽንሰ ሀሳብ፣ የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተዳስሰውበታል። ስለህይወት ታሪክ ምንነት፣ ትርጉም ከተለያዩ አካላት የተሰጡ ብያኔዎች፣ ስለግለ ታሪክ በዝርዝር ቀርበዋል። በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ዝምድና ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ዳሰሳ ተደርጓል።

## 2.1 የጽንሰ ሀሳብ

### 2.1.1 የህይወት ታሪክ ምንነት ፦

የህይወትታሪክ፣እንዲሁም
“Bio”ተብሎየሚጠራው፣ስለሰውህይወትተጨባጭመረጃየሚሰጥልብወለድያልሆነስራነው።
የህይወት ታሪክ በግለሰቡ በራሱና በሌላ ሰው ሰለአንድ ሰው ሲፃፍ ያለውዋነኛውልዩነትየህይወትታሪክጸሐፊርዕሰጉዳይአለመሆኑነው።የህይወትታሪክዛሬምየሚኖርሰ ውሊሆንይችላልወይምከአመታትበፊትስለኖረሰውጉዳይሊሆንይችላል።
የህይወትታሪክየርዕሰጉዳዩንህይወትየቀረጹቁልፍክስተቶችዝርዝሮችእናስለትውልድቦታቸው፣ትምህ ርታቸው፣ስራቸውእናግንኙነቶቻቸውመረጃንያካትታሉ።የህይወትታሪክተመራማሪዎችቃለመጠይቆ ችን፣ደብዳቤዎችን፣ማስታወሻደብተሮችን፣ፎቶግራፎችን፣ድርሰቶችን፣የማጣቀሻመጽሃፎችንእናጋዜ ጦችንጨምሮበርካታየምርምርምንጮችንይጠቀማሉ።የህይወትታሪክአብዛኛውንጊዜበጽሑፍቢሆንም ፣እንደሙዚቃቅንብርወይምፊልምባሉ ቅርጾችሊዘጋጅይችላል።
የህይወት ታሪክ ዒላማ የሆነ ሰው በህይወት ከሌለ፣ የህይወት ታሪኩን ለመጻፍ ብዙ ምርምር ይጠይቃል። ቃለ-መጠይቆች ከታሪክ ባለሙያዎች፣ ግለሰቡን ከሚያውቁ ሰዎች (ለምሳሌ፣ ጓደኞች እና ቤተሰብ) ወይም ሌሎች በቀደሙት ዓመታት ስለ ሰውዬው ከጻፉ ሰዎች ሌሎች የቆዩ ሀሳቦችን ለማንበብ መረጃን ለመሰብሰብ ሊያስፈልግ ይችላል። ሰውዬው በህይወት ባለበት የህይወት ታሪክ ውስጥ ጸሃፊው ስለ ህይወቱ ግንዛቤ ለማግኘት ከታለመው ሰው ጋር ብዙ ቃለመጠይቆችን ማድረግ ይችላል።

የሕይወት ታሪክ አላማ አንባቢያንን የግለሰቡን የሕይወት ታሪክ፣ የልጅነት ግዜአቸውን ወደ ጉልምስና እና የጉርምስና አመታትን፣ የአዋቂነት ሕይወታቸውን በቀሪዎቹ አመታታ ውስጥ ማካተት ነውለለ የሕይወት ታሪክ ግለሰቡ ሕይወቱን ትምህርቶችን እንዴት እንደተማረ እና ግለሰቡ ዓለምን እንዴት እደሚመለከት እና ታሪክ ይናገር፡፡ አንባቢው ስለ ሰውየው ስዕብና ፣ባህርያትእና በዓለም ውስጥ ስላለው ግንኙነት ግልጽ የሆነ ምስል መስጠት አለበት፡፡ የሕይወት ታሪክ በአንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ስብስብ ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ ይህ ቡድን የቡድኑን አካል የሆነው የሆነ ዋና ሰው ሊኖረው ይችላል፡፡

### 2.1.2 ግለ ታሪክ (Auto biography)ጽንሰ ሀሳብና ትርጓሜ

ግለ ታሪክ በአንድ ሰው የተፃፈ የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ ነው፡፡ ደራሲው የታሪኩ ዋና ገፀ ባህሪ ምስል ሆኖ ግለታሪኩ የተፃፈው በመጀመሪያ ግለሰብ ነው፡፡ አብዛኛው ግዜ የሕይወት ታሪክ የሚፃፈው የመጽሀፉ ርእሰ ጉዳይ በሆነ ሰው ነው፡፡ አንዳድ ግዜ ግን የሕይወት ታሪክ በሌላ ሰው ይጻፋል፡፡ ግለ ታሪክ አብዛኛው ግዜ የፀሐፊው የሕይወት ታሪክ ስለሆነ ጭምጡ ከሀይማኖታዊ እስከ የግል መለያው ድረስ ለልጆቹ ማስተላላፍ ይችላል፡፡ የግል ታሪክ ዓለማው የደራሲውን የሕይወት ተሞክሮ ና ስኬቶችን ማሳየት ነው፡፡ አብዛኛቹ ግለታሪኮች በተለምዶ በርእሰ ጉዳይ ሕይወት ውስጥ በኋላ ያፃፉሉ፡፡ የተፃፈው ከፀሐፊው እይታ አንጻር ነው፡፡ ስለዚህ ታሪኩን ለመግለጽ በተለምዶ የመጀመሪያው ሰው መለያዎችን ይጠቀማል፡፡ የግል ታሪክ ብዙ ግዜ የሚጀምረው ገና በልጅት ግዜ ሲሆን በደራሲው ሕይወት ውስጥ ያሉ ቁልፍ ክንውኖች በግዜ ቅደም ተከተል ይዘረዘራል፡፡

ግለ ታሪኮቹ ብዙን ግዜ አንድ ሰው የት እንደ ተወለደ እና እዳደገ፣ ስለትምህትርታቸው ፣ስለ ስራቸው፣ስለ ሕይወት ልምዳቸው፣ ስለ አጋጠማቸው ተግዳሮቶች እና ዋና ዋና ስኬቶቻቸው መረጃን ያካትታሉ፡፡ አልፎ አልፎ የግል ታሪክ ከአንድ ሰው ማስታወሻ ደብተር ወይም ትውስታዎች ይፈጠራሉ፡፡ ማስታወሻ ደብተር ጥቅም ላይ በሚውልበት ግዜ ደራሲው ውብ ግዜ ቅድመ ተከተል እና በአንድ የተጣመረ ታሪክ ለመፍጠር ማደራጀት አለበት፡፡ ታሪኩ አንድን የተወሰነ ክስተት ለመግለጽ ወይም ብልጭታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ዋናው የታሪክ መስመር ከፀሐፊው የልጅነት ሕይወት ጀምሮ እስከ አሁን ዝግጅታቸው ድረስ በግዜ ቅደም ተከተል መከተል አለበት፡፡ ግለ ታሪክ (Ato biyogerfi) ማለትም ግለ ታሪክ በግለሰቡ ሲፃፍ

የበለጠ ተጨማጭ የመሆን አዝማሚያ አለው። ይህ የሆነበት ምክንያት በርእሰ ጉዳዩ የሚያካትተተው ስለ አንድ የተወሰነ ሁኔታ በራሳቸው ትውስታ ላይ ተመስርተው እውነታውን ያቀርባሉ። ታሪኩ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የፀሐፊውን አስተያየት ይሸፍናል እና አንዳንድ ሁኔታዎችን ሲቃኙ ስለ ስሜታቸው ዘገባ ያቀርባሉ። በግለሰቡ የሚፃፉ ግለ ታሪኮችን ግላዊ እና የግለሰቡን የፈጠራ ችሎታ ትኩረት የሚያደርግ ነው። ነገር ግን በሶስተኛ ወገን ስለመ አንድ ግለሰብ የሕይወት ታሪክ በሚጻፍበት ወቅት የግለሰቡን ፈጠራ የተካተተበት ሳይሆን ፀሀፊው የራሱን ችሎታ ተጠቅሞ ዘገባ ማቅረብ ያሆናል።

## የህይወት ታሪክ ርዕሰ ጉዳዮች

የህይወት ታሪክ በሚጽፉበት ጊዜ ሦስት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል። በህይወት ውስጥ ማንነት ላይ ትኩረት ያደርጋል።ሕይወት ለባለ ታሪኩ ምን ማለት እንደ ሆነ እና የወደፊቱንስለ ህይወት ባለ ታሪኩ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል በሚሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል። በዚህ መሰረት "የመጀመሪያው የክርስቲያን መሪ ቅዱስ አውግስጢኖስ የግሉን የሕይወት ታሪክ ከተጻፈ ከ400 ዓ.ም ጀምሮ የሕይወት ታሪኮች መፃፍ ጀምረዋል። የህይወት ታሪክ በአንድ ሰው የተፃፈ ስለራስ ህይወት መረጃ ነው። የህይወት ታሪክ በሚጽፉበት ጊዜ ህይወት አጋጣሚዎች ሁሉ በተቻለ መጠን በማብራራት አስደሳች እውነታ ሥነ ጽሁፋዊ ለዛ በማላበስ መፃፍ ተገቢ ነው። የህይወት ታሪክ ሲፃፍ መጀመሪያ ስለ ህይወት ብዙ እውነታዎችን በማካተት ይጀመራል። ብዙ መረጃ መስጠት የሚችልሆኖመፃፍ አለበት። መግቢያ ከተፃፉ በኋላ፣የመጀመሪያውን የህይወት ታሪክ አንቀጽ ለመጀመር የሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ለምሳሌ መቼት፣የትውልድቦታ፤የሚኖሩበት ቦታ (ከተማእናግዛት)፤ስለ ትምህርታቸው ፣ስለማህበራዊ ሕይወታ ቸውትኩረት ማድረግ አለበት።ከዚህ በተጨማሪም የህይወት ታሪክን የተመረጡ ተግባራት እናመልካም ስምን መግለጽ ላይ ማተኮር አለበት።እያንዳንዱ የህይወትታሪክን አንቀጽ በሚፃፍበት ጊዜ የባ ለታሪኩን የህይወት ተሞክሮዎች እውነታዎችን ማካተት አለበት።ለምሳሌ ማንኛውም ሁኔታየተገኙ ሽል ማቶች፤ትምህር ትደረጃ፤ ኮሌጅ ከፍተኛ ትምህረት ሁኔታዎችን ማካተት አለበት(ኢንሳይክሎፔድያ፣1992)። በአጠቃላይ የህይወት ታሪክ በሚፃፍበት ጊዜ የሚከተሉትን ግለ ታሪክ ማተኮሪያዎቹን ይዞ፣ ፀሀፊው የታሪክ መዋቅር ማበጀት፣ባለታሪኩን መርጦ ለጽሁፉ የኢልቦለድ አፃፃፍን ጥበቦች ይዞ ያተርካል። ከተዘረዘሩት ማተኩርያ ውስጥ እንደባለታሪኩ ተሳትፎ ተግባራት እንዲሁም ሕይወት ታሪካዊ አቅጣጫ እና የጸሐፊው ምርጫ አንዳዶቹ በረጅሙ ከፍ ያለ ትረካ ጊዜ ሊሰጣቸው ይችላል። አንዳንዶቹ ደግሞ አነስ ባለ መልክ ሊተረኩ ይቻላሉ(ዘሪሁን፣2013)።

### 2.1.3 የህይወት ታሪክ ዓይነቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚካተቱ የሕይወት ታሪክ ዓይነቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡የሕይወት ታሪክ ጽሁፎች የባለ ታሪኩን አስተዳደግ እና የሥራ መስክ ሕይወት እና ልምድ ላይ ልዩ ዕይታን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ፣ የሕይወት ታሪኮች በትኩረት፣ በአጻጻፍ ስልታቸው እና በአቀራረባቸው በስፋት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ የተለመዱ የሕይወት ታሪክ ዓይነቶች አሉ፡፡ እነሱም

**የተለመደ የህይወት ታሪክ፡-** ይህ አይነት የህይወት ታሪክ ዋና ዋና ሁነቶችን፣ ስኬቶችን፣ ግንኙነቶችን እና ተሞክሮዎችያጋጠሙ ተግዳሮቶች የሚዳስስ የግለሰብ ሕይወት አጠቃላይ ዘገባ የሚያቀርብ ነው ፡፡ የተለመደ የሕይወት ታሪክ ዓላማው ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ዝርዝር እና ሚዛናዊ አጭር መግለጫ ማቅረብ ነው፡፡

**ግለ ታሪክ** (Biography) **፡-** የህይወት ታሪክ በርዕሰ ጉዳዩ በባለ ታሪኩ ግለሰብየተፃፈ የህይወት ታሪክ ሲሆን ይህም የባለታሪኩ ሕይወት ታሪክበ ግለሰቡ ተጽፎ የሚቀርብ ነው፡፡በዚህ የሕይወት ታሪክ ዓይነት ስለ ባለታሪኩ ሃሳቦች፣ ስሜቶች፣ልምዶች እና ግንዛቤዎችን ይሰጣል፡፡

**ማስታወሻ፡** ትዝታዎች ከግለ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ነገርግን ማስታወሻ አጠቃላይ ዕይታን ከማቅረብ ይልቅ በጸሐፊው ህይወት ውስጥ በተወሰኑ ወቅቶች፣ ጭብጦች ወይም ክስተቶች ላይ ያተኩራል፡፡ማስታወሻዎች ወይም ትዝታዎች ብዙውን ጊዜ በግል ልምዶች፣ ስሜቶች እና ነጸብራቆች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

**የወል የሕይወት ታሪክ፡-** የወል የሕይወት ታሪክ የሚያተኩረው የወል ወይም የቡድን ባህሪያትን፣ ልምዶችን ወይም ግንኙነቶችን በሚጋሩ የግለሰቦች ወይም ቡድኖች ትኩረት የሚያደርግ የሕይወት ታሪክ ዓይነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወል የሕይወት ታሪክ በአንድ የተወሰነ ቤተሰብ፣ በማህበረሰብ ወይም በማህበራዊ ቡድን የህይወት ታሪኮችን ሊያካትት ይችላል፡፡

**ሥነ-ጽሁፍዊ የህይወት ታሪክ፡-** የስነ-ጽሁፋዊ የህይወት ታሪክ አይነት የሚያተኩረው በጸሃፊዎች፣ ባለቅኔዎች ወይም ሌሎች የስነ-ጽሁፍ ሰዎች ህይወት ላይ ነው፡፡ እነዚህ የሕይወት ታሪኮች የርዕሰ ጉዳዩን ሕይወት ከሥራቸው፣ ከተጽዕኖቻቸው እና ከሥነ-ጽሑፋዊ ትሩፋቶቻቸው ጋር በማገናኘት ይዳስሳል፡፡

**ታሪካዊ የህይወት ታሪክ፡-** ታሪካዊ የህይወት ታሪኮች የሚያተኩሩት በታሪካዊ ክስተቶች፣ እንቅስቃሴዎች ወይም ወቅቶች ውስጥ ጉልህ ሚና በነበራቸው ግለሰቦች ላይ ነው፡፡ እነዚህ የህይወት ታሪኮች ርዕሰ ጉዳዩ የኖረበትን ሰፊ ታሪካዊ አውድ ግንዛቤን ይሰጣል፡፡

**የታዋቂ ሰዎች የሕይወት ታሪክ፡-** የታዋቂ ሰዎች የሕይወት ታሪክ በመዝናኛ፣ ስፖርት፣ ፖለቲካ ወይም ሌሎች መስኮችየሕይወት ላይ ያተኩራል፡፡ እነዚህ የህይወት ታሪኮች ብዙውን ጊዜ የርዕሰ ጉዳዩን ወደ ታዋቂነት፣ የግል ትግል እና የህዝብ ገጽታ ያጎላል፡፡

**ስነ ልቦናዊ-የሕይወት ታሪክ ፡-** የስነ-ልቦና የሕይወት ታሪክ ወደ ርዕሰ ጉዳዩ የአዕምሮ ውስጣዊ አሠራር ውስጥ በመግባት ስብዕናቸውን፣ ተነሳሽነታቸውን እና የስነ-ልቦና እድገታቸውን መርምሮ የሚፃፍ የሕይወት ታሪክ አይነት ነው፡፡ ይህ አይነት የህይወት ታሪክ ብዙውን ጊዜ የስነ-ልቦና ንድፈ ሃሳቦችን እና ዘዴዎችን ይሳያል፡፡

**ወሳኝ የህይወት ታሪክ፡-** ወሳኝ የህይወት ታሪክ የህይወት ታሪክ መረጃን ከባለ ታሪኩ ስራዎች ወይም ወሳኝ አስተዋጾ ከትንተና ጋር አጣምሮ የሚያቀርብ ነው፡፡ ይህ የህይወት ታሪክ ከባለ ታሪኩ ህይወትእና ፈጠራ ወይም በአእምሮአዊ ውጤት መካከል ስላለው ግንኙነት ግንዛቤዎችን ይሰጣል፡፡

**ተጽእኖ ፈጣሩ ግለሰቦች የህይወት ታሪክ፡-** ተጽኖ ፈጣሪ ግለሰቦች የህይወት ታሪክ በአጠቃላይ ታዳሚ የተፃፉ ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩት በታዋቂ ወይም ተደማጭነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ ነው፡፡ ይህ የህይወት ታሪክ ዓላማው በአሳታፊ ተረት መልክ እናበቀላል አገላለጽ አንባቢዎችን ለማዝናናት፣ ለማሳወቅ እና ለማነሳሳት የሚፃፍ ነው፡፡

## 2.2 የሕይወት ታሪክ የአጻፃፍ ዓይነቶችና ምድቦች

ግለ ታሪክ የባለ ታሪኩ የሕይወት ውጣ ውረድ በራሱ አተያይ ያቀርባል፡፡ የአጻፃፍ ዓይነቶቹም በዓብይነት ከሚተኮርባቸው ገጽታዎች አንፃርበሚከተሉትምድቦችሊከፋፈሉይችላሉ፡፡

**ትኩረት ተኮር** (Thematic) **ግለታሪክ ፡-** አንድጸሐፊየጉዳዩንሕይወትየሚገልጽበትናየሚተርክበትየሕይወትታሪክዓይነትነው፡፡ግንአንዳንድሌሎችጉዳዮችንያጎላል፡፡**ትኩረት ተኮር** (Thematic) ግለታሪክንየመጻፍዓላማእውነታዎችንማቅረብብቻሳይሆንአስቀድሞየተወሰነአመለካከትንመስጠትነው፡፡

**የዘመናትታሪክ** (Chronological) **፡-** የዘመንቅደምተከተልየሕይወትታሪክ የባለ ታሪኩ የሕይወት ታሪክ በቅደምተከተልየሚያቀርቡበትየሕይወትትረካአይነትነው፡፡ከልጅነትጀምሮበተለያዩየህይወትደረጃዎች ውስጥያልፋል፡፡በዚህየህይወትታሪክአይነት፣ ባለታሪኩ አጠቃላይልምዳቸውንእና ወጥነት ያለው

እይታለማቅረብያለመሲሆንይህምአንባቢዎችበጊዜሂደትየተፈጥሮክስተቶችንእንዲከታተሉያስችላቸ ዋል፡፡

***ሃይማኖታዊ/መንፈሳዊየሕይወትታሪክ፡-*** *ሀይማኖታዊየህይወትታሪክ ባለ ታሪኩ በሀይማኖቱ መንፈሳዊ ሕይወቱ ለማሳየት የተፃፈ ሁነተቶች ወይምልምዶችስብስብነው፡፡*

***የሕይወት እጣ ፋንታ ግለታሪክ ፡-*** *የሕይወት እጣ ፋንታ ግለታሪክ የህይወት ጉዞን በማንፀባረቅ እና የስራ ምርጫ የተደረገባቸውን ቁልፍልምዶችመለየት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ይህ የአስተሳሰብለውጥ የሚያመጣ አንባቢዎችን የሚስብ የህይወትታሪክነው፡፡ የሕይወት ጉዞን የሚመሩክስተቶችን ያካተተ ነው፡፡*

***ልብወለድየህይወትታሪክ፡-*** *ልብወለድየህይወትታሪክ የባለ ታሪኩን ልምድ እውነትን ሊያሳ በሚችል መልኩ የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ሊያሳይ በሚችል መልክ የሚጻፍ የሕይወት ታሪክ ነው፡፡ ይህ አይነት ሕይወት ታሪክ የባለ ታሪኮችን ማንነት ለመጠበቅ በገሀዱ ዓለም ውስጥ ያሉ ግለሰቡን በቀጥታ የማይገልፁ ግን እውነታን የሚያሳዩ ታሪኮች የተካተቱበት የግለ ታሪክ ነው፡፡ይህ አፃፃፍ የሚጠቅመው የባለ ታሪኩ ሊሰወሩ ወይም ሊደበቁለት የሚፈለጉ አንዳንድክፍሎች በሚኖርበት ግዜ ጥቅም ላይ የሚውል አፃፃፍ ነው፡፡ በዚህአይነትየህይወትታሪክውስጥክስተቶችለጭብጥወይምለሥነጥበባዊዓላማዎችሊጋነኑወይምሊቀ የሩይችላሉ፡፡*

***የዘመን የህይወት ታሪክ ፡-*** *ይህ የዘመን የሕይወትታሪክ ባለታሪኩ ከልደታቸው ወይም ከልጅነታቸውጀምሮእስከመጽሐፉበሚጻፍበትጊዜድረስየሕይወትዘመናቸውንሁሉ የሚዘግብነው፡፡የዚህ የህይወትታሪክ ፀሀፊዎች በሚተረኩበትጊዜየዘመንአደረጃጀትን ይመርጣሉ፤ ምንምእንኳንይህአስፈላጊባይሆንም፡፡ከተወለዱበትቀንጀምሮእያንዳንዱቅጽበትማካተት ባይኖርበትም ባለ ታሪኩ በሕይወትዘመናቸውሁሉየተከሰቱትንማንኛውንም ሁነቶች በጥልቀት የሚመረምር ነው ፡፡*

***ኑዛዜ ግለ ታሪክ ፡-*** *የኑዛዜግለ-ታሪኮችየተጻፉትብዙውንጊዜየተደበቀምስጢርወይምሊገልጡትበዕልፈ ሕይወታቸው የሀይማኖት አባት ወይም ሌላ ግለሰብ እዲቀርብላቸው በማድረግ ስለ ሕይወታው የሚናገሩበት ወይም የሚናዘዙበት በጽሁፍ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህ የሕወት ታሪክ ባለታሪኩ ከሌሎች ግለሰቦች ሊሰወርላቸው ወይም ሊደበቅላቸው የሚፈልጋቸው የሕይወት ተሞክሮዎች ሚስጢርን በመጠበቅ ያደረገ የሕይወት ታሪክ ነው፡፡ ለምሳሌ ከሱስ ጋር ወይም የወንጀል ታሪክ ሊሆን*

ይችላል፡፡እንዲሁም ባለታሪኩ የተቸገረበት እና ከደረሰባቸው ለመውጣት ከሚመኙት ማንኛውም ነገር ጋር የተቆራኘ ሊሆን ይችላል፡፡

**የገጸ ምድራዊ ትውስታ** ፡- የባለታሪኮቹ የተወለዱበት ያደጉበት የኖሩበት አካባቢ መልክአ ምድራዊ መልክ ከገዛ ራስ ሕይወት እና ከሕዝቡ አኗኗር ጋር ተጣጥሞ የሚቀርብት ነው፡፡

**ምሁራዊ ግለ ታሪክ** ፡- ከግለሰቦች ወይም ከቡድኖች ጋር የነበረው ቅርርብና አግባብ አጉልቶ የሚያሳ፣ወዳጅነት የእውቀት ተጋሪነትን የሀሳብ መለዋወጥንና የኑሮ አብሮነት እና ከተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖች ጋር የነበረውን ተሳትፎ የሚያሳ ነው፡፡

**ጭብጥ ግለ ታሪክ**፡- የተለያዩ የማህበረሰብ ነክ ጭብጦች አሳሳቢ ጉዳዮች በዐብይነት የሚቀርብበት ነው፡፡

**ሙያዊ እና የስራ መደብ** (Vocational and Occupational) **ግለ ታሪክ** ባለታሪኩ በሕይወት ዘመኑ በአከናወናቸው የተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ያተኩራል፡፡ የሀገር መሪነት የመሪነት ታሪኩን፣መምህሩ የመምህርነት ታሪኩን፣ የሕክምና ባለሙያው የሐኪምነት ታሪኩን፣ነጋዴው የነጋዴነት ታሪኩን እና የጦር መኮንኑ የጦር ሜዳ ውሎውን ታሪክ የሚጽፉበት ዓይነት ነው፡፡

**ታሪካዊ ግለ ታሪክ** (historical)ግለ ታሪክ፡- በአብዛኛው በአንድ ሀገር የተወሰነ ዘመን ታሪክ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ባለ ታሪኩ በዘመኑ የታየውን፣ የታዘበውን የሀገር ታሪክ ይተርካል፡፡እንዳየሁትና እንደሰማሁት ብሎ ዐበይት ዓላማው የዘመኑ ታሪክ መግለጽ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ታሪክ ታሪከ ግል ጸሐፊው በታሪኩ የነበረውን ሚና ያስታውሳል፡፡ የፈታኝ አጋጣሚ የስቃይ የተጋፍጠ እና የትግል ሁኔታው ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ነው፡፡

**የቤተሰብ ታሪክ** ፡- የቤተሰብ ታሪከ ግል የሚባለው ደግሞ የባለ ታሪኩ ማንነት ፍለጋ የዘርያ ሥር ከየት መጣን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚጻፉ ነው፡፡

## 2.3 ግለ ታሪክ ሲፃፍ ሊተኩርባቸው የሚገባ ነጥቦች

የተወለዱበት፣ያደጉበት እንዱሁም የኖሩበት አካባቢ መልክአምድራዊ ገጽታና ባህላዊ መልኮች፡፡ ከቤተሰብና ከሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጋር የነበረው ቅርርብና ወዳጅነት፡፡ የቤተሰብ ማንነት በባለ ታሪኩ እድገት ቤተሰብ አባላት የተጫወቱት ሚናከቤተሰብ ከሌሎች ግለሰቦችና የእውቀት የአሳብ መለዋወጥና በሕይወት ጎዳና የነበረው ተሳትፎ ተጋሪነት፡፡ማህብረሰቡ ውስጥ የተከናወኑ አሳሳቢ ጉዳዮች በነዚህ ውስጥ የባለ ታሪኩ መነካት ሚና ባለታሪኩ በሕይወት ዘመኑ ያከናወናቸው ተግባራት እና የተሰማራባቸው የስራ መስኮች፡፡ የዘመን ታሪክ ባለ ታሪኩ እንዳየው

እንደሰማውና እንደታዘበው እንደተሳተፈው፡፡ በአገሩ የታሪክ ሂደት ውስጥ ባለታሪኩ የነበረው ተሳትፎና የተለያዩ ገጠመኞች፡፡በማህብረሰቡ ውስጥ የተከሰቱ ድርጊቶች፣ለምሳሌ ጦርነት የፖለቲካ ቀውስ የተፈጥሮ አደጋ በእነዚህ ውስጥ ባለታሪኩ ያደረገውን ተሳትፎ እነዚህ ሕይወቱን የነኩበት ገጽታ፡፡በአገር ግንባታ ረገድ ያደረጋቸውን መስክ ባለ ታሪኩ የገጠሙት ፈታኝ ሁኔታዎች ከነዚህ ለመላቀቅ ያደረገው ትግልና ጥረት፡፡በሕይወት ታሪክ ውስጥ በመነሳት ሆነ በመውደቅ የሕይወት አቅጣጫ እንዲለውጥ ያደረጉ ግለሰቦችና አጋጣሚዎች፡፡ ባለ ታሪኩ በሕይወት ዘመኑ ለፈፀማቸው ተግባራት የተሰጡት ሙገሳዎችና ነቀፌታዎችባለታሪኩ ለሕይወትና ለሰው ልጅ እንዲሁም ለአገር ያለው አመለካከት መካተት አለባቸው፡፡(ዘሪሁን፣2013)

## 2.4 የግለ ታሪክ አፃፃፍ መርሆዎች

ግለ ታሪከ አፃፃፍ መርሆዎች ደራሲያን የህይወት ታሪክ ሲጽፉ የሚከተሏቸውን መመሪያዎች እና ሀሳቦችን ያካትታል፡፡ አንዳንድ ቁልፍ መርሆች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ትክክለኛነት ሊያንፀባርቅ ግድ ይለላል፡፡ የግለ-ታሪክ የባለ ታሪኩን የሕይወት ተሞክሮዎች እውነተኛ  መግለጫዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡በግለ ታሪክ ጽሑፍ ውስጥ ሐቀኝነትን እና ቅንነትን ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ፡፡(Gloria Anzaldúa,1987) ራስንማንጸባረቅ ማለትም ግለ-ታሪክ ብዙውን ጊዜ በጥልቀት መመርመር ማገናዘብን ይጠይቃል፡፡ ባለ ታሪኩ የህይወት ጉዟቸውን፣ ልምዶቻቸውን፣ እምነቶቻቸውን፣ እሴቶቻቸውን እና ግላዊ እድገታቸውን በትረካው ውስጥ ማንፀባረቅ ተገቢ ነው፡፡(Gloria Anzaldúa,1987) ግልጽነት እና ቅንጅት ሊኖረው ይገባል፡፡የግለ-ታሪክ በደንብ የተደራጁ እና ወጥነት ያላቸው፣አንባቢን በደራሲው የሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚመራ ግልጽ መዋቅር ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ የግዜ ቅደም ተከተል የተለመደ ትግበራ ነው፡፡ ነገር ግን ተግባር ተኮር ወይም ቲማቲክመዋቅር ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡ (Gloria Anzaldúa,1987) ዝርዝር እና ግልጽነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበትግለ ታሪክ በባለ ታሪኩ  ህይወት ውስጥ ስላሉ ጉልህ ክንውኖች፣ ቦታዎች እና ሰዎች ዝርዝር መግለጫዎች እና ዘገባዎች ጥቅም መዋል አለባቸው፡፡ የስሜት ህዋሳት የሚቀሰቅሱዝርዝር ጽሁፎችስለ ባለታሪኩ ለመተረክ መጠቀም አለባቸው፡፡(Gloria Anzaldúa,1987)□□□ድምጽ ቅላፄእና ዘዬ ትኩረት መሰጠት አለበት ግለ-ታሪክ ብዙውን ጊዜ የባለታሪኩን የድምፅ ቅላፄ እና ዘዬበአጻጻፍ ስልት ውስጥለማፀባረቅ መሞከር ባለታሪኩን የበለጠ ለአንባቢ ቅርብ ያደርገዋል፡፡ Gloria Anzaldúa,1987)□□የባህል እና የታሪክ አውደ ነጸብራቅ ማለትምግለ-ታሪክ ብዙ ጊዜ ባለ

ታሪኩን በኖረበት ባህላዊ እና ታሪካዊ አውድ ተጽዕኖ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። ባለ ታሪኮች ሕይወታቸውን በተቀረጹት የማኅበረሰብ ደንቦች፣ ታሪካዊ ክስተቶች እና ባህላዊ ተጽዕኖዎች ላይ ሊያንፀባርቅይችላል፡፡ (Gloria Anzaldúa,1987)

ሁለንተናዊ ጭብጦች እና ተያያዥነትሊኖረው ይገባል የህይወት ታሪክ በተፈጥሯቸው ግላዊ ቢሆኑም፣ብዙ ጊዜ ከተለያዩ አስተዳደግ እና ሌሎች የሕይወት ተሞክሮች ጋር የሚስማሙ ሁለንተናዊ ጭብጦችን እና ልምዶችን መዳሰስ አለበት። ባለታሪኮችታሪካቸውን ለብዙ አንባብያን ተዛማጅ እና ትርጉም ያለው ለማድረግ መጣር አለባቸው፡፡(Gloria Anzaldúa,1987)ሥነምግባር ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡የሕይወት ታሪክ በተለይ የባለ ታሪኩ የሕይወት ታሪክ አካል የሆኑትን ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮችን ሊያትቱ ይገባል።ባለ ታሪኩ ትረካቸው በሌሎች ግለሰብ ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ በማጤን እና በማስብ በአክብሮት ለማሳየት መጣር አለባቸው፡፡ (Gloria Anzaldúa,1987)ክለሳ እና እርማት ሊተገበር ይገባል፡፡ የግል ታሪክ ግልጽነት፣ ወጥነት እና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ብዙ የክለሳ እና የአርትዖት ስራዎችን ማካሄድአለባቸው። ረቂቁን ለማሻሻልደራሲልምድ ያለውአንባቢ ወይም አርታዒ አስተያየት መውሰድ አለባቸው፡፡ (Gloria Anzaldúa,1987)ዓላማ እና ግንዛቤ ትኩረት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ የግል ታሪክ የህይወት ታሪካቸውን ዓላማ እና የታለመላቸውን ተመልካቾች በግልፅ ማስረዳት አለበት። ዓላማ እና ግንዛቤ ያለው የሕይወት ታሪክ ባለ ታሪኩን መግለጽ፣ ታሪካዊ ሰነዶች በዓላማ እና ግንዛቤ ሊፈጥሩ በሚችል መልክ መዘጋጀት አለባቸው፡፡(Gloria Anzaldúa,1987)

## 2.5 የእንስትነት(ሴትነት) (Feminism Theory) ንድፈ ሀሳብ

የመጀመሪያዋ የእንስትነት (feminism) ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ በፓሪስ ከተማ ከቡርዣው ቤተሰብ የተወለደችውና ከ1908-1986 የኖረችው ሲሞን ዴ ቢዩቮይ ነች። አድናቆትንና ጥልቅ ተጽዕኖ ማሳረፍ በቻለው ‘ ሁለተኛው ጾታ’ (1949) በሚለው መጽሐፏ ትታወቃለች። ሲሞን ‘ሌላነት’ ወይም ‘ባዕድነት’ የሰው ልጅ መሰረታዊ የዕይታ ማዕቀፍ ነውትላለች። እንደሲሞንሴትንየምንለያትናትርጉምየምንሰጣትከወንድአንጻርእንጂከራሷ ከሴት ወይም ‘ሴትነት’ አንጻር አይደለም። እሷ የአጋጣሚ ክስተት ነች። ከተፈላጊው ከወንድ አንጻር ሴት አላስፈላጊእንደሆነችአድርገንነውየምናያት። ወንዱነውዋናውጉዳይ። እርሱ ፍጹምነው። እሷግን‘ሌላ’ወይም‘ባዕድ’ነች። ሲሞንእውነቷንነው።ወንዶቹቢበዛቢበዛ‹‹ዘሲግኒፊካንትአዘር›› /The

Significant other/ የሚልተቀጽላብንመርቅላቸውነው:: እንስትነት (feminism)ን አብዛኞቻችን የምናውቀው የአክራሪ እንስትነትን ጽንሰ ሀሳብ በምንረዳበት መንገድ ነው:: ይህ የወንዶች ብቻ ሳይሆን የሴቶችም አመለካከት ነው:: ለማንኛውም መሠርታዊው የእንስትነት ጽንሰ ሀሳብ የሚለው ወንድና ሴት በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊና በፖለቲካው መስክ እኩል ይሆኑ ዘንድ መጣር ነው:: ይህ ዋነኛው(core) የእንስትነት ጽንሰ ሀሳብ ነው:: ነገር ግን በርካታ ቅጂዎች አሉት:: እያጠራን መሄዱ መልካም ሳይሆን አይቀርም::

### 2.5.1 ባህላዊ እንስትነት /Cultural Feminism/

ሴትና ወንድ መሰረታዊ ልዩነት አላቸው ብሎ ይቀበላል:: እንደዚሁም የሴቶች ልዩነት የተለየና ሊከበር(ሊወደስ) ይገባዋል ይላል:: የስነ አፈጣጠራቸው ልዩነት በባህሪይ ላላቸው ልዩነት አስተዋጽኦ አድርጓል ባይ ነው:: ለምሳሌ ሴቶች ከወንድ ይልቅ ደግና ቀና ናቸው ይላል:: ይህም ሴቶች የሚመሩት ዓለም ከጦርነት ነጻ ይሆናል የሚለውን አመለካካት ወልዷል:: የባህል እንስትነት ጾታዊነትን(sexism) ለማጥፋት የሴቶች የተለዩ ስጦታዎችንና ክህሎቶችን ያደንቃል:: የሴቶች መንገድና ልምድ የተሻለ ነው ብሎም ያስባል:: (Derrida,1996)

### 2.5.2 ኤኮፌምኒዝም /Eco-feminism/

የአባሆይ (Patriarchal) ፍልስፍናዎች ለሴቶች ለህጻናትና ለሌሎች በዙሪያችን ለሚገኙ ህይወት ላላቸው ነገሮች አይጠቅምም ይላል:: የአባሆይ መዋቅር ላለፉት 5000 ዓመታት የቆየ ሲሆን የሚያተኩረው በሴቶች ላይ በሚደረግ የጸና ጭቆናና ለመቆጣጠር በማይመቸው የሴቶች 'ያልተገራ የዱር ባህሪይ' ላይ እንደሆነ ያትታል:: በአጠቃላይ አለማችን የተሻለ ሰላም መረጋጋትና ዘለቄታዊ ልማት እንድታመጣ ሴቶች የማህበረሰብ መዋቅርና ሚና ማዕከል ወደ ሆኑበት የእማሆይ ዘመን መቀየር ግድ ይላል ብሎ ይቀበላል፡፡ የአባሆይዘመንለአካባቢደንታየሌለውናከአካባቢውኢኮሎጂየሚገኘውንማንኛውንምሀብትበ ማውጣት/Extractive use/ መጠቀምላይያተኮረስለሆነበእማሆይዘመንይህንማስቀረትይቻላልብለውያስባሉ:: (Crenshaw,1989)

### 2.5.3 ግላዊነት ወይም ሊብሪቴሪያን እንስትነት /Individualist or Libritarian/

ይህ 'አነስተኛ' የመንግስት ቁጥጥር ወይም ወደ አናርኮካፒታሊስትነት የቀረበ ፍልስፍና ነው:: ዋነኛው ትኩረት የግለሰቡ ነጻነት ራስን መቻል መብት አርነት ከተጽዕኖ መላቀቅና ብዙህነት ነው:: በሰፊውም ወንድን ያካትታል:: እንደዚሁም ትኩረት የሚያደርገው ሴቶችም ሆነ ወንዶች በጾታቸው ምክኒያት ስለሚደርስባቸው ተጽዕኖዎችና ተግዳሮቶች ነው::(Butler,1990)

### 2.5.4 ቁሳዊ እንስትነት /Material Feminism/

ይህ እንቅስቃሴ የተጀመረው በ19ኛው ክ/ዘመን መገባደጃ ላይ ነው:: የማጀት ሥራ ተጽዕኖ ለመቀነስ በሚልና በልማዳዊው የሴቶች የቤት ውስጥ ሥራዎች ለምሳሌ የምግብ ማብሰል ዓይነት ተጽዕኖዎች ላይ ያተኮረ ነው::(collins,1990)

### 2.5.5 ለዘብተኛ እንስትነት /Moderate Feminism/

ይህ የእንስትነት ጽንሰ ሀሳብ በወጣት ሴቶች የተሞላና ታሪካዊ የሴቶች ጭቆናና መድልዎ አይመልከተንም ብለው የሚያስቡ ሴቶች ጥርቅም ነው:: እነዚህ ልማዳዊውና የቀድሞው የእንስትነት ሀሳቦች ከአሁኑ ጊዜ ጋር አይሄዱምና ለውጥ ያስፈልጋቸዋል:: እንስትነት/feminist/ የሚለውን እንደ ስም መቀበል ይከብዳቸዋል::(Butler,1993)

### 2.5.6 ብሔራዊ የሴቶች ተቋማት /National Women's Organizations/

እኒህ ሴትና ወንድን እኩል ለማድረግ ለሴቶች የተለዩ መብቶችና ጥቅሞችን ማስጠበቅ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ:: ወንዶች ለሴቶች ጥቅሞች ተግዳሮቶች መሆን የለባቸውም ይላል:: ሴቶችን ከወንድ እኩል ለማድረግ ሴቶች ላይ ማተኮርና ለሴቶች የተለየ ጥቅም መቆም ያስፈልጋል ይላሉ:: (Sandarbem,1993)

### 2.5.7 ጽንፈኛ እንስትነት /Radical Feminism/

በርግጥ ይህ ጽንሰ ሀሳብ ለብዙዎቹ የእንስትነት ጽንሰ ሀሳቦች መራቢያ ሆኖ አገልግሏል::ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበረባቸው አመታት ከ1967-75 ያሉት አመታት ናቸው:: በአሁን ዘመን ያን ያህል ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የለውም:: ይሁንና ይህ ጽንሰ ሀሳብ የሴቶች ጭቆና በጣም መሰረታዊው ጭቆና ነው ብሎ ይረዳል:: እንደዚሁም የዘር የባህልና የምጣኔ ሀብት ድንበሮችን አልፎ ይተገበራል:: በማህበራዊ ለውጥ በተለይም በአብዮት ልኬት ያለ ለውጥን

ይናፍቃል ይላል:: በተለይ በስነ ፍጥረት ላይ በተመሰረተ ባህርይና በባህል ተጽዕኖ ላይ በተመሰረተ ባህርይ መካከል ልዩነት ለመፍጠር ይሞክራል::(Zimmerman,1987)

## 2.6 የሴትነትግል(የሴትነት ግዴ ትግል) ፅንሰ-ሀሳብቁልፍጽንሰ-ሐሳቦች

የሴትነትፅንሰ-ሀሳብየተለያዩአመለካከቶችንእናአቀራረቦችንየሚያጠቃልልሰፊመስክነው ፤ የሥርዓተ-ፆታአለመመጣጠንንለመረዳትእናፈታኝነው::አንዳንድቁልፍፅንሰ-ሀሳቦችእናበሴትነትጽንሰ-ሀሳብውስጥታዋቂሰዎች፣ከጥልቅፍለጋማጣቀሻዎችጋርእዚህአሉ፡ቁልፍጽንሰ-ሐሳቦች

*ሀ. ፓትርያርክ(አባዊ ሥርአት)* :- ወንዶችየመጀመሪያደረጃስልጣንየሚይዙበትእናሴቶችብዙጊዜየተገለሉበትማህበራዊስርዓት:: (Crenshw,1989)

**ለ.ኢንተርሴክሽንሊቲ፡-** እንደዘር፣ጾታእናመደብያሉየተለያዩየማህበራዊመለያየትዓይነቶችመስተጋብርእናልዩየጭቆናልምዶችንእስተዋፅዖያደርጋሉየሚልሀሳብነው::(Collins,1990)

ሐ. ***የሥርዓተ-ፆታአፈጻጸም፡-***የፆታማንነትአንድየሆነሳይሆንአንድየሚያደርገውነውየሚለውጽንሰ-ሐሳብ;ሥርዓተ-ፆታየሚከናወነውበአፈጻጸምነው:: (Butler,1993)

*መ.* ***የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታ፡-***የሥርዓተ-ፆታሚናዎችእናማንነቶችየሚፈጠሩትበተፈጥሮከመሆንይልቅበማህበራዊሂደቶችነውየሚለውአስተሳሰብ::(Butler,1993)

*ሠ.* **የወንዶችእይታ፡**የእይታጥበባትእናስነጽሁፍሴቶችንከወንድአንፃርየሚያሳዩበትንመንገድለመግለጽበላውራሙልቬይየተፈጠረቃልነው፣ሚናቸውንየሚቃወሙእናየሚገድቡ:: (Mulviy,1975)

### 2.6.1 ፓትርያርክ (አባዊ ሥርአት)

ፓትርያርክበሴትፅንሰ-ሀሳብውስጥዋናፅንሰ-ሀሳብነው፣እሱምወንዶችየመጀመሪያደረጃስልጣንንየሚይዙበትእናበተለያዩየህብረተሰብተቋማትውስ

ጥየበላይነታቸውንየሚያሳዩበትንማህበራዊስርዓትነው።ይህጽንሰ-ሐሳብየሥርዓተ-
ፆታአለመመጣጠንእናኃይልበተለያዩፆታዎችየሚከፋፈልባቸውንመንገዶችለማብራራትይረዳል።

**ትርጉምና ባህርያት በተመለከተከዚህ እደሚከተለው ይገለፃል።**

ሐይል ናሥልጣን፡-
በአባቶችሥርዓትወንዶችበአጠቃላይበፖለቲካ፣በኢኮኖሚናበማኅበራዊጉዳዮችየሥልጣንናየሥልጣን
ቦታዎችንይይዛሉ።ይህብዙውንጊዜወደአለመመጣጠንየሀብቶች፣እድሎችእናየውሳኔሰጪሃይልተደራ
ሽነትይተረጎማል።

የሥርዓተ-
ፆታተዋረድ፡ፓትርያርክየወንድእሴቶች፣አመለካከቶችእናሚናዎችበሴቶችእናሁለትዮሽባልሆኑግለሰ
ቦችላይልዩመብትየሚያገኙበትተዋረዳዊመዋቅርይመሰርታል።ይህተዋረድብዙውንጊዜየወንድየበላይነ
ትንበሚያጠናክሩባህላዊ፣ሃይማኖታዊወይምማህበራዊደንቦችይጸድቃል።

ተቋማዊአለመመጣጠን፡ፓትርያርክነትእንደቤተሰብ፣መንግስት፣ትምህርትእናየስራቦታባሉተቋማት
ውስጥተካቷል።ለምሳሌ፣ባህላዊየቤተሰብአወቃቀሮችብዙውንጊዜወንዶችንየቤተሰብአስተዳዳሪአድርገ
ውያስቀምጣቸዋል፣የሕግእናየኢኮኖሚሥርዓቶችደግሞእንደውርስእናየደመወዝእኩልነትባሉአካባቢ
ዎችወንዶችንሊደግፉይችላሉ።

**ባህላዊእናማህበራዊደንቦች፡-**

የአባቶችእሴቶችየሚቆዩትበባህላዊእናማህበራዊደንቦች፣የሚዲያምስሎችን፣ስነ-
ጽሁፍንእናባህላዊየስርዓተ-
ፆታሚናዎችንጨምሮግለሰቦችበጾታላይተመስርተውእንዴትመሆንእንዳለባቸውየሚጠቁሙናቸው።
(Crenshay,1989)

### 2.6.2 ኢንተርሴክሽንሊቲ

ኢንተርሴክሽንሊቲየወቅቱየሴቶችፅንሰ-ሀሳብቁልፍፅንሰ-
ሀሳብሲሆንየተለያዩየማህበራዊመለያየትዓይነቶች -
እንደዘር፣ጾታ፣ክፍል፣ጾታእናሌሎችማንነቶችእንዴትእርስበእርስእንደሚገናኙእናውስብስብየጭቆና
እናልዩመብቶችንእንደሚፈጥሩየሚመረምርነው።ይህማዕቀፍየግለሰቦችንየአድልኦእናየእኩልነትልም

ዳቸውንለመቅረጽበርካታየማንነትገጽታዎችእንዴትእንደሚገናኙለመረዳትይረዳል።ፍቺእናአመጣጥ በተመለከተእደሚከተለው ይገለፃል፡፡ኢንተርሴክሽንሊቲየተለያዩየማንነትእናየማህበራዊምድቦች (እንደዘር፣ጾታ፣ክፍል፣ጾታዊነት፣አካልጉዳተኝነት፣ወዘተ) ልዩልዩየጭቆናወይምልዩጥቅሞችንእንዴትእንደሚፈጥሩየሚዳስስየትንታኔማዕቀፍነው።ማህበራዊ ምድቦችእራሳቸውንችለውየሚሰሩናቸው፡፡የሚለውንሀሳብይሞግታልእናየተለያዩየማንነትዓይነቶችእ ናአለመመጣጠንእርስበርስየተያያዙእናእርስበርስየሚደጋገፉናቸው፡፡

"ኢንተርሴክሽንሊቲሊቲ" የሚለውቃልበ1989 በኪምቤርሌክሬንሾየተፈጠረነው።የህግምሁርእናወሳኝየዘርፅንሰ-ሀሳብምሁርክሬንሾሀሳቡንአስተዋወቀውየባህላዊየሴቶችእናየሲቪልመብቶችትንታኔዎችውስንነቶችን ለመፍታትነው፣ይህምየሚያስከትለውንውስብስብውጤትብዙጊዜግምትውስጥማስገባትአልቻለም።ተ ደራራቢማንነቶችበ intersectionality ውስጥቁልፍጽንሰ-ሐሳቦች በርካታ የማንነት መጠሪያዎች Intersectionality ግለሰቦችልምዳቸውንእናየሃብቶችንእናእድሎችንተደራሽነትየሚነኩብዙ፣ተደራራቢማንነቶች (ለምሳሌዘር፣ጾታ፣ክፍል፣ጾታዊዝንባሌ) እንዳላቸውይገነዘባል።የተጠላለፉየጭቆናስርዓቶች፣ማዕቀፉየጭቆናስርአቶች (እንደዘረኝነት፣ሴሰኝነት፣ክላሲዝምእናግብረሰዶማዊነትያሉ) እንዴትራሳቸውንችለውእንደማይሰሩ፣ግንእርስበርስእንደሚገናኙእናእንደሚገናኙ፣ውስብስብእናዘር ፈብዙ ጎጂ ልምዶችንእንደሚፈጥርይዳስሳል።

ኢንተርሴክሽንሊቲእያንዳንዱንየማንነትዘንግበተናጠልበመመርመርየመድልዎተጽእኖሙሉበሙሉ ሊረዳእንደማይችልያረጋግጣል።ለምሳሌየጥቁርሴትልምዶችዘርንእናጾታንለየብቻበመመልከትሙሉበ ሙሉሊረዱአይችሉምይልቁንምበእነዚህማንነቶችመካከልያለውልዩመስተጋብርልምዶቿንይቀርፃሉ፡፡ ኢንተርሴክሽንሊቲማዕቀፍየተገለሉቡድኖችበዋናሴትነትእናበማህበራዊፍትህእንቅስቃሴዎችውስጥእ ርስበርስየሚገናኙማንነታቸውካልታሰቡእንዴትሊታለፉእንደሚችሉያጎላል።ለምሳሌዋናዋናሴትነትበ ታሪክውስጥበመካከለኛደረጃነጭሴቶችጉዳዮችላይያተኮረነው፡፡ብዙውንጊዜ የሴትችን የስራመደብአሳሳቢነትችላ የሚል ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ (Crenshaw,k,1989,Collins,1990 and Davis,A1981)

### 2.6.3 የሥርዓተ-ፆታአፈፃፀም

በጁዲትበትለርበሴሚናልሥራዋየሥርዓተ-ፆታችግር፡ፌሚኒዝምእናማንነትንማፍረስ (1990) ያስተዋወቀችውጽንሰሃሳብነው።ይህሃሳብየወቅቱየሥርዓተ-ፆታፅንሰ-ሀሳብየማዕዘንድንጋይሆኖባህላዊየሥርዓተ-ፆታንግንዛቤዎችንየሚፈታተንነው።የፅንሰ-ሃሳቡንዝርዝርእይታእነሆ- ፍቺእናቁልፍጽንሰ-ሐሳቦችየሥርዓተ-ፆታአፈፃፀም( Gender perfprmativity)

- ትርጓሜ፡- የሥርዓተ-ፆታአፈፃፀምስርዓተ-ፆታውስጣዊወይምቋሚማንነትሳይሆንበተደጋገሙድርጊቶች፣ባህሪያትእናየማህበረሰብደንቦችየተገነባነገርነው፡፡በዚህአተያይመሰረትፆታማለትበህብረተሰቡበሚጠበቀውመሰረትግለሰቦችየሚያቀርቡትአፈጻጸምወይምተከታታይትርኢትነው።

- ቁልፍሃሳብ፡አንድሰውየያዘውየተረጋጋማንነትከመሆንይልቅጾታአንድሰውየሚያደርገውወይምየሚፈጽመውነገርነው።እነዚህትርኢቶችየተረጋጋየሥርዓተ-ፆታማንነትገጽታንይፈጥራሉ, ነገርግንይህማንነትበተደጋገሙድርጊቶችእናበማህበራዊስምምነቶችየተገኙውጤቶችናቸው።ዋናመርሆዎች

ሀ. ተግባራዊነት፡-በትለርሥርዓተ-ፆታከህብረተሰባዊደንቦችጋርበሚጣጣሙአፈጻጸምተግባራትየተመሰረተእንደሆነይከራከራሉ።ለምሳሌየተወሰኑልብሶችንመልበስ፣የተወሰኑተውላጠስሞችንመጠቀምወይምየተለየባህሪንመከተልግለሰቦችጾታቸውንየሚፈጽሙባቸውመንገዶችናቸው። ትርጓሜውምእነዚህድርጊቶችየሥርዓተ-ፆታማንነትንአያሳዩምይልቁንምበማምረትእናበመድገምያጠናክሩታል።

ለ. የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታ፡-ጾታባዮሎጂካልወይምአስፈላጊባህሪሳይሆንማህበራዊግንባታነው።የሥርዓተ-ፆታደንቦችእናየሚጠበቁትበባህላዊልምዶችእናተቋማትነው። ትርጓሜውም ሥርዓተ-ፆታየተገነባበመሆኑበተለያዩአፈጻጸሞችናአሠራሮችሊፈታእናሊገለጽይችላል።

ሐ. መፈራረስእናመቋቋም ፡- ሥርዓተ-ፆታንመደበኛባልሆኑመንገዶችወይምባህላዊየሥርዓተ-ፆታሚናዎችንበመገዳደርግለሰቦችየተመሰረቱየሥርዓተ-ፆታደንቦችንመገልበጥእናመቃወምይችላሉ።ትርጓሜውም የሥርዓተ-ፆታአፈፃፀምለአማራጭየሥርዓተ-ፆታአገላለጾችእድሎችንይከፍታልእናየፆታግትርየሁለትዮሽግንዛቤንይፈታተራል። (Butler,2004)

### 2.6.4 የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታ

የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታየስርዓተ-ፆታመለያዎች፣ሚናዎችእናተስፋዎችበባዮሎጂያዊቅድመ-የተወሰነሳይሆንበማህበራዊሂደቶችእናባህላዊደንቦችየተፈጠሩእናየሚጠበቁናቸውብሎየሚከራከርየንድፈ-ሀሳባዊማዕቀፍነው::ይህአመለካከትሥርዓተ-ፆታንእንደተፈጥሯዊወይምተፈጥሯዊባህሪከሚመለከቱትከአስፈላጊአመለካከቶችጋርይቃረናል::የሥርዓተ-ፆታማህበራዊግንባታንበጥልቀትስንመለከት የሚከተሉትቁልፍጽንሰ-ሐሳቦች አሉት፡፡

ሀ. ማህበራዊግንባታ፡-ፆታየሚገነባውበማህበራዊመስተጋብር፣በባህላዊደንቦችእናበህብረተሰቡበሚጠበቀውመሰረትነውየሚለውሃሳብቋሚ፣ተፈጥሯዊባህሪከመሆንይልቅ::ይህማለትየሥርዓተ-ፆታሚናዎችእናማንነቶችበማህበራዊነትሂደቶችየተቀረጹእናበተለያዩባህሎችእናታሪካዊወቅቶችሊለያዩይችላሉ::

ለ. የፆታሚናዎች፡-ህብረተሰቡበሚሰማቸውጾታመሰረትለግለሰቦችተገቢነውብሎየሚያያቸውየሚጠበቁእናየባህሪዎችስብስብ::እነዚህሚናዎችከልጅነታቸውጀምሮበቤተሰብ፣በትምህርት፣በመገናኛብዙሃንእናበሌሎችማህበራዊተቋማትይማራሉ::ምሳሌዎች፡የባህላዊየሥርዓተ-ፆታሚናዎችብዙውንጊዜወንዶችቆራጥእናበሙያላይያተኮሩእንዲሆኑይደነግጋል፣ሴቶችግንማሳደግእናየቤትውስጥሀላፊነቶችላይማተኮርአለባቸው::

ሐ.የሥርዓተ-ፆታደንቦች፡በአንድየተወሰነማህበረሰብውስጥለእያንዳንዱጾታተቀባይነትያለውወይምዓይነተኛባህሪየሚባሉትንየሚገልጹደንቦችእናደረጃዎች::እነዚህደንቦችበማህበራዊነት፣በተቋማትእናበባህላዊልምምዶችተፈፃሚይሆናሉ::ምሳሌዎች፡ደንቦቹበአለባበስ፣በግንኙነትዘይቤእናበሙያምርጫዎችዙሪያየሚጠበቁነገሮችንሊያካትቱይችላሉ::

መ. የሥርዓተ-ፆታግንኙነት፡- ግለሰቦችበህብረተሰባቸውየሚጠበቁትንየሥርዓተ-ፆታደንቦችእናሚናዎችየሚማሩበትእናየሚያውቁበትሂደት::ይህሂደትከቤተሰብ፣ከእኩዮች፣ከመገናኛብዙኃንእናከትምህርትተቋማትጋርባለውግንኙነትነው::ምሳሌዎች፡ህጻናትበፆታላይየተመሰረቱአሻንጉሊቶችንእንዲጫወቱወይምበጾታላይየተመሰረቱተግባራትንእንዲከታተሉሊበረታቱይችላሉ:: ሠ.ልል እናልዩነት :-የማህበራዊግንባታእይታጾታየማይለዋወጥሳይሆንልልእናበተለያዩአውዶችእናባህሎችየሚለያይመሆ

ኑንለመረዳትያስችላል።ይህማለትየሥርዓተ-

ፆታመለያዎችበጊዜሂደትሊለወጡይችላሉእናበአለምአቀፍደረጃየተስተካከሉአይደሉም።

(Butlir,1990,West,&Zimmerman,1987, connell,1995 &Bem 1993)

### 2.6.5 የወንድእይታ(The malegaze)ጽንሰ-ሐሳብ

በሴትየፊልምቲዎሪስትላውራሙልቪበ 1975 የታተመው "የእይታደስታእናትረካሲኒማ" በተጽዕኖበተሞላውድርሰቷላይያዘጋጀውወሳኝማዕቀፍነው።እናየወንድአመለካከቶችንእናየኃይልተለዋ ዋጭነትንያፀናል.የወንድእይታንአጠቃላይእይታእነሆ- ፍቺእናቁልፍጽንሰ-ሐሳቦችየወንዶችእይታፍቺ ማለት የወንድእይታየእይታባህልንበተለይምሲኒማተመልካቾችንከወንድአንፃርአለምንእንዲያዩእናእንዲተረ ጉሙየሚያደርግበትንመንገድያመለክታል።የሴቶችንተጨባጭነትእናየአካሎቻቸውንውክልናየወንድ ፍላጎትእናቁጥጥርንያካትታል. አካላት፡-የካሜራእይታ፡የካሜራእይታብዙውንጊዜየወንድአመለካከቶችንያንፀባርቃል፣በሴትገፀ-ባህሪያትላይያተኮረመልክእናየፆታፍላጎትንበሚያጎላመልኩ።የገጸባህሪያቱእይታበፊልሞችውስጥወን ድገፀ-ባህሪያትብዙውንጊዜየሴትገፀ-ባህሪያትንበተጨባጭእናበፆታዊግንኙነትሲመለከቱይታያሉ።ይህተለዋዋጭየሥርዓተ-ፆታተዋረዶችንእናየኃይልአለመመጣጠንያጠናክራል. የተመልካቾችእይታ፡- ጽንሰ-ሀሳቡተመልካቾችበተለይምወንድተመልካቾችየሴትገፀባህሪያቶችንበፆታዊዓላማእናበወንድደስታመነ ጽርእንዲመለከቱየሚጋበዙበትንመንገድያካትታል። (Mulvey,1975,McCabe&Akass,2007& Doane,1987)

## 2.7 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህጥናትጋርቀጥተኛግንኙነትያላቸውየታተሙናያልታተሙየመመረቂያፅሁፍችእና ጆርናሎችን ለ ማግኘት ጥረት ቢደረግም ማግኘት አልተቻለም፤ይሁን እንጂ በተወሰነ መልኩ የሚቀራረቡ ጥናታዊ ፅሁፍችተቃኝተዋል፡፡ስለሆነም ከዚህጥናትጋር በዘውግ ተያያዥነት ያላቸው ጥናትናምርምሮች ስራን እናማህበራዊ ህይወትን መሰረት አድርገው የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳዮችን በማሳየት በተለያየ ይዘት የቀረቡናቸው፡፡

ማርቆስ የሻነው (2000) “የኮርያ ዘማች ግለ ታሪኮች የመዋቅር የጭብት ትንተና” በአዲስአበባዩኒቨርስቲፎክሎርና ሥነ ጽሁፍ ክፍልበሁለተኛድግሪጥናትአድርጓል፡፡ የጥናቱ ዋና

ዓላማ በኮርያ ጦርነት ከተሳተፉ ቃኘው ዘማቾች ግለ ተረኮች ሰብስቦ ያላቸውን መዋቅራዊ ገጽታ ጭብጥ መፈተሽ ነው፡፡ በዋናነት የተመለከተው ግለ ተረክ ይኖሩታል ተብሎ የሚታሰበውን መዋቅራዊ በዘማቾቹ በተሰበሰቡ ግለ ተረኮች ውስጥ ያላቸውን ገጽታ ፍተሻ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ በግለ ተረኮቹ ውስጥ የተስተዋሉ አብይ ጭብጡን በግለ ተረክ ውስጥ ሊገኙ ከሚችሉ ስድስት መዋቅሮች ውስጥ በአራቱ ላይ አድርጓል፡፡ማርቆስ የሻነው በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ የኮርያ ዘማቾች ከአዲስ አበባ ሽኝት ከተደረገላቸው በኋላ ኮርያ  እስኪደርሱ ድረስ  በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ ማለፋቸው እና በጦርነቱ ጊዜ ግን ስኬታማ እንደነበሩ ያሳያል፡፡ማርቆስ የሻነው ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የኮርያ ዘማቾችን ግለ ተረኮች ላይ የተጠኚዎቹ የሕይወት ታሪክ መነሳት መቻሉ ሲሆን የእኔ ጥናት በሁለቱ ፆታዎች ንጽጽራዊ ጥናት መሆኑ እንዲሁም የምንጠቀመው ቲዎሪ የሚለየን ይሆናል፡፡

ሐረገወይን ሽዋረጋ (2004) በባህርዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የሕይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ የቀረበ ነው፡፡ ሐረገወይን ሽዋረገድ ጥናት ዋና ኣለማ የአዝማሪ ሙዚቀኛ ክዋኔአዝማሪ ዘንድ ምን እንደሚመስል ማመላከት ነው፡፡ እንዲሁም በባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ ባለታሪኮቹ ተረኮች አማካኛነት ለማሳየት የተሰራ ጥናት ነው፡፡ሐረገወይን ሽዋረገድ በጥናቷ ውስጥ የአዝማሪዎችን የሕይወት ታሪክ፣የስነ ልቦና ውቅራቸውን፣ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ችሎታ ቸውን እና የሚጠቀሙት ቃላዊ ግጥሞች በመነሳት ልታሳየን ሞክራለች፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የአዝማሪዎችን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ቃላዊ ግጥሞች በተለዩ አውዶች ላይ የሚነገሩት የይዘት ትንተና አድርጋለች፡፡የእኔ ጥናት ከሐረገወይን ሽዋረገድ ስራ ጋር የሚጋራው የህይወት ታሪክ (ግለ ታሪክ) ጉዳይ ላይ መነሳቱ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብን በባለ ታሪኮቹ ተረክ አማካኝነት ማሳየት ነው የእኔ ጥናት ትኩረት የሕይወት ታሪክ ላይየሕይወት ተሞክሮ፣ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነትና መመሳሰል መመርመር እና መተንተን በመሆኑ ጥናታችንን የተለያየ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ለናሙና የምንጠቀማቸው ግለ ታሪኮች የሙያ መለያየትና እና የእኔ ግለ ታሪክ በመጽሀፍ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለአናባቢ የቀረበ በመሆኑ ሌላው ልዩነት ነው፡፡ከላይ የቀረቡት ሁለት ጥናቶች ስለ ግለ ተረኮች (የሕይወት ታሪክ) ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ቢሆንም ጥናታቸውን ያደረጉበት አካሄድ ከኔ ጥናት ይለያሉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3 የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር የተመረጡ ሶስት ግለ ታሪኮች በፀሐይ ይትባረክ የተፃፈ የፀሐይ ጉዞ የሚለው እና በዶ/ር ትግስት ግርማ የተፃፈውን "ትሙት ግድ የለም" የውብ ድንበር የሕይወት ጉዞዋን ላይ ትኩረት በማድረግ በጥናቱ ዝርዝር አላማዎች መሰረት ፍተሻ ተደርጓል፡፡

## 3.1. ውልደት፣ እድገትና ትምህርት

### ትሙት ግድየለም / ዶክተር ትግስት ግርማ/

ትግስት ግርማ እንደፃፈችው "ትሙት ግድ የለም "የሚል መጽሀፍ ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ገጽ ያሉት ሲሆን በውስጡም በንኡስ ርእስ የተከፋፈሉ ታሪኮች እና ፎቶ ግራፍ አካቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከድሮ አውሮፕላን ማረፊያ በአሁኑ አጠራር ጦር ሀይሎች እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ከአባቷ ከአቶ ግርማ ከእናቷ ከወ/ሮ ደብረሽ ለጥይበሉ በ1945 ዓ/ም በወርሃ ሐምሌ 30 ተወለደች፡፡ ትግስት ለቤተሰቧ የመጀመሪያ ልጅ ናት፡፡በጥቂት ቀናት ውስጥ ከፍተኛ ተቅማጥና ቱከት ስለያዛት ከነበራት ኪሎ ቀንሳ ለሕይወቷ አስጊ ደረጃ ደረሰች፡፡ እናትየውም ህመም በጣም ከባድ ስለነበረ የዶክተሮቹም ሆነ የቤተሰቡም ትኩረት ከተወለደችው ህፃን ይልቅ ወደ እናቲቱ ሆነ፡፡ በዚህም ቤተሰቦቿ ተዋት "ትሙት ግድ የለም" እናቲቱን ብቻ አድኑልን በማለት እኔ

ተረሳው ትላለች ባለ ታሪኳ፡፡ ህክምናውን ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ ልጅሽ ከዚህ መውጣት አትችልም ህመሟም ተባብሷል ከእንግዲህ እዚህ ትቀመጥ በሞተች ቀን መጥተን ወስደን እንቀብራታለን፡፡ ብለው ሊሰናበቷት ወደ ተኛችበት ክፍል ሄደው ጡጦ ሲሰጧት መጥባት ጀመረች፡፡ እድለኞች ናችሁ ልጃችሁ ነቅታለች፣ጡጦ መጥባት ከጀመረች፣ተቅማጥም ማስመለስም የለም ነርሷ ስትላቸው ከእናቷ ጋር ወደ ቤት መሄድ ቻለች፡፡ እስከ ሁለት ዓመቷ በልዩ ትኩረት እና እንክብካቤ ብታድግም ወንድሟ መንክር ከተወለደ በኋላ ግን የሚሰጣት ትኩረት አነስተኛ ሆነ የቤተሰቡ አይን ወደ መንክር ዞረ በዚህ ጊዜ በውስጧ በጣም ትቀና ነበር፡፡ እንዲሁም ጉዳት ብታደርስበትም የበለጠ ጫናውና ቁጣው ወደ እርሷ ስለሚሆን ወንድሟን ክፉኛ ጠላቸው፡፡ የቤተቦቿን ልዩ ትኩረት ለማግኘት በሶስት ጉዳዮች ላይትኩረት አድርጋ መስራት ጀመረች የመጀመሪያም ሳያማት እንደ አመማት በማስመሰል መውደቅ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ታወቀባት ሁለተኛው ደግሞ በአስራ ሁለት አመቷ በትምህርቷ ጎበዝ በመሆኗ የፈለገችውን የቤተሰብ ትኩረት አገኘች፡፡ ቤተሰቦቿ በወቅቱ ደህና ገቢ ስለነበራቸው የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በጊዜው ከነበሩት በጣም ጥሩ ከሚባሉት አንደኛው ነው፡፡

ቤተሰቦቿ ወደ ሐረር ተዛውረው ሲሄዱ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት ገባች፡፡ ለእረፍት ወደ ቤተሰቦቿ ስትሄድ በመንፈሳዊ ሕይወቷ ጠንካራ ስለነበረች የአባቷን ትኩረት እና ፍቅር መልሳ ማግኘት ቻለች፡፡ ታናናሽ እህትና ወንድሞቿን ስትንከባከብ በእናቷም በኩል የቀድሞ አመለካከታቸው እና ፍቅራቸውን ማግኘት ችላለች፡፡ ከታናናሾቿም እህት አበባ የሚል ስም ወጣላት፡፡ ትግስት በልጅነቷ ፍቅር ስለጎደለባት በጥረቷ እና በብልሃቷ የቤተሰቦቿን ፍቅር ስታስገኝ፡፡ ልጅነቴ የመጀመሪያ የትግል ትምህርት ቤቴ ሆነ ትላለች፡፡

በልጅነቷ ቴአትር መፃፍና መስራት በጣም ትወድ ነበር፡፡ ነገር ግን ቤተሰቦቿ ለቀለም ትምህርት እንጂ ለሥነ ጽሁፍ ተሰጥቶ ድጋፍ ባለማግኘቷ ሳትቀጥልበት ቀርታለች፡፡

ትግስት ወጣትነቷን በጥናት እና በቤተሰብ ፍላጎት ውስጥ ነው ያሳለፈችው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስታጠናቅቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆነ በፈረንሳኝ አገር የሚሰጠው ፈተና ጥሩ ውጤት ስላመጣች ፈረንሳይን በመምረጥ ወደ ፈረንሳይ ተጓዘች፡፡ ከአንድ አመት በኋላም የመረጠችው የትምህርት መስክ ብዙም ስላልተስማማት እስኮላር ሽፕ በማፈላለግ ከፈረንሳይ ወደ ሴኔጋል (ዳካር) አፍሪካ አገር መጣች የሕክምና ትምህርት ከጨረሰች በኋላ የተላላፊ በሽታ

ስፔሺያሊስት ሆና ተመርቃለች፡፡ በዓለም ጤና ድርጅት በመቀጠር የተለያዩ የእስያ እና የአፍሪካ አገራት በመዘዋወር ሰርታለች፡፡

**የፀሀይ ጉዞ/ ፀሀይ ይትባረክ/**

ፀሀይ ይትባረክ በወለጋ ጠቅላይ ግዛት በ1923 ዓ.ም ጥር 21 ከእናቷ ከወ/ሮ አበራሽ ገብረ ሥላሴ እና ከአባቷ ከአቶ ይትባረክ ተገኝ በነቀምቴ ከተማ ተወለደች፡፡ ለቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ስትሆን አባቷ ከተወለደች ከስድስት ወር በኂላ አርፉ፡፡ ፀሐይ በተወለደችበት አካባቢ በወቅቱ ሴትን ልጅ ወደ ትምህረት ቤት ማስገባትም ሆነ ማስተማር በቤተሰቡም ሆነ በማህብረሰብ ብዙም ልማድ አልነበረም፡፡ ሆኖም ፀሀይ ከየት የመጣ እንደሆነ የማታውቀው የትምህርት ፍቅር ገብቷት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እና መማር እንዳለባት በማወቅ ከእናቷ በኩል ግን ብዙ ተግዳሮት ገጥሟት ነበር፡፡ ሆኖም ትምህርት ቤት መሄድ አለብኝ የሚለው የዘውትር ጭቅጭቂ እናቷን ሀሳብ እንዲቀየር ተደርጎ በአክስቷ ልጅ አማካኝነት ትምህረት እንድትጀምር አደረጋት በወቅቱ የሄደችበት የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርት ጥሩ አቀባበል አደረገችላት በዚህም ትምህርት ቤቱን ወደደችው፡፡ ከክፍል በጊዜው በሚፈቅደው የትምህረት ስርአት ሁለት ጊዜ በአገኘችው ውጤት ክፍሎችን በአንድ እርከን ማለፍ ችላለች፡፡በትምህርቷም ጎበዝ ነበረች፡፡ ከስምንተኛ ክፍል ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሊያስገባ የሚችለውን በብሔራዊ ደረጃ የሚሰጠውን ፈተና ጥሩ ውጤት በማምጣቷ ወደ አዲስ አበባ መጣች፡፡ በወቅቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው ከአዲስ አበባ ውጪ በተወሰኑ ጠቅላይ ግዛቶች እንደ ሐረር፣ጎንደር፣ ወሎ ወ.ዘ.ተ ነበር፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በመነን አዳሪ ትምህረት ቤት መከታተል ጀመረች አስራ አንደኛ ክፍል እንደጨረሰችም በማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት ለመከታተል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገባች፡፡ ከሁለት ዓመት በኂላ በዲፕሎማ በማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት ተመርቃለች፡፡ ወደ እንግሊዝ ለንደን በመሄድ ለመኮንንነት (probation officers) የሚያበቃውን ትምህርትና ስልጠና በማጠናቀቅ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች፡፡ በስራ አለም ጥቂት ከአገለገለች በኂላ በድግሪ ትምህርቷን አጠናቃለች፡፡

**የውብ ድንበር /የውብ ድንበር ነጋሽ/**

የውብ ድንበር ነጋሽ ከአባቷ ከአቶ ነጋሽ ኃይለ ማርያም ከወ/ሮ ጥሩነሽ ገላን አላባ ቁልቢ ተወለደች፡፡ እናቷ በተከታታይ አምስት ሴት ልጅ በመውለዳቸው የተነሳ ትዳራቸውን ለመፋታት ደርሰዋል፡፡ ልጆች ተበታትነው በየዘመዱ እና በእንጀራ እናት እና አባት ማደግ ጀመሩ፡፡ የውብ

ድንበር እጣፋንታ እንደ እህቶቿ መቂ በእንጀራ እናት ማደግ ነበር፡፡ እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ እስከ ስድስተኛ ክፍል ብትማርም በቤተሰቡ በተፈጠረ የቦታ ቅያሪ እና የእንጀራ እናቷ ወደ አባታቸው ድሬደዋ መሄድ ስለፈለጉ የውብ ድንበር ትምህርት ሳያስጨንቃቸው ትተዋት ወደ ድሬደዋ ሲሄዱ የውብ ድንበር ዘመድ ጋር በመቀመጥ እስከ ስምንተኛ ክፍል እየተማረች ሳለ ለቤተሰቧ በሚቀርበው የትዳር ጥያቄዎች እና በግሏ ለሚቀርብላት የፍቅር ጥያቄዎች፣ የመፈለግ ስሜት እና ከወጣትነቷ ጋር ተደማሮ ትምህርቷ ላይ ጫና በመፍጠሩ በልጅነቷ ወደ ትዳር አለም ገባች፡፡

## ባለታሪኮቹ የትምህርት ሁኔታ

የተሻለና የበለጠ ነገር ከታወቀ በኂላ አለመሻት ተስፋ የሌለው ድንቁርና ይሆናል፡፡(መስፍን ወልደ ማርያም) ትምህርት ለሰው ልጅ በሕይወትእና በዙሪያ ባለው አለም ላይ ትልቅ ተፅእኖ አለው፡፡እ ንድናድግ እንድንማር አቅማችን በአግባቡ እንድንጠቀም የሚረዳን ነው፡፡ ትምህርት ማግኘት ማለት መመራመር፣ዕወቀት፣ ክህሎትን ልምድና ሞራልን እምነትንና ሳቢ ምግባርን፣መጨበጥ ነው፡፡ በመሆኑም በሴቶች የሕይወት ጉዞ ውስጥ ለትምህርት የነበረው ልምድና አመለከካትን እንመለከታልን፡፡

የፀሀይ ይትባረክ በልጅነቷ ፍላጎቶቿ ካልተሟላ ሰላም የምትሰጥ ልጅ አልነበረችም፡፡ በዚህም ባህሪዋ ሁል ጊዜ ከእናቷ ጋር ብዙም አይስማሙም ነበር፡፡ እናቷ ጥያቄ ሲበዛባት እሷም ለቅሶ ለከት ሳይኖረው ሲቀር ትቆነጥጣት ነበር፡፡ እቤት ውስጥ መስማማት ሲያቅታቸው በአጋጣሚ በመጡት የአክስት ልጅ ነበር ወደ ትምህረት ቤት የገባችው፡፡ ትምህርቷን ከጀመረች በኂላ ግን ብዙም የወላጆቿን ሆነ ከታላላቅ የቤተሰብ አካላት ትምህርትን በተመለከተ የምታገኘው ምንም አይነት ድጋፍ አልነበረም፡፡ የትምህርት ምንነት ምን እንደሆነ ግንዛቤ ባልነበራት እድሜዋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ከአንድ እስከ አምስት ድረስ የትምህርት ውጤቷ ከፍተኛ ስለነበረ የመምህራኖቿን ትኩረት ለመሳብ ችላለች፡፡ ከአንደኛ ክፍል እስከ አምስተኛ ክፍል ስትማርም ባገኘችው ውጤት አንድ እርከን ማለፍ ችላለች፡፡በዚህም ችሎታዋ መምህራኖቿን ማሳመን ችላለች ያላት በትምህርት አልሸነፍ ባህሪ ማሳየት ችላለች፡፡

> በእውነቱ በዚህ በለጋ እድሜ ምንም ጊዜ ቢሆን በትምህርት ተቸግሬ አላውቅም፡፡ አጠናለሁ፣ አነባለሁ፣ የቤት ስራዬን በወቅቱ እሰራለሁኝ፡፡ በክፍል ውስጥም የተማሪዎች ተሳትፎ በሚያስፈልግበት ሁኔታ ሳልፈራ ወደኂላ ሳልል የማውቀውን

ወይም የሚመስለኝን ለመግለጽ ወደኋላ አልልም፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስለኛል፤ ውጤቴ ምንጊዜም ቢሆን ከመጀመሪያ ረድፍ ከሚገኙት መካከል ለመሆን የበቃው፡፡ ከፍተኛ ውጤት በአንድ የትምህርት አይነት ዘጠና ሰባት ቢሆንም የእኔ ከዚያ በላይ ሆኖ ነበር የሚገኘው፡፡ እኔን የሚያበሳጨኝ ሌላ ተማሪ በሁለትና በሶስት ማርክ ሲበልጠኝ ሲሆን ብዙን ጊዜ በክፍሉ ውስጥ አንደኛ ነበር የምወጣው፡፡ (ፀሀይ፣ 24)

ፀሀይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ ደረጃ እና ዩኒቨርስቲ ትምህርቷን በጥሩ ውጤት እንደጨረሰች እንመለከታለን፡፡

በዩኒቨርስቲ በነበረን ቆይታ በአስመዘገብነው ውጤት አንደኛ እና ሁለተኛ ለሆኑ ወጣቶች በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ ሊያሰራቸው የሚያስችል ተጨማሪ እውቀትን የሚገበዩበት እድል ተመቻቸልን፡፡

በተመቻቻላቸው እድልም በሳውዝ ሀምስተን ዩኒቨርስቲ ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት ከመጡ ተማሪዎች ጋር የተማረች ሲሆንም ትምህርቱም የንድፈ ሀሳብና የተግባር በመሆኑ አጥጋቢ ውጤት በማግኘት በመኮንንት ከእንግሊዝ ሀገር ሰርቴፍኬት አግኝታለች፡፡ ፀሀይ በትምህርቷ እና በሥራ በጣም ትጉ ሴት ናት፡፡ይህ ለትምህርት ያላት ፍቅር አስቀጥላ መሄድ ችላለች፡፡

በሳምንት ሁለት ቀን እንዲሁም ቅዳሜ እና እሁድ ቢሮ እየገባሁ መደበኛ ስራዬን እያከናወንኩኝ ቀደም ሲል የተማርኩት ትምህርት በዲግሪ ደረጃ በሀይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ የማህራዊ አገልግሎት ትምህርት በዲግሪ ደረጃ መስጠት ሲጀምር እኔም ከመጀመሪያዎቹ አንዷ በመሆን ትምህርቱን ጀመርኩ፡፡ በዚህም ለሁለት ዓመት የድግሪ ትምህርት ፕሮግራም በማጠናቀቅ ከግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ እጅ በታላቅ ማዕረግ የማኀበራዊ ኑሮ አገልግሎት ባችለር ዲግሪ ተቀበልኩ፡፡ (ፀሐይ፤84)

ከላይ እንደ ተመለከትነው አላማን ለማሳከት የእረፍት ሰአቷን መስዋት በማድረግ አላማዋ ላይ ለመድረስ የምታደርገው ተጋድሎ ከፍተኛ መሆኑን እናያለን፡፡ በዚህ ይህች ሴት የዓላማ ሰው ናት ማለት ነው፡፡

ፀሀይ በተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶች እንደ ዩኒሴፍ ድርጅት ተቀጥራ በምትሰራበት ወቅት በአፍሪካም ሆነ በእስያ ውስጥ ከፍተኛ ትግስት እና ብልሀል የሚጠይቁ ጊዜያትን በጥበብ አሳልፋች፡፡ ለስራው ባላት ጽኑ ፍላጎት ከበላይ በሚደርሳት አድናቆት ብታገኝም በደሞዝ እና በስራዋ ላይ ግን ማደግ አልቻለችም ነበር፡፡ በዚህም ትምህርቷን ከድግሪ ደረጃ ማሳደግ

እንዳለባት በማመን በምትሰራበት መስሪያ ቤት ምክንያቶቿንና ያላትን ልምድ ተጠቅማ እንዲያስተምራት አመለከተች፡፡ ያቀረበችው ማመልከቻ ተቀባይነት አግኝቶ በኒውዮርክ በሚገኘው ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ በጤና አጠባበቅ የማስተር ዲግሪዋን አግኝታለች፡፡

> ሁለቱን ልጆቼን እያስተማርኩና የእናትነት ተግባሬን እያከናወንኩኝ፤ እኔም ተማሪ በመሆን ከነበረብኝ የሕይወት ውጣ ውረድ ጋር ትምህርቴን ከፍ ባለ ውጤት ለመመረቅ በመቻሌ በተለይ በሕይወቴ ላደርገው ከምመኛቸው ዋናው ግብ አደረስኩኝ፡፡ (ፀሐይ፤170)

ከላይ እንደተመለከትነው ፀሐይ አላማዋን ለማሳካት ያጋጠማትን የሕይወት ውጣ ውረዶች፣ ችግሮች እንዲሁም ሴት ከመሆኗ እና በምትሰራበት መስሪያ ቤት ከተሰጣት ኃላፊነት አንፃር የማስተርስ ትምህርቷን በውጭ ሀገር መከታተል አስቸጋሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የዓለማ ለማሳካት ጽናትና እና ጥረት ታክሎበት ያለመችውን ራዕይ ለማሳካት በቅታለች፡፡ ሴቶች ከወንዶች ጥላ ስር ሆነው የቤት ውስጥ ስራ ብቻ ተወስነው ልጆች ማሳደግ ብቻ ዋነኛ ስራቸው በሆነበት ማህበረሰብ ውስጥ በማይለዋወጥ ስዕብና በመያዝ ዓላማን ማሳካት እንደሚቻል አሳይታናለች፡፡ እንደ ዘሪሁን አባባል ሴቶች በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ሴቶች በበታችነት መታየታቸው ተደጋግሞ የሚነገር እውነት ነው፡፡ ወንዶች ጠንካራ፣ አዋቂ፣ አሳቢ፣ ጀግና ሲባሉ ሴቶች ደግሞ አላዋቂ እና የማያስቡ እና ፈሪ ይባላሉ ( ዘሪሁን፣1988፡84) የሚለውን አስተሳሰብ ፀሐይ ግለ ታሪኳን ይህንን እሳቤ ያሸነፈችበት ነው፡፡ ባለታሪኳ ራሷን ብቻ ሳይሆን ያሸነፈችው ሴቶች አይችሉም ከሚለው ማህበረሰብ ያለምንም እርዳታ በትምህርቷ ላይ ባሳየችው ያላሰለሰ ጥረት እና ችሎታ ማሸነፍ ችላለች፡፡ ፀሀይ በተለይ “የሰው ልጅ የእድሉ መሀንዲስ ነው” የሚለው አመለካከቷ በሕይወት ዘመኗ ልትደርስበት ስታልመው የነበረው ህልሟ ላይ መድረስ የቻለች ሴት ናት፡፡

**ትግስት ግርማ/ ትሙት ግድ የለም/**

ትግስት በትምህርቷ ፍቅር ለማግኘት ነበር፡፡ ምንም እንኳን ትግስት የመጀመሪያ ልጅ ሆና የቤተሰብ ፍቅር እያገኘች ያደገች ቢሆንም ወንድሟ መንክር ከተወለደ በኋላ ወላጆቿ ለመንክር የተለየ ፍቅር እና እንክብካቤ ማድረግ ስለጀመሩ ይህ ደግሞ በውስጧ ቅናት ስላደረባት የቤተሰብ ትኩረት ለመሳብ ብዙ ጥፋቶች ብታጠፋ የበለጠ መቆጣት መደብዳብ ሲሆንባት ነበር ፊቷን ወደ ትምህረት ያዞረችው፡፡ በዚህም የቤተሰቦቿን ትኩረትና ፍቅር ማግኘት ችላለች፡፡ አባቴ

በጉብዝናዬ በጣም ተደስቶ ከወትሮ ይልቅ ያቀርበኝና ይንከባከበኝ ጀመር፡፡ በጣም ወደደኝ (ትሙት፣22) በዚህ መንገድ የጀመረችው በትምህርት ውጤታማ መሆን የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በስኬት እንድታጠናቅቅ እረድቷታል፡፡ የኢትዮጵያ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ላይ የሚሰጠውን(ማትሪክ) አለፈች እንዲሁም የተማረችበት ትምህረት ቤት አለማቀፋዊ እውቅና ስላለው የባሎሪያግን ፈተና የሚያስፈትን ሲሆን የባሎሪያግን ፈተና ቀላል አልነበረም ግን እኔ ከሳይንስ ሴክሽን አንደኛ ወጥቼ አለፍኩ፡፡ (29) ትለናለች፡፡ ትግስት የቤተሰብ ትኩረትን እንክብካቤ እና ፍቅር ለማግኘት ብላ ያሰበችውን ትምህርቷን ለቀጣዩ የሕይወት ክፍሏ ያሳረፈው ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡

ወደ ፈረንሳይ ሄዳ ትምርህቷን በምትከታተልበት ጊዜ ብዙ አስቸጋሪ ጊዜያትን አሳልፋለች፡፡ የመጀመሪው ከቤተሰብ ውጭ መሆንና በሀገሪቱ የሚሰጠው የትምህርት ስርአት አመቺ አለመሆን በትምህርቷ ተግዳሮቶች እንዲገጥማት አድርጓል፡፡ ሕክምና የመማር ፍላጎት ቢኖራትም የደረሳት ግን የጥርስ ሀኪም መሆን ነበር፡፡ የጥርስ ህክምናን ትምህርት ደግሞ ፈጽሞ ስለማትወደው በመከራ እስከ ሶስት ወር ድረስ ከተማረች በኋላ መቀጠል አልቻለችም፡፡ እርሷም ይህንን ትምህርት ለመማር ፍላጎት ስላልነበራት ከፈረሳይ ሀገር ወደ አፍሪካ ሴኔጋል በመሄድ በብዙ ውጣ ውረዶች እና ያጋጠማትን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀምም ከዳካር ሴኔጋል ዩኒቨርስቲ የሜዲካል ዶክትሬት ተመረቀች ብዙም ሳትቆይ በዚሁ ዩኒቨርስቲ የተላላፊ በሽታ ስፔሻሊስት አደረገች፡፡ የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት ከገባች በኋላ በተለያዩ የአፍሪካ አገራት በመስራት ባገኘችው አጋጣሚ በትምህቷን እያሳደገች በባክቴሪዮሎጂ ቫይሮሎጂ ዲግሪ፣የሌፐሮሎጂ ዲፕሎማ ኤፒዴሚሎጂ ዲፕሎማ ከጆን ሆፐኪንስ ዩኒቨርስቲ አሜሪካ አግኝታለች፡፡ በዚህም ስራዎቿ ላይ ተጽዕኖ አሳዳሪ ሴት መሆን ችላለች፡፡

**የውብ ድንበር**

የውብ ድንበር ቤተሰቦቿ በልጅነቷ ስለተለያዩ (ስለተፋቱ) አስተዳደጓ ሐላፊነት የሚወስድ አካል ስላነበረ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷ በውጤቷ መካከለኛ ደረጃ የምትመደብ ተማሪ የነበረች ሲሆን የቤተሰብ አለመስማማት እና በወቅቱ በሀገሪቱ ላይ የነበረው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምክንያት በልጅነቷ ወደ ስራው እና ወደ ትዳር ገብታለች፡፡ ነገር ግን አስረኛ ክፍል እያለች ብታረግዝም አስራ አንደኛ ክፍል ወልዳ ትምህርት ሳታቋርጥ አስራ ሁለተኛ ክፍል ማትሪክን መፈተን ችላለች፡፡ ውጤቱ ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡ ከአንድ ትምህርት በስተቀር ውጤት አልመጣም ነበር፡፡ ጊዜው በሚፈቅደው መሰረት ድጋሚ እየተፈተነች ውጤት ማጠራቀም

ጀመረች፡፡የትምህርት ፍላጎት ስለነበራት በማታው የትምህረት ክፍል በመመዝገብ አያያዝና ሥራ አመራር በሰርተፍኬት ተመረቀች፡፡ የውብ ድንበር ጋውን መልበስ ዓላማዋ ስለነበረ ሰርተፍኬቷን ካገኘች በኋላ ከሰላሳ ዓመት በኋላ በአካውቲግ ዲግሪዋን ይዛለች፡፡

እነዚህ ሴቶች በትምህርት ራሳቸውን ለመለወጥ ያደረጉትን ተጋድሎ ከቤተሰብ፣ከማህብረሰብ እንመለከታለን፡፡ ተክለ ሐዋርያ ተክለ ማርያም የሰው መበላለጥ የመጣው በመመራመር ልዩነት ነው፡፡ ይላሉ እንዲሁም ታላቁ የነጻነት ተጋዳይ ኔልሰን ማንዴላ ትምህርትን በተመለከተ ሲናገሩ ትምህርት ራስን ለማሻሻል ትልቁ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው፡፡ የአንድን አርሶአደር ልጅ ዶክተር የምትሆነው፣የማእድን ቆፋሪ ልጅ የማእድን ማውጫው አለቃ የሚሆነው፤የግብርና ሰራተኞች ልጅ የአገር መሪ የሚሆነው በሚሰጠው ሳይሆን ካለን ባገኘነው ነው፡፡ ይላሉ በግለ ታሪኮቹ ሴቶች በትምህርቱ ዓለም በራሳቸው ጥረት ስንመለከት የፀሀይ በተፈጥሮ ያገኘችውን ብሩህ አእምሮ ከሯሳ ትጋት ጋር በመጨመር የህይወቷን አቅጣጫ ስትቀይር እንመለከታለን፡፡ በሕይወት ጎዳና ውስጥ ያገኘቻቸው መልካም አጋጣሚዎች በትምህርት ምክንያት መሆኑን እናያለን፡፡ ትግስት በልጅነቷም የቤተሰብ እንክብካቤ የነበራት እና ወላጆቿ ለትምህረት ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ ስለነበረ ያጋጠማትን መልካም እድል እና የራሷ ጥረት ተጨምሮበት አሳክታለች፡፡ የውብ ድንበር ገና ከጅምሩ አባቷ ለሴት ልጅ ባላቸው አመለካካት እና በአስተዳደግ ችግር ምክንያት በትምህርቷ ተወዳዳሪ ሆና መውጣት ሲያቅታት እናያለን፡፡ ነገር ግን የትምህርትን ዓለም ከተወች ከሰላሳ ዓመት በኋላም ተምሮ ጋውን ለብሶ መመረቅ ሕልሟን አሳክታለች፡፡ ሴቶቹን ስንመለከት መድረስ የሚፈልጉት ቦታ ላይ መድረስ ችለዋል፡፡ የዓላማ ጽናት ይታይባዋል፡፡

### 3.2. የግለ ታሪኮቹ የትዳር ሕይወት ሁኔታ

ትዳር ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም መመስረቻ እና ዋና ማኀበራዊ ክንዋኔ ነው፡፡ በዝምድና ላይ ያልተመሰረተ የጋራ ኑሮ በጋብቻ ይጀመርና ወደ ቤተሰብ ምስረታ ያድጋል፡፡ የትዳር አጋር፣ውሃ አጣጭ የሕይወት አጋር፣አሚን የሚሉት የሁለቱን ሰዎች በሕይወት መጣመር የሚገልፁትን ጋብቻ የሕይወት ፍላጎቶች ለማሟላት የሚደረግ ማኀበራዊ ክንዋኔ መሆኑን ነው፡፡ ለኑሮ ትግል እያለፍን ፍላጎታችንን አሟልተን በደስታ ስንኖር መልካም ሕይወት መራን እንላለን፡፡ በተለይ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የትዳር አመለካካት ሴቶች በአብዛኛው በስሜት የሚገዙ በቡድን የምታስብ ስሜቷንና ብልሀቷን ትዳር ላይ የምታውል ጭንቀትና ድብርት በቀላሉ የሚያጠቃት በአንድ ወንድ መወሰን የምትደሰት ሞቅ ያለ አየር ጠባይ የምትመርጥ፤ማንበብና ማዳመጥ የምትሻ፤መወራጨት የማትወድ፤ አድማጭ የሆነች

አስተዋይነት የተላበሰችና ሰውነቷ በስብ ደንደን ያለች ናት፡፡ በወንዱ በኩል ደግሞ ጠለቅ ባለ አስተሳሰብ ብሱ አመክዮና የሚሄድና ሁሉን ነገር በምክንያታዊነት ማየት የሚወድ፤ብዙ የማይሞቀውና የማይበርደው ሁል ጊዜም በማነበረሰቡ ዘንድ የወንድነት መገለጫዎችን ለማስጠበቅ ራሱን መስዕዋት ከማድረግ የማይመለስ፤ሰውነቱ በጡንቻ ደልደል ያለ ነገሮችን አቀናጅቶ በመሄድ ለመከወን የሚጥር እና ለትዳር ጓደኝነት የሚፈልጋት ከራሱ እድሜ ያነሰች እንድትሆን ትልቅ መሻት ያለው ነው፡፡ (እናት፤356) የባለ ታሪኮቹ የትዳር ሕይወታቸው ስናይ የውብ ድንበር በአስራዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነበር፡፡ ከብዙአየሁ ጋር የፍቅር ግንኙነት ትጀምራለች፡፡ ይህ የፍቅር ግንኙነት እርግዝና ሲመጣ ልጅ መውለድ ቻሉ፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ልጃቸው ሶስት አመት ሲሞላት ሻማ ያዢ አድርገው በሰርግ ተጋቡ፡፡ ይህ ሲሆን ሃያ አመት አልሞላትም ነበር፡፡ ሁለቱም በጣም የሚዋደዱ ሲሆን ጥሩ የፍቅርና የመተሳሰብ ሕይወት ያሳልፉ ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙአየሁ አንድ መጥፎ አመል አለበት፡፡ በትዳር አጋሯ ግን ከሌሎች ሴቶች ጋር የዝሙት ፍላጎት ነበረው፡፡ የዝሙት ፍላጎቱ ከመጋባታቸው በፊት ፍንጭ ቢኖራት ጋብቻውን ልተትወው አስባ ከጋብቻ በፊት በመውለዷ ወላጆቿን በተከበሩበት ሀገር ዲቃላ ወልዳ ስማቸውን በክፉ ላለማስነሳትና በተለይ እርሷን ለጋብቻ የሚፈልጓት ብዙ ሰዎች ስለነበሩ በእነርሱ ዘንድ የሚደርስባትን እፍረት እና መሸማቀቅ መጋፈጥ ስላልቻለች ይለወጣል በሚል እሳቤ ወደ ትዳር ገብታለች፡፡ ከጋብቻ በኃላ ግን እንዳሰበችው ሊያርፍ አልቻለም፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱ መካካል ጥል እና ጭቅጭቅ መፍጠር ተጀመረ እየባሰ ሄዶ በትዳራቸው ውስጥ ሽማግሌዎች እየገቡ ያስታርቋቸው ጀመር፡፡ ነገር ግን ብዙአየሁ ከስህተቱ ሊማር አልፈለግም ተመልሶ ተመልሶ እዛው ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ የውብ ድንብርም ይህ ነገር መስተካካል ስላልቻለ ከትዳር ልትፋታ ወሰነች፡፡ በብዙ ሽምግልና ትዳሩ ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ ስራዋን ወደ አዲስ አበባ እንዲቀየር ካደረገች በኃላ ልጇን ለእናቷ ሰጥታ ትዳሯን ፈታች፡፡ አሰላን ለቃ አዲስ አበባ ስራዋን ጀመረች፡፡ ነገር ግን ብዙአየሁ ባለስልጣን ስለነበረ የፍቺስነ ስርአቱ በቀላሉ የተከናወነ አልነበረም፡፡ የመጀመሪያ ትዳሯን ስትፈታ ሃያ ሶስት ዓመቷ ነበር፡፡

የመጀመሪያ ትዳሯ ከፈረሰ በኋላ ሁለተኛ ትዳር መስርታለች፡፡ የትዳር አጋር የሆናት በልጅነቷ ቤታቸውን ተከራይተው የፍቅር ጥያቄ ያቀርብላት የነበረው ብሩክ ከውጭ አገር ተምሮ ሲመለስ አድራሻዋን አፈላልጎ አገኛት ግንኙነታቸው ወደ ትዳር ተቀይሮ አንድ ልጅ ማፍራት ችለዋል፡፡ የውብ ድንበርና ብሩክ ከተጋቡ በኋላ ለአስር አመት አብረው ቆይተዋል፡፡ በእነዚህ አመታት ውስጥም ተጣልተው እንደገና ታርቀው መኖር ጀምረው ነበር፡፡ ነገር ግን የውብ ድንበር የዲፕሎማ ትምህርቷን ለማሳደግ ትምህርት በጀመረችበት ጊዜ በተፈጠረ ክፍተት ብሩክ ፊቱን

ወደ ሌሎች ሴቶች ማዞር ጀመረ፡፡ በትዳሩ ላይ መማገጥ(ዝሙት) መፈፀም ጀመረ ይህንን ስህተት ማለፍ የማትችለዋ የውብ ድንበር አማራጭ ያደረገችው ፍቺ ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ሁለተኛዋን ትዳሯን ልትፈታ ችላለች፡፡

*ዶ/ር ትግስት ግርማ*

ትግስት የሕክምና ትምህርቷን በምትከታተልበት በሴኔጋል ውስጥ አብራው ከምትማረው የብሩንዲ ዜግነት ካለው ሰው ጋር ትዳር መሰረተች፡፡ሁለቱም የሕክምና ተማሪዎች ሲሆኑ በሕክምናቸው ስፔሻሊስት አድርገዋል፡፡ የትግስት በትምህርት ቤት ቆይታዋ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ስለነበራት ለትዳር ያላት አመለካከት የተለየ ነበር፡፡ ጋብቻ ሶሻል ኮንትራት ነው፡፡ከተዋደዱ አብረው መኖር ፍቅር ከሌለ ደግሞ ጥሎ መሄድ ነበር አስተሳሳቧ፡፡የመጀመሪያ ልጇን ስትወልድ ግን ሀሳቧ ተቀየረ፡፡ በዚህም ከአደለ ሒትማን ጋር ትዳር መሰረተች፡፡ ሁለቱም የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ለመሆን እቅድ ስለነበራቸው ይህንን ለማሳካት ከኢትዮጵያ ይልቅ ቡሩንዲ ሄዱ ምክንያቱም ትምህርቱ በፈረንሳይኛ ስለሚሰጥ፡፡ እንዳሰቡትም በዩኒቨርስቲ ውስጥ ስራ ሲያመለክቱ እርሱ የአገሩ ተወላጅ በመሆኑ ተቀበሉት እርሷን ግን የውጭ ተወላጅ ነች በማለት በአስተማሪነት ሊቀጥራት አልቻሉም፡፡ በዚህም የፕሮፌሰርነት ሕልማን ጨልሟል፡፡ በሕክምና በአንድ ሆስፒታል ተቀጥራ ሥራዋን ጀመረች፡፡ የብሩንዲ ማህበረሰብ ወንዶች በሙሉ ማታ እየተገናኙ ቢራ መጠጣት ነው ሥራቸው፤ ሴቶቹም በበኩላቸው እርስበርስ እየተገናኙ ያንኑ ቢራ መለጋት በመሃላቸው ልጆቿቸው ብቻቸውን ይጫጫሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በየቤቱ እየዞሩ ስለባሎቻቸው ማውራት ነው ሥራቸው፡፡ በዚህም እየቆየ ባለቤቷ የሀገሩን ባህል መሰረት ከጓደኞቹ ጋር እያመሸ መጠጣት እና ማምሸት ሲጀምር በመካከላቸው አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ በሁለቱ መካካል መደባደብና ፀብ መፈጠር ሲጀምር ትዳሯ እንዳበቃለት ተረዳች፡፡ሁለት ልጆቿን ይዛ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ብታስብም ሳይሳካላት ቀረ ብቻዋን ወደ ሀገሯ ተመለሰች፡፡ በዓለም ጤና ድርጅት ውስጥ ሥራ ካገኘች በኋላ ከባለቤቷ ጋር ያለው ግጭት በመፍታት ልጆቿን ወደ ራሷ አድርጋ ኑሮዋን በኮንጎ አደረገች፡፡ በዚህም ባለቤቷ በማይድን በሽታ በመያዙ እና ባደረገው ስራ በመፀፀቱ ታርቀው ልጆቹን እየመጣ እንዲጠይቅ እድል ሰጥታዋለች፡፡ በታመም ጊዜ አስታማ ሲሞት ሬሳውን ይዛ ወደ ብሩንዲ በመሄድ በክብር እንዲቀበር አድርጋለች፡፡ትግስት ከመጀመሪያ ትዳሯ ውጪ ሌላ ትዳር አልመሰረተችም፡፡ ከአገር አገር በመዞር ሙሉ ትኩረቷን በስራዋና ልጆቿን በማድረግ ልጆቿን ለወግ ማእረግ አብቅታለች፡፡

**ፀሀይ ይትባረክ/ የፀሐይ ጉዞ/**

ፀሐይ የትዳር አጋሯ ጋር የተገናኙት በዩኒቨርስቲ የዲፕሎማ ተማሪ በነበረችበት ጊዜ ነበር። ከተፈራ ወልደ ቂርቂስ የተዋወቀችው። ይህ በሁለቱ ፍቅረኛሞች የተጀመረው ግንኙነት ወደ ትዳር ሲሸጋገር በወቅቱ ፀሐይ ባላት የትምህርት ደረጃ እና ከወደፊት የሚያጋጥማት የስራ ድርሻ ለማግባት ከመረጠችው ሰው ይልቅ በስልጣንም ሆነ በገንዘብ የበለጠ ሰው ማግባትና ተደላዳለ ኑሮ መምራት ምርጫዋን እንድታስተካክል ቢመክሯትም ለትዳር መሰረቱ በሁለት ሰው መካካል ያለው ፍቅር ነው በሚለው አቋሟ ተፈራን ልታገባ ችላለች። በትዳር ሕይወታቸው አራት ልጆችን ማፋራት ችለዋል። በትዳር ሕይወታቸው ለአርባ ሰባት ዓመት የቆዩ ሲሆን ኑሮቸአውን በፍቅርና በመተሳሰብ ለመምራት ችለዋል። በሁለቱ መካከል በተለይ በልጆች አስተዳደግ ላይ ልዩነት ነበራቸው። ተፈራ የልጆች ባህሪ መቅረጽ ለማስተካካል የሚፈልገው በቅጣት ሲሆን ፀሐይ ደግሞ ልጆችን በቅርብ በማነጋጋር በመምከር እንደሆነ ቅጣት የመጨረሻ አማራጭ ማድረግ ሲሆን ሌላው ልዩነትታቸው ደግሞ የሚከተሉት የስራ ባህል ነው ባል ንግድ ይወዳል። ሚስት ደግሞ ገንዘብ ብቻ ሰውን አያኖርም በሚል አመለካከት ቢኖራቸውም ይህንን ልዩነታውን አቻችለው በትዳር ይኖራሉ። ፀሀይ ካላት የስራ ኃላፊነት እና ከሀገር ውጪ በምታደርገው ጉዞዎች በቤት ውስጥ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ልጅን ማሳደግ መንከባከብ ወ.ዘ.ተ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በመስተሳሰብ እና በመከባበር ማሳለፍ እንደሚቻል የታየበት የባለ ታሪካችን በእምነቷ በውስጣዊ ጥንካሬዋን እንመለከታለን።

አጠቃላይ በግለ ታሪኮቹ ሴቶቹንስንመለከት የራሳቸው የሆነ አስተሳሰብ፣አመለካካት፣ ፍላጎትና ርዕዮት አላቸው። የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሚፍጨረጨሩ ናቸው። በዚህ ውስጥ ደግሞ አንድም ጊዜ በብርና በተለየየ ጊዜ ጥቅማጥቅሞች አልተደለሉም። ነገር ግን የየራሳቸው እንዲሟላላቸው የሚፈልጉት ነገር አለ። የውብ ድንበርን ስንመለከት ከአንድ ሁለት ትዷሯን የፈታች ሲሆን ምክንያቷ ደግሞ ወንዶቹ ለትዳራቸው ታማኝ ባለመሆናቸው ተፋታለች። የመጀመሪያ ባሏ በወቅቱ ባለስልጣንና ሀብትና ንብረት ያለው ሲሆን ሁለተኛውን በተመሳሳይ የራሱ ክሊኒክ እና ሀብትና ንብረት ያለው ቢሆንም ለትዳር ታማኝ መሆን እና ታማኝነት ይልቃል ብላ ሀብታምነት ይቅርብኝ መኪናም ፎቅም ባለድርጀት መሆንም ይቅርብኝ ብላበራሳ ፍላጎት መለያየትን መርጣለች። ከትግስት ከባህል ልዩነት በተለይ ትዳር ሲመሰረት አንዲት ሴት ከሀገሯ ሰው ውጭ ካገባች ባሏን ብትወድም ሀገሩን ባህሉን ሳታውቅ የትውልድ ሀገሩ መሄድ እንደሌለባት ነው። እንዲህ አይነት ጋብቻ ብዙ ጊዜ የሚሰራው የሁለቱ ባልሆነ ሀገር ሲኖሩ

ነው። ፀሀይ የትዳር መሰረቱ የሁለቱ ተጋቢዎች ግላዊ መስማማት እንጂ በሀብትና ንብረት አይደለም በሚል አመለካካቷ በትዳራ ረጅም እድሜ አስቆጥራለች።

እነዚህ ሴቶችን ስንመለከት የሚያፈቅር ልብ አላቸው ነገር ግን ከመጡበት ማህበረሰብ አንፃር ያላቸው ባህሪ በትዳራቸው ላይ ተንፀባርቋል። የውብ ድንበር ገና ብዙም በአእምሮም ሆነ በስነ ልቦና ባልጠነከረችበት አመት ትዳር የመሰረተች። የመጀመሪያዋን ትዳሯን የተመሰረተውም ከፈረሱ ጋሪው ቀድሞባት ነው። ጋብቻ ከመፈፀሟ በፊት ልጅ መጣ። ለቤተሰቦቿ እና ለራሷ ክብር ላለማሳጣት ስትል ምክንያቱም በኢትዮጵያ ባህል መሰረት ሴት ልጅ ከትዳር በፊት ልጅ ከወለደች ዲቃላ አመጣች እንጂ እንደ ልጅ አለመቀበል ይታያል ይህ ክስተት በቤተሰብ እና በዘመድ አዝማድ ቅራኔን ሲመጣ በማህረሰቡ ደግሞ ለቤተሰቦቿ የሚሰጠው አመለካከት ይቀንሳል። ሌላው የውብ ድንበር ከሰባተኛ ክፍል ጀምራ በወንዶች ዘንድ ተፈቃሪ እንዲሁም ልጃችሁን ለልጃችን የሚሉ ብዙ ስለነበረ እንዲህ አይነት የሕይወት ውድቀት ሆና ነበር በትዳሩ ላይ እንደሚማግጥ እያወቀች አስተካክለዋለሁ ብላ አገባችው። ከመጀመሪያው ስህተት ስታገባው የበለጠ ተሳሳተች። ነገር ግን ሁለቱን ስህተት ተቀብላ መኖር አልቻለችም። ስልጣኑ እና ሀብቱን ትታ ለሕሊናዋ አደረች። ፀሐይን ከመጣችበት የህይወት ተሞክሮ በተለይ በአዳሪ ትምህርት ቤት እና በማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት ክፍል ያገኘችው እውቀት በትዳር ሕይወቷ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር። ፀሐይ አፍቃሪ ልብ ያላት ከቁሳዊ ይልቅ አስተሳሳብ ላይ የምታተኩር። ለሀብትና ለንብረት ሳይሆን እውነትን የምትወድ፣የሰው ስሜት የምትረዳ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች እና ለነገ ብላ የምትጨነቅ ለቤተሰቧ ከፍትኛ መስዋትነት የምትከፍል በስሜት ሳይሆን በእቅድ የምትመራ የራሷን ማንነት ጠንቅቃ የምታውቅ ሴት ናት።ትግስት ትዳር በሚል ነገር መጠመድ የማትፈልግ ፍቅር ካለ አብሮ መኖር ካለቀ ደግሞ መለያየት በሚል እምትነት ውስጥ ሆና ልጇን እርጉዝ ስትሆን ይህንን አስተሳሰብ በመተው ወደ ትዳር የገባች ብትሆንም። ለትዳሯ ባሏን የምትወድ ታማኝ ብትሆንም ከባህሏ ውጭ ያለውን የማህረሰቡን በሴቶች ላይ ያለውን ዝቅተኛ አስተሳሰብ እና ባሏም ለትዳር ያለውን ሀላፊነት የማይወስድ መሆኑን ስታውቅ የራሷን ውሳኔ መወሰን የቻለች ናት። በትዳር ሕይወታቸው ለተፈጠሩ ልጆች ግን ለወደፊት ሕይወታቸውም ሆነ ለስነ ልቦናቸው በመጠንቀቅ የአባትና የእናት ፍቅር ሳያጡ እንዲያድጉ ያደረገች ሴት ናት።

ሶስቱም ሴቶች ግለ ታሪክ የምናስታውለው ነገር ላመኑበት የትዳር ሕይወት የሚያስከፍለውን መስዋትነት በመክፈል ለመኖር ሲጥሩ እናያለን። በሚያራምዱት የሕይወት አመለካካት፣

አስተሳሰብ የህይወት መርህ ውጤቱ መልካም ሆነ መጥፎ ያመኑነትን ሲኖሩ ይታያል፡፡ የዓላማ ሴት መሆናቸውን እንመለከታልን፡፡

**ተመሳስሎ**

ስራና ስኬት፡- የግለሰቦቹ ሙያዊ ጉዞዎች እና ስኬቶች የሕይወት ታሪኮችን ይዘረዝራሉ፡፡ የሴት የሕይወት ታሪክ ማነፃፀር በሙያ ምርጫ፣ያጋጠሙ መሰናክሎች እና በፆታ ላይ የተመሰረተ የስኬት ግንዛቤን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡

## 3.3. ማህበራዊ ተሳትፎ እስከ ሙያዊ አበርክቶ

**ፀሐይ ይትባረክ**

የፀሀይን ግለ ታሪክ ስንመለከት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሌለበት ማህረሰቡ ሆነ ቤተሰቦቿ ለሴት ልጅ ትምህርት ትኩረት ከማይሰጥበት አካባቢ የተገኘች ናት፡፡ ነገር ግን በትምህርቷ ትኩረት በመስጠት እንደ እህቷ በልጅነቷ አግብቶ ልጅ ከመውለድ ራሳን ነፃ አድርጋ ላሰበችው አላማ መምህሮቿ እንደ ሚሲት ለሀገርየራሷን የሆነ የሙያ አበርክቶ አድርጋለች፡፡

ፀሀይ በጠባይ ማረሚያ አስተዳዳሪ ሆና ስትመደብ ከተሰጣት የስራ ድርሻ ያለፈ ስራ መስራት ችላለች፡፡ በእንግሊዝ አገር ስለ ወጣት አጥፊዎች አሰራር በተማረችውን ትምህርት መሰረት አመለካካታቸውና ክህሎታቸውን ለመጨመር ከስራ ባላደረባዋ ጋር በመሆን የተሰሩት ስራ በመምህራን እና በተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት መሻሻል አሳይቷል፡፡

**ጉልህ የሙያ ጉዞዎች**፡ በጡረተኛ፣ የበጎ ፈቃደኝነት ሥራዎች  የዩኒሴፍ አግልግሎት ኢትዮጵያ ከፍተኛ ፕሮግራም መኮንን የዩኒሴፍ ተጠሪ -ፓውፓ ኒው የክልላዊ የመሰረታዊ አገልግሎት ጥምረት ኡጋንዳ የእስያ ክልላዊ ድጋፍ ፕሮግራሞች ኒውዮርክ፣በኒዎርክ የሥርአተ ጾታ ከፍተኛ አማካሪ፤የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማህበር አንደኛ የሥራ አፈጻፀም ዳሬክተር፤ በኢትዮጵያ የወጣት ሴቶች ክርስቲያን ማህበር አንደኛ የስራ አፈፃፀም ዳሬክተር፤የሰራተኞች ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር፣የማህበራዊ አገልግሎት ክፍል ምክትል ኃላፊ፣የተማሪዎች መኮንን እና የወጣት አጥፊዎች ማረምና ሥልጠና ማዕከል ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ፀሐይ ከስራ ኃላፊነት ሌላ በተለያዩ የቦርድ አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማህበር የቦርድ ፕሬዝዳንት ወሴክማ የኢትዮጵያ የቦርድ ፕሬዝዳት በኢትዮጳያ

የቀድሞ ዓለም አቀፍ የመንግስት ሠራተኞች ማህበር የቦርድ አባል እና በሌሎች በርካታ ተሳትፎ በማድረግ አገሯን አገልግላለች፡፡ ለዚህም አገልግሎታቸው ከተለያዩ ድርጅቶች ክብርና ሽልማት ማግኘት ችለዋል፡፡ ከዩኒሴፍ ምስጋና፤በኒዩርክ የምስጋና ሰርተፍኬት፤ዓለም አቀፍ ፕላንድ ፓረንትሁድ ፌደሬሽን ስዊዘርላንድ፣ከኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማህበር እውቅና ኢትዮጵያ፤ኦነሪግ ዎርልድ ውመን፣የዓለም ወሴክማ ሽልማቶችና አግኝተዋል፡፡

ፀሀይ ወደ ሀገሯ ከተመለሰች በኃላ ከቀድሞ ትሰራበት የነበረውን ወሴክማ እንደገና ኢትዮጵያ እንዲቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ በቤተሰብ መምሪያ ማኀበርና በወሴክማ ፕሬዝዳትነትም የተቻላትን ያህል አገልግላለች፡፡

## ዶ/ር ትግስት ግርማ

ትግስት ግርማ በኢትዮጵያ የኑሮ ስሌት መሰረት በኢኮኖሚያቸው ከፍ ካሉ ቤተሰብ የተወለደች ናት፡፡ በዚህም በልጅነቷ ትምህርት የማግኘትና ውጤታማ እንድትሆን የአባቷ እርዳታ የምታገኝ ናት፡፡የተማረችበት ትምህርት ቤት በወቅቱ በሀገሪቱ ከነበሩት ትምህርት ቤቶች አንደኛ ነበር፡፡ ትግስት የራሷ ጥረት፣የአባቷ ልፋት እና መምህራኖቿ ድጋፍ ተደማምሮ በትምህርቷ ውጤታማ ነበረች፡፡ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ከአጠናነቀች በኃላ ፈረንሳይ ሀገር ለትምህረት በመሄድ የሕክምና ትምህርቷን ለመከታተል ነበር፡፡ ሆኖም ያገኘችው እድል የጥርስ ሀኪም በመሆኑ ያለ ፍላጎቷ ለመማር ብትሞክርም ትግል ስለ ሆነባት ወደ አፍሪካ አህጉር ዳካር በመመለስ ትምህርቷን መከታተልና እና መጨረስ ችላለች፡፡ ትግስት ከዳካር ሴኔጋል ዩኒቨርስቲ የሜዲካል ዶክትሬት፣የተላላፊ በሽታ ስፔሻሊስት አድርጋለች፡፡ የባክቴሪዮሎጂ ቫይሮሎጂ ዲግሪ፣የሌፕሮሎጂ ዲፕሎማ ኤፒዴሚሎጂ ዲፕሎማ ከጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርስቲ አሜሪካ አግኝታለች፡፡

**ጉልህ የሙያ ኀዞዎች**በኮንጎ ብራዛቪል በአለም ጤና ድርጅት ውስጥ የኤድስ ቡድን መሪ በመሆን አገልግላለች፡፡ በቦትስዋና የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ልዩ ተጠሪ በመሆን አገልግላለች፣ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በተባበሩት መንግስታ የአፍሪካ ልዩ ተጠሪ፣ የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ኤች. አይ ቪኤድስ ምክትል ዳይሬክተር፣ የአምሬፍ ዳይሬክተር ጅነራል፤የሮያል ፌሎው ኦፍ ፊዚሻንስ፤ ለእናቶች ለህጻናት ሕይወት ማዳኛ የተባበሩት መንግስታት ኮሚሽነር በመሆን አገለግላለች፡፡ በዚህም ስራዋ የፈረንሳይ መንግስት ከፍተኛ ሜዳሊያ ተሸላሚ፣ ሆነች እንዲሁም በቦትስዋና በኤች.አይ.ቪ. ላይ በተመለከተ ከፕሬዝዳቱ ጋር ያደረገችው ተጋድሎ ቀላል

አልነበረም። በመጀመሪያ ፖለቲካው ይበላሻል ብለው ቢያስቡ እና ስራዋን በንቀት ቢመለከቱም በስተመጨረሻው ግን ባላት ጽናት እና ችሎታ ተመራጭና ተመስጋኝ አድርጓታል።

> እኔም በዚህ ስራዬ ብዙ ምስጋና ከቦትስዋና መንግስት አገኘሁ። አንዳንዴ ቁጭ ብዬ ሳስበው በዛ ሁሉ ንቀት የጀመረው ሥራዬ በብዙ ምስጋና አክብሮት መገባደዱ ግርም ይለኛል። (ትሙት፣122)

> የቦትስዋና ሽኝት አስገራሚ ነበር። እንደዛ መጀመሪያ ላይ እንዳልናቁ በመጨረሻ በጣም ተሰምቷቸው የሀገራችን ሕዝብ ሕይወት ባንቺ አነሳሽነት ነው። የተረፈው ብለው ብዙ ሽልማትና ብዙ ንግግር በጤና ጥበቃና በውጭ ጉዳይ ሚኒስተሮች አዘጋጅነት አደረጉልኝ። በሽኝቱም ላይም አንድ ወዳጄ ሰው ይህንን ዓይነት ምስጋና ሰው የሚያገኘው ሲሞት ነው። አንቺ ግን በሕይወት ይኸንን አገኘሽ ያለኝ በአንጎሌ ውስጥ ተቀርጾ ይኖራል።(ትሙት፣125)

የትግስት ኒዮርክ ከተመለሰች በኃላ ኑሮ በብቸኝነት እና ራስ ወዳድነት እና ገንዘብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እና የበለጠ ደግሞ እልም ያለ ፖለቲካ መሆኑ ሥራው ብዙም አልወደደችም ነበር። ነገር ግን ለአፍሪካ ከተሰጣት ኃላፊነት ሌላ በራሷ ተናሳሽነት በአሜሪካ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ጤና የሚያሳይ ኤግዚብሽን በማዘጋጀት በአሜሪካውያን ስለ አፍሪካ ያላቸውን አመለካከት ለመቀየር፣ በኒዮርክ በሚገኘው ትልቁ የባቡር ጣቢያ ውስጥ የአፍሪካ ቀኖችን በሚል ስያሜ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የግብረ ሰናይ ድርጅቶች ስራቸውን የሚሳዩበት ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት፣ እና ለአንድ ገጠር ውስጥ ስትወለድ የሚስፈልጓትን ቁሳቁስ የያዘ ኪት መግዢያ ብር በማሰባሰብ ወደ አፍሪካ ልካለች። በተላከው ገንዘብ በገጠር የሚገኙ የብዙ ሴት ሕይወት ማዳን ተችሏል። በዚህም ብዙዎችን መታደግ ችላለች። ትግስት በተለይ በአፍሪካ አገራት ኤች፣አይ.ቪ መኖሩ ባልታወቀ ጊዜ ትግስት ባላት የሕክምና እውቀትና ልምድ እንዲሁም በሰራችበት ሀገራችን ካሉ መሪዎች ጋር ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ የብዙ ሰዎች ሕይወት ያለ አግባብ እንዳይቀጠፍ አድርጋለች።

ትግስት ከስራ ኃላፊነት ሌላ በተለያዩ የቦርድ አባል በመሆን አገልግላለች። በሮታሪ ክለብ አባልና የፓል ሐሪስ ፌሎው በመሆንና በካናዳ የሚገኘው የማጊል ዩኒቨርስቲ የቦርድ አባል በመሆን አገልግላለች። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች በኃላ የጤና ኮሌጅ በመክፈት የእናቶች ሞትን ለመታደግ አላማው አድርጎ የገጠር ሴቶችን በማስመጣት በሚድ ዋይፍነት አስመርቆ ተመልሰው ሄደው እህቶቻቸውን እንዲረዱ ማድረግ ነው።

**የውብ ድንበር**

የውብ ድንበር እስከ ስምተኛ ክፍል ድረስ የነበራት የትምህርት ተሳትፎ እኔም ከትምህረት ስመለስ ከምሳ በኋላ ተኝቼ ሌሊት በማጥናት ለደረጃ ባላልፍም መካከለኛ ባሉ ደረጃዎች የማልፍ ተማሪ ነበርኩ፡፡(የውብ ድንበር፤ 54) የቤተሰብ ድጋፍና በተለይ በአፍላ እድሜዋ በቤተሰብ ቁጥጥርና ድጋፍ አለማግኘት በራሷ ሕይወት ላይ የተከሰተውን ክስተት በመቋቋም በስራ ላይ ለማሳየት በቤትእርዳትነት በተለምዶ የቤት ሰራተኛዋን በመደበኛ ትምህርት እንድትማር በማድረግ ራሷን እንድትችል እንድትወስን አድርጋታለች፡፡ በተለይ በሀገራችን ለቤት ሰራተኞች የሚሰጠውን አመለከካከት ለመቅረፍ ሀሳብ ከመስጠት ይልቅ ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ይህንን አስመልቶ ዶክተር ይሁኔ እናት በሚለው መጽሀፋቸው ላይ ሴትን ጨቋኝ ሴቶች በሚል ንኡስ ርዕስ ስር ስለ ቤት ሰራተኝነት ሲገልፁ

ችግሩ ከፖለቲካ መዋቅሩ በቀጥታ ወደ ቤተሰባዊነት መዋቅር ይወርዳል፡፡ ለምሳሌ በአገራችን ካለው የሥራ ክፍፍል አድካሚውን ውሃ መቅዳት እንውሰድ፡፡ ውሃ ከሚቀዱት ባባዛኛው እናቶችና ሴት ልጆች ናቸው፡፡ ከ15 በታች ያሉትን ሕፃናት ብንወስድ ውሃ የሚቀዱ ሴት ልጆች ከሦስት እጥፍ በላይ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በቤት ሠራተኝነት ያለውን ስምሪት ብንወስድ የጉልበትና የመብት እጅ በቀጥታ እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቤት ሠራተኞች እና እመቤቶች መካካል ያለው አለመግባባት የጭቆናው ዋና ምንጭ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ጭቆናው አካላዊ ጥቃትን ጨምሮ ከምግብ ክልከላ እስከ ሥራ ጫና እንደሚደርስም ይታወቃል፡፡ ለስራ ያልደረሱ ምስኪን ሴት ልጆችን ጉልበት ተመጣጣኝ ባልሆነ ክፍያ መበዝበዝ የተለመደ ነው፡፡ በዚህም ሴቶች በዋናነት የመበዝበዙ ተዋናይ ሆነው ይገኛሉ፡፡ (እናት፤326) ይሉናል ታዲያ በማህብረሰቡ ውስጥ የአብዛኛው ይህንን አስተሳሰብ ገዝፎ የሚገኝ ቢሆንም የውብ ድንበር ግን በእርሷ በግል ሕይወቷ ብዙም ያልተመቻቸላትን የትምህርት ሕይወቷ አብራት የምታገለግላትን ሴት ወደ እውቀት ማዕድ እንድትገባ የራሷን አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ በተለይ ይህንን ያደረገችበት ወቅት የመጀመሪዋን ልጅ ወልዳ የቤት ሥራውን የቤት አጋዥ ባስፈለጋት ጊዜ ነበርና በተለይ ሰራተኛዋ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ስራውን የሚሸፍኑላት እናቷ ስለነበሩ በዚህም ከፍተኛ ተቋውሞ ይደርስባት ነበር፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የሴቶቹ በማህበራዊ ተሳትፎአቸው እና ሙያዊ አስተዋጽአቸው አንድ አይነት አይደለም፡፡ በሄዱበት የሕይወት መስመርና ባጋጠማቸው ችግሮችን ተቋቁሙ የማለፍ ጥንካሬ መሰረት ለሀገርም ሆነ ለማኅብረሰብ የሚያደርጉት አስተዋፆ ሊለያይ ችሏል፡፡

ስኬት ለሁሉም ሰው የተለያየ ትርጉም አለው፡፡ ለህይወት ዋጋ ከምነሰጣቸው ነገሮች ጋር የተያያዘ ነገር ነው፡፡ እያንዳንዱ በልፋቱ የሚያገኛቸው ደሞዝ ዋጋ ነው ሌላው ደግሞ ትምህርቱን ጨርሶ ያሰበውን ሥራ መያዝ ማግባት መውለድ ሊሆን ችላል፡፡ ሌላው ደግሞ ለአካባቢው ባሉ ሰዎች ወይም በብዙሀን ዘንድ ለሰራው ሥራ እውቅና ዝናን ማትረፍ ሊሆን ይችላል፡፡ የሴቶቹ ግለ ታሪክ ስንመለከት ፀሐይ ለሕይወት ያላት አመለካከት የተለየ ነው፡፡ የሰው ልጅ የእድሉ መሀዲስ ነው፡፡ የሚለው አመለካከቷ በኖረችበት ዕድሜ የሕይወት መርህ አድርጋ ተጉዛለች፡፡ ባደገችበትና በማኅበረሰብ እና ቤተሰብ ለሴት ልጆች የሚሰጠውን አመለካከት ያሸነፈች ናት፡፡ በተለይ ሴቶች የኑሮ ሁኔታ የሚወሰነው በሚያገቡት ባል በመሆኑ፡፡ ቤተሰብ ለሴት ልጁ የሚመኘውን ጥሩ ባል አግብታ እና ልጆች ወልዷ ወግ ማዕረግ ማሳየት እንዳለባት በሚታመንበት ማህበረሰብ ውስጥ አላማዋን ለማሳካት ቆርጣ የተነሳች አስተዋይና ጠንካራ ሴት ናት፡፡ በተለይ የሰው በትምህርት ጊዜዋን በአግባቡ የምትጠቀም ራሳን የምታከብር በእጇ የገባው እድሎች በአግባቡ ከውጤት ጋር የምትጠቀም በባህሪዋ ግትር ያልሆነች በሥነ ምግባር የታነፀች በእቅድ የምትመራ በጋለ ጥልቀትና ፍቅር ተግታ የምትሰራ ሥራ ወዳድ የሆነች ሴት ስትሆን እድሎቿ በራሷ ትጋት እንዲሳካ እና ሕልሟን መኖር የቻለች ሴት ናት፡፡ ትግስት በትምህርቷ ጎበዝ የጀመረችው በቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ብላ ብትጀምርም  ያሰበችውን ዶክተር መሆን ችላለች፡፡ ህልሟ ግን ፕሮፌሰርነት መሆን ግን አላሳካችም፡፡ የሕክምና ትምህርቷ ግን አልጋ ባልጋ አልነበረም፡፡

የሕክምና ትምህርት ለመከታተል የሄደችው ወደ ፈረንሳይ ነበር፡፡ ነገር ግን የደረሳት የጥርስ ሕክምና ሲሆን ያህንን ለመማር ፍላጎት ስላልነበረ ከአውሮፓ ሀገር ወደ አፍሪካ መመለስ  እና ለትኬት የሚሆን ብር ያስፈልጋት ነበር፡፡ ብሩን ለማግኘት የጉልበት ሥራ መስራት ነበረባት፡፡ ትግስት ያደገችው የተሻለ ኢኮኖሚ ያላቸው ቤተሰብ ምንም ሳይጎድላባት ያደገች ነበረች፡፡ ሁሉ ነገር ቤተሰብ የሚሸፍን በመሆኑ ኑሮን እንዴት መጋፈጥ እንዳለባት አልተማረችም ነበር፡፡ በጊዜው ሕልሟን ለማሳካት ወደ አፍሪካ የምትሄድበትን ትኬት ለመግዛት በሆስፒታል ውስጥ የጉልበት ስራ በመስራት ይህንን ችግር ተጋፍጣ አልፋለች፡፡ ሴኔጋል ከመጣች በኋላም የራሷን ወጪዎች የምትሸፍነው ራሷ በመሆኗ ቀን ቀን እየተማረች ማታ ማታ ልጅ በመጠበቅ እና በክረምት ፈረንሳይ ሀገር በመሄድ ከእንግሊዝኛ ወደ ፈረሳይኛ የማስተርጎም ሥራ እየሰራች ለዓላማ ያላትን ቁርጠኛ የመርህ ሰው ናት፡፡ ሁለተኛ ዜጋ በመሆኗ የፕሮፌሰር የመሆን ህልሟ ቢጨናገፍባትም ለትዳሯ ስትል በብረንዲ ለመኖር ወስና በአንድ ሆስፒታል ተቀጥራ ብትኖርም

በባህል ግጭት ትዳሯ ላይ የነበረውን ክፍተት ቁጭ ብሎ ከማልቀስ ወደ ውሳኔ እድትገባ አድርጓታል፡፡በዚህም የሚያጋጥማትን ተግዳሮቶች እያለፈች ለስኬት የበቃች ሴት ናት፡፡ ትግስት ከልጅነቷ ጀምሮ ያሰበችውን ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አትልም፡፡ ባላት ጥበብ ተጠቅማ የቤተሰብ ፍቅር ወደራሷ እንዲመለስ አድርጋለች፡፡ በምትፈልገው የሙያ መስክን እንድትሰማራ ሆናለች፡፡ በጥንካሬዋ ልጆቿን በምትፈልገው መንገድ ቀርፃ አሳድጋለች፡፡ ዘረኝነትንና እና የሴትነት በበታችነች በሚታይበት ዓለም ሴት መስራት እንደምትችል ሰርታ ያሳየች ሴት ናት፡፡ ጀግና፣ቆራጥ እና ለዓላማዋ መስዋት የምትከፍል እናት ናት፡፡ ማንኛውም ሰው የማህብረሰብ ግንኙነትና የሕይወት ተሞክሮ ውጤት እንደመሆኑ ስዕብናውም የሚቀረፀው በቤተሰቡና በማህረሰብ ነው፡፡ በመገንዱ ላይ ሊያቆም የሚችለውን መሰናክሎች ቢኖሩትም ስኬት ላይ ለመድረስ የራሱን  የሚፈልገው ግብ ላይ ለመድረስ ላይ ያተኩራል በመሆኑም ሴቶቹ መድረስ የሚፈልጉበት ደረጃ ለመድረስ እና ማሸነፍ ያለባቸውን እሳቤዎች አሸንፈው መውጣት የቻሉ ሴቶች ናቸው፡፡

## 3.4. ሴትነት ያጋጠማቸው ተግዳሮት

በተለይ በጊዜው ሴቶች ብዙም የማይመረጠውን የጠባይ ማረሚያ ቤት ስራ በወጣትነቷ ነበር የገባቸው፡፡ የጠባይ ማረሚያ በወጣትነቷ ነበር ሀላፊ የሆነችው፡፡ በዚህም በሴትነቷ ብዙ ትችቶች የተቀበለች ሲሆን ለአላማ ጽናትን እና በሚደርስባት

> በዚህ ሥራ ላይ ስመደብ እድሜ በሀያዎቹ አጋማሽ ላይ የሚገኝ የነበረ ሲሆን ከእድሜ በተጨማሪ ከፆታዬና ከቁመቴ ማጠር ጋር ተደምሮ በተቀሩት የድርጅት ወንድ ስራተኞች ዘንድ በመጠኑም ቢሆን የማጉረምረም ስሜት መታየቱ አልቀረም፡፡ (ፀሀይ፤74)

ከላይ እንዳየነው ፀሀይ በችሎታዋ እና በጥረቷ ይህንን ሥራ አግኝታ ማህበረሰቡን ለማገልግል ስትሞክር ነገር ግን ማህበራዊ ግዴታዋን እንዳትወጣ ተግዳሮት ሲሆኑባት እንመለከታለን፡፡

ፀሀይ በኃላፊነት የምትሰራበት መስሪያ ቤትም ትኩረት አድርጋ የምትሰራቸው ስራዎች ማህበራዊ ኑሮ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል የሚባሉትን እናቶች፣ ሕጻናትን በእድሜ የገፉ አዛውቶችን እና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ለማገዝ የምትንቀሳቀስ ሲሆን በዚህም ከተለያዩ ባለስልጣናት ጋር የሚያገናኛት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በዚህ

በምታደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ በምትሰጠው ሀሳብ ተመራጭ ሲያደርጓት ነገር ግን ሴት በመሆኗ እንዴት የሚሉ ጥያቄዎች ይነሱባት ነበር፡፡

> እኔ ከተመደብኩበት የሥራ ኃላፊነት ሴት እንዴት የሚለው የኅብረተሰብ አመለካከት በተለይ መልኩ ይገለጽ ነበር፡፡ ስሜ ፀሐይ ሆኖ ሳለ የሚደርሰኝ ደብዳቤ አቶ ፀሐይ ተብሎ የሚደርሰኝ ጊዜ ነበር፡፡

ከላይ እንደምንመለከተው ፀሀይ በሚኒስተር መስሪያ ቤት ተዛዋውራ በምክትል ኃላፊ በነበረችበት ጊዜነበር እንዲህ ያለ ደብዳቤ በተደጋጋሚ የሚደርሳት፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን በሚኒስተር መስሪያ ቤት ደረጃ በኃላፊነት የሚመሩ ሴቶች ቁጥራቸው አነስተኛ ነበር፡፡ ለሴት ልጅ ይህንን መሰለ ኃላፊነት ላይ ሊሰጣት አይችልም የሚል እሳቤ እንዳለ የሚያመለከት ነው፡፡ አሁኑም ቢሆን በሀገሪቱ በሚኖሩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በኃላፊነት የሚመሩት የሴቶች ቁጥር ከወንዶች እኩል መሆን አልቻለም፡፡ ማህብረሰቡ ለሴት ልጅ ያለውን አመለካከት ለሴት ልጅ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ተመሳሳይነት አገልግሎት ዘመን ከወንዶቹ እኩል ቢኖረን ለሴቶች የተደረገው አነስተኛ ሆነ፡፡ እንደሆነ የሚያሳይ ነው ፡፡

> *በመስሪያ ቤታችን ለሠራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ተደረገ፡፡ የተደረገው ጭማሪ በተመሳሳይ የሥራ ምደብና ተመሳሳይ የአገልግሎት ዘመን ከወንዶቹ እኩል ቢኖረንም ለሴቶች የተደረገው አነስተኛ ሆነ፡፡ ይህንኑ በተመለከተ አራት የምንሆንና በተለያየ ምድብ ሥራዎች ላይ የምንሠራ ሴቶች ተሰብስበን አቤቱታችን ለማሰማት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊ ዘንድ ቀረብን፡፡*
>
> *ጉዳያችን ያስረዳናቸው አለቃ <አሁን እናንተ የሚከፈላችሁ መቼ አነሳችሁ፣የሚያስፈልጋችሁ ባሎቻችሁ ያመጡላችኋል፡፡ እናንተ ብሎ ደሞዝ ጠያቂ>* ብለው ተቆጡ(ፀሐይ፤84)፡፡

ከላይ እንደምንመለከተው ለሴቶች የሚሰጠው አመለካካት በእጅጉ አነስተኛ መሆኑ ነው፡፡ በተለይ በከፍተኛ ሀላፊነት ያሉ በትምህርት ዝግጅታቸው ሆነ በተሰጣቸው ሀላፊነት እንዲሁም የእናቶችን(የሴቶችን) የኑሮሁኔታ ለማሻሻል የሚተጋ መስርያ ቤት ሐላፊ እንዲህ ያለ አመለካከት መኖር በሴቶች ላይ ለሚደርስ ሥርአተ ፆታ እኩል አለመሆን ብቻ ሳይሆን ይህንን አመለካከት ለመታገል እና ሴቷ ከወንዱ እኩል መሆኗን የሚሰራው የአመለካከት ለውጥ አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

> በተሰማራሁባቸው ሥራዎች በሴትነቴ ብዙ ችግር አጋጥሞኛል፡፡ ሴት ሆኖ በተለይም በባለሙያ ደረጃ () መስራት ብዙ ፈተናዎች አሉት፡፡ ብቻዬን ውጭ ሀገር በነበርኩበት ጊዜ "ባልሽ የለም፤ ምን አለበት…." በማለትም ሆነ በማስፈራራት በሴትነቴ ለመጠየቀም የሞከሩ አልጠፉም፡፡ ይህንን ሁሉ ተቋቁሞ ለማለፍ መቻል ትልቅ ፈተና ነው፡፡ ከተመደብኩበትና ከምሰራው ሥራ ይልቅ ሴትነት ጎልቶ የታየበት ጊዜም አጋጥሞኛል፡፡(134)

ፀሐይ በፓፓዎ ኒው ጊኒ ሀገር ውስጥ በምትሰራበት ወቅትም ስራዎቿ ሳይሆን እክል የሚገጥማት የነበረው የሀገሩ ባህል ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ሴቶች ሕይወትን የሚያመለከቱ በመጀመሪያ ሴት የወንድ የበታችነት እንደሆነች አምነው ተቀብለው ነው፡፡ ይህ እምነትም አነዚህ ተምረው የተባሉ የፖርላማ አባላትንና ሌሎችንም ያጠቃልላል፡፡ በባሎቻቸው ይደበደባሉ፣ የሚደርስባቸውንም የጾታ ትንኮሳ እንደ አንድ የሕይወት ትክክለኛ ገጽታ ተቀብለውት በሚኖሩ ማህብረሰብ ውስጥ መኖር ለባላታሪካችን በእጅጉ ፈታኝ ነበር፡፡ ከዚህም በተነሳ ፀሐይ ላይ የሚደርሰው የጾታዊ ትንኩሳ ብዙም ክብር የሚነካ ነገር አድርገው አይመለከቱትም ነበር፡፡ ይህ አመለካካት ተምረዋል ማህብረሰቡን ይለውጣሉ የሚባሉ የህግ አውጪዎችም ላይ የሚስተዋል መሆኑ ደግሞ የነበረውን ተግዳሮቶች ከፍተኛ ነበር፡፡

> የአፍጋኒስታል ሴቶች በጤና፣ በትምህርት ባልተመጣጠነና መጠኑ አነስተኛ በሆነ የምግብ አቅርቦት ካለባቸው የጎላ ችግር በተጨማሪ መጠኑ አነስተኛ በሆነ የምግብ አቅርቦት ኀብረተሰቡ የሚያደርስባቸውን በደልም እንዲሁም የከፋ ነው፡፡ ፆታ ትንኮሳና ጥቃት፣ በመደፈር ያለ እድሜ ጋብቻና በመሳሳሉት ከሚደርስባቸው በደልም በተጨማሪ የሀገሪቱ ሕግም የሚታደጋቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ (ፀሐይ፤ 162)

ማኅብረሰቡ የራሱን ወንድና ሴት (ማንነት) የሚፈጥርበት ብዙ ድርጊቶች አሉት፡፡ የአፍጋኒስታን ሴቶችም የኢኮኖሚ ችግሮች ብቻ ሳይሆን ያለባቸው ጭቆናዎች ሴቶችን እንደ ሰው ሳይሆን ወንዶች አገልጋይ ተደርጋ ነው የምትታየው፡፡ የማርክሳዊ ሌሊናዊ መዝገበ ቃላት ስለ አባዊ ስርአት ሲገልጽ በኢኮኖሚ በማኅበራዊ በቤተሰብ ኑሮ ረገድ የወንድ የበላይነት የሰፈነበት የጥንት ማኅበረሰብ ሥርአት ነው፡፡ አባዊ ስርአትን ያሰፈነው የጥንት ማኅበረሰብ ኢኮኖሚ እየዳበረ መምጣቱና ምርታማነቱ ከፍ ማድረጉ ነው፡፡ ሴቶች ሲሰሩት የነበረውን የከብት እርባታ፣የአደን፣እርሻ ወ.ዘተ ወንዶቹ እየተረከቡ ሴቶች ወደ በቤት ውስጥ ሥራ ተወሰኑ፡፡ ውርስ የአባትን ዝርያ መስመር እየቆጠረ ይሄድ ጀመር፡፡የጎሳው መሪ ወንድ ነበር፡፡

በእማዊ ወደ አባዊ ሥርአትን ቀስ በቀስ ተሸጋገረ፡፡ ዩቫል ሐረሪ ሳፔንስ በሚለው መጽሀፍ ከግብርና አብዮት ጀምሮ ብዙዎችን ማህበረሰቦች አባዊ ነበሩ፡፡ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች ብዙ ዋጋ የሰጡ ናቸው፡፡ ይላል ከአባዊያን ሥርአት መገለጫዎች ውርስና ዘር ቆጠራ ቅድሚያውን ይወስዳሉ፡፡ በማለት ዶ/ር ይሁኔ ይገልፃሉ፡፡ የአፍጋኒስታል ሴቶችን ስንመለከት ሴቶች የባሎች ወይም የማህበረሰብ ንብረት ተደርገው ተቆጥረዋል፡፡ እንደ "ዩቫል ሐራሪ አገላላጽ በብዙው የታሪክ ሂደት ሴቶች የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብ ንብረት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡" ይህ በእውኑ ዓለም የታየ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ሴት ልጅ የወንድ አገልጋይ ተደርጋ የምትታየው፡፡ ሴትን ዘርን ከማስቀጠል እና ለቧላ አገልጋይ ውጪ ሌላ አስተዋጽኦ እንደሌላት የሚያመለክት ነው፡፡ይህም አባዊያን ሥርዓት የፆታ እኩልነት በማዛባት ብሎም በሴቶች ላይ በደል እንዲደርስ እና የወንዶች የበላይነት በመጠበቅ ለሴት ዝቅ አድርጎ በማሳየት ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ጨቋኝነቱን የሚያሳይ ነው፡፡

## ዶ/ር ትግስት ግርማ

አደለ ሒትማና እና ትግስት በዳካር ዩኒቨርስቲ በህክምና ትምህርት ሲማሩ የተዋወቁት፡፡ እሷ ከኢትዮጵያ እርሱ ከብሩንዲ ቀስ በቀስ የተጀመረ ጓደኝነት ወደ ፍቅር ተቀይሮ በስተመጨረሻ ወደ ጋብቻ አመራ፡፡ ሁለቱም በትምህርታቸው ውጤታማ ነበሩ፡፡ እርስ በእርስም የሚዋደዱ የሚፋቀሩ ነበር፡፡ በሁቱም በጾታ እኩልነት ያምናሉ፡፡ ወደ ትዳርም የገቡት ቀስ በቀስ በመሆኑም ኑሮቸውን እኩል እየተጋገዙ ይሰሩ ነበር፡፡

> *ለመጀመሪያ አንድ የስቱዲዮ አፓርታመንት እንደ ማረፊያ ተከራይተን ገባን፡፡ የቤት ሠራተኛም አልነበረም፤ ከሁሉ የማስታውሰው እኔ ምግብ ስሰራ ባለቤቴ ቤት ይጠርግ ነበር፡፡ በኋላ አንድ ወዳጃችን የሆነች መጣችና "ያንቺ ባል ቤት ይጠርጋል" ብላ ተገርማ በማዘን ታየው ጀመር፡፡* (ትሙት፤73)

በብሩንዲ ወንዶች እንደ ንጉስ ነው የሚያታዩት፡፡ ማህበረሰቡም ስንል ወንዶችም ሆነ ሴቶች ወንዶች የበላይ እንደሆኑ የሚያስቡት፡፡ ትግስት በትምህርቷ ከቧላ እኩል እንደውም በተሻለ ውጤት የሕክምና ስፔሻሊስት ናት፡፡ በእውቀት ሲታይ የተሻለች እርሷ ሆኗ ሳለ የቤት ውስጥ ስራን ግን ለሴቷ ብቻ ተወስኖ ሲሠጣት እንመለከታለን፡፡ ሴት ልጅ ምንም ብትማር በቤት

ውስጥ ያለውን ስራዎች መስራት ያለባት የሚለው አመለካከት በማህበረሰቡ ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡

> ያንተ ቤት ሚስትህ ናት ሱሪ የታጠቀችው እሷ ነች የምታዝህ፤ አሁንስ አበዛኸው፤ ወንድ ሁን እንጂ እያሉ ነው፤ ደግሞ ባለቤቴ አንድ ያንገት በላይ ስፔሻሊስት ሥራው በጣም ተፈላጊ ስለሆነ ሰው ሁሉ ዶክተር ዶክተር ስለሚለው ኩራት እራሱ ላይ ወጣበት፡፡ (ትሙት፣81)

ትግስት በእስያ የኤፖልንስራ ከጀመረች በኋላ ለጥቁር ሴቶች ያላቸውን ንቀት አልፋ ባሳየችው ችሎታዋ ሁሉንም ያከብሯት ጀመር፡፡ በስራዋ በጣም ስላከበሯት የኖርዌይ ተወላጅ አለቃ ሲየር የመጀመሪያ የሴት የሀገሩ የአለም የጤና ጥበቃ ልዩ ተጠሪ ሆና ተሾመች፡፡ በዚህ ኑሮዋን ተለማምዳ በስራዋ ውጤታማ እየሆነች መጣች፡፡ አዲሱ አፍሪካ ዳይሬክተር ለአፍሪካ እንድትሰራ አፍሪካ እንዳንቺ አይነት ሴት ያስፈልጋታል የሚል ደብዳቤ ላከላት እርሷም ትልቁ ህልሟ ስለነበረ ለአፍሪካ ለመስራት እስያን ትታ ወደ አፍሪካ መጣች፡፡ መጀመሪያ የተመደበችው የጋምቢያ የዓለም ጤና ድርጅት ልዩ ተጠሪ ተብላ ነበር፡፡ ነገር ግን የባለቤቷ ሀገር ሰውየሆነ እርሱ እና የቤተሰቡ ጥሩ ወዳጆቿ በመሆናቸውእና እርሱ የተመደበበትም አዲስ ስለሆነ እርሱን ለመረዳት በማሰብ ከጋምቢያ ቀርታ የኤች.አይ.ቪ ሪጅናል አማካሪ ሆና መስራት ጀመረች፡፡ በኤድስ ሥራዋም ያፈራችው ልምድን በመጠቀም ከአርባ ስድስት ሀገራ ያሉትን ፕሮግራሞች በጥሩ ማስኬድ ጀመረች፡፡ ነገር ግን ውጤታማ መሆኗን አለቃዋ አልወደደላትም

> በጠዋት ከምጀምርበት ሰዓት ጀምሮ በየአምስት ደቂቃ እየደወለ በሆነ ባልሆነው ይጮሀል፡፡ ከነጭራሹ አንድ ቀን አለቃ ብለሽ ጥሪኝ አለኝ፡፡ እኔ ድሮም በስምህ ነው የምጠራህ አሁን እንደዛው ነው የምቀጥለው፤ ይኼ ግን ላንተ ያለኝን አክብሮት አይቀንስም አልኩት፡፡ ከነጭራሹ ለትምህርት የምሄድበትን አንድ ጉዞ በመጨረሻ ሰዓት አስቀረብኝ፡፡ በስብሰባ መካከል ሌሎቹ እስኪ ገረሙ ድረስ ያሾፍብኛል፡፡(ትሙት፤114)

ትግስት ከተደላደለ ስራ እና ኑሮ ለቅቃ ለአፍሪካ ለመስራት ወስና ብትመጣም ባገኘችው ውጤታማ መሆን አለቃዋን አላስደሰተውም፡፡ የብሩዲው አለቃዋ ውጤታማ እንዲሆን ነበር የመጀመሪያው ሀሳቡ ነገር ግን የድርጅቱ ውጤት ሳይሆን የጾታ የበላይነቱ ነው የታየው፡፡ በተሰራው ስራ እውቅና ከመስጠት ይልቅ እኔ ልግዛሽ አንቺ ደግሞ ሎሌ ሆኚ አይነት አስተሳሰብ

ነው ያለው፡፡ ይህ የወንዶች የበላይነት በተማሩ እና ማህበረሰብን እንጠቅማለን እናገለግላለን ለማህረሰብ ቆመኛል የሚሉ ወንዶችም ሴት በእውቀት ከበለጠቻቸው እንደማይቀበሉት ያሳያል፡፡

በያዘችው የሥራ መደብ ላይ ተሹማ የመጣው አለቃ በየጊዜው ለስብሰባ እና የአሜሪካ ትልልቅ ሰዎች ለማግኘት ሲመጣ ከኤርፖርት ተቀብላ ማስተናገድ አንዱ ሥራዋ ሆነ፡፡ሰውዬው የሰባ አምስት ዓመት ሽማግሌ ብዙ ልጆችና የልጅ ልጆች ያለው ሲሆን ትግስት እንደ አባቴ በማየት ታከብረዋለች፡፡ አንድ ቀን ከጄኔቫ ወደ ሶልት ሌክ ሲቲ ሞርሞር የሚባሉ ሃይማኖት ያላቸውን ማህረሰቦች ጋር ሲሄዱ አውሮፕላን ውስጥ ፆታዊ ፍላጎት እንዳለው ይነግራታል፡፡ ነገሩ እንዳልገባ ለማለፍ ብትሞክርም ይህ ፍላጎት ከአለቃዋ የበለጠ እየተጣናከረ መጣ፡፡ በዚህም ቁጭ ብለው ለእርሱ ያላትን እህታዊ አክብሮት እንጂ ለጾታዊ ግንኙነት ማድረግ እንደማትፈልግ ገለፀችለት፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የበለጠ ጫና ያደርግባት ነበር እንዲሁም ያለውን ንቀት ያሳያት ነበር፡፡

> ከተናገርኩኝ ዕለት ጀምሮ ትልቁ ስቃዬ ሆነ፡፡ አንዴ ሰው ፊት ያልሆነ ነገር ይናገረኛል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ምንም ስራ እንዳልሰራ ምክንያት እየፈጠረ ያቆመኛል፡፡ አንዳንዴ ምንም ሳልዘጋጅ ስብሰባ ይልከኛል፡፡ ኤርፖርት ውስጥ እኔን አቁሞ ጫማውን ያስጠርጋል፡፡ አንድ ቀን ስብሰባ መሃል ቁመቷ ጣት ያክላል ኩራቷ ግን ተራራ ያክላል ብሎ ተናገረ፡፡ (136)

ወንዶች ሴቶች ላይ በስነ ልቦና ባላቸው ውጫዊ አቋም አካሏ ላይም ማላገጫ ሲደረግ እንመለከታለን፡፡ በደረሰባት የስነ ልቦና ጉዳትም የምትወደውን ሥራ ላይ የራሱን ተጽእኖ ሲያሳድር እንመለከታለን፡፡

አምፍሬ አለማቀፋዊ ድርጅቶች በመሆኑ በተለይ ዋና አላማው አድርጎ የተነሳው የሰው ሕይወትን መለወጥ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራው ደግሞ በአፍሪካ ላሉ ከከተማ ርቀው ደሃ ማህበረሰብ ባህሉን ሳይጋፋ በሚያስፈልገው መንገድ ጤናውን እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡ ይህ ለአፍሪካ የተቋቋመው ድርጅት ግን አፍሪካዊ ሴት በዳይሬክተርነት መቀበል ሲያቅተው እንመለከታለን፡፡ ድርጅቱ በጤናው ዘርፍ የራሱን አስተዋጽኦቢያርግም ይህንን የሚመሩት መሪዎች ግን ወንዶች በመሆናቸው ሴት በመሆኗ ብቻ መቀበል ሲያቅታቸውና በአደባባይ ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ እናያለን፡፡

እኔ የመጀመሪያ አፍሪካዊ ሴት የአምሬፍ ዋና ዳይሬክተር በመሆኔ፤ እነዛ በቀድሞ አመራር የፈለገውን ሲሰሩ የከረሙ ሰዎች እንዴት ባንዲት አፍሪካዊ ሥር እንሰራለን ብለው አሻፈረኝ አሉ። አንዴ በየሀገራቸው የአምሬፍ ቢሮ የተቋቋመበትን ህግ፤ አንዴ እነርሱ ገንዘብ ካላመጡ መስሪያ ቤቱ እንደማይሰራ ይነግሩኛል።(160)

ትግስት ይህንን አስተሳሰባቸውን ለማስቀየር ብዙ መጣርና መልፋት ይጠበቅባት ነበር። የገጠማት ችግሮች በሙሉ የበለጠ ጠንካራ እንድትሆን አደረጉላት። ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው ድርጅቱ በውጭ ባሉ ለጋስ ሀገራት ከሚገኝ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ የድርጅቱ ህልውና ወሳኝ በመሆኑ ይህንን አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ማሸነፍ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጥንካሬ እና በራስ መተማማን ይጠይቃል። ያላትን ልምድና እውቀት በመጠቀም ከነበረው አስራር በመውጣት አፍሪካን ለአፍሪካውያን በሚል ፕሮግራም በማቀድ ብዙ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ተሳታፊ በመሆናቸው ለድርጅቱ ከፍተኛ ገቢ ማስገኘት ተቻለ። በንጽጽር ሲታይ ከአፍሪካ የሚሰበሰው ገንዘብ ከአውሮፓ እና ከአሜሪካ ከሚሰበሰበው ከፍተኛ በመሆኑ ስልጣኑም ወደ አፍሪካ እንዲያዘነበል ተቻለ።

ትግስት በሕይወት ዘመን በርካታ ፈተናዎችን እንቅፋቶችን ቢገጥሟትም መሸነፍና እጅ ስትሰጥ አንመለከትም። ችግሮችን እስካልተጋፈጠ ድረስ ምንም አይነት ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል አሳይታናለች።በሕይወት በውጣ ውረድ የተሞላች ናት። በጽናት ለተጓዘ የተሻለ ቦታ ላይ እንደሚደረስ አሳያታናለች። የተሻለ ቦታ ይዞ ለመዝለቅ በጽናት መታገል ዛሬ በደረስችበት የስኬት ደረጃ እንዳበቃትና እና ተግታ መስራቷ እና ለመወሰን ያለማመነታቷ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በራሳ መተማመኗ ሴት መሆኗ ነው።

### የውብ ድንበር

የውብ ድንበር በአስራዎቹ መጨረሻ በአፍላ ወጣትነቷ ጊዜዋ አፈቀርኩሽ ብሎ አላስቆም አላስቀምጥ ካላት ባለስልጣን ጋር ጾታዊ ግንኙነት ጀመረች። ይህ ስህተት ቀጣይ ሕይወቶቿ እና ህልሞቿን መኖር እንዳትችል ጋሬጣ ሆኖባታል። ወንዶቹ (አፍቃሪዎቿ) አሁንም እንደሚወዷት ይነግሯታል። ምኗን አይተው ውጫዊ ውበቷ ቆንጆ ስለሆነች።

ተካልኝ ብስጭቱ ሊቋቋመው ስላልቻለ ሀገር ለቆ አዲስ አበባ ሄዶ ትምህርቱም እየተማረ መሆኑን ሰማሁ። ኤርፎርሱ ከመውለዴ በፊት አግኝቶኝ ሲለምነኝ እንቢ ብዬ እንዲህ በመሆኔ ያሳዘነው መሆኑን ነግሮኝ ልጁን ለአባቱ ሰጥቼ እንድንጋባ

ጠየቀኝ፣ ባህር ሃይሉም ከባለስልጣ ጋር ያለሁበት ሁኔታ ሰምቶ ይህ ባለስልጣን የውበት ጊዜሽ እስካለ አብሮኝ የሚቆይና በኋላ እንደሚከዳኝ በመግለፅ ወልጄ ልጄን ለአባቱ ሰጥቼ እንድንጋባ ዓፈልኝ። (የውብ ድንበር፣ 131)

ውበቷ በወንዶች ዘንድ ተፈላጊና ተፈቃሪ አድርጓታል። ነገር ግን በተፈጠረው ችግር አለሁልሽ የሚል አታገኝም። እጇን ዘርግቶ ወደ ህልሟ የሚያደርሳትን ወንድ አፍቃሪ አልተገኘም። እንድውም ልጅሽን ለአባቱ ስትጥሽ እኔን አግቢኝ ከእርሱ እኔ እሻልሻሁ የሚል አፍቃሪ ያለው። ወንዶች ሴቶችን የሚፈልጉት ለራሳቸው ስሜት ብቻ ነው። ስለሚያፈቅራት የራሳቸው ለማድረግ እንጂ እርሷ ልጇን ትታ ወደ እነርሱ ስትመጣ የሚደርስባትን የስነ ልቦና ጉዳት አልታየቸውም። ሴት መሳሳትና መውደቅም አይፈቀድላትም፤ከተሳሳተችና ከወደቀች ግን አለቀላት፤ ከጨዋታ ውጭ ትሆናለች። አንድ ወንድ አንድ ትልቅ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ለሁለት ሰዓታት ያህል ሊጨነቅ ይችላል። ሴት ግን ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ እቅልፏን ልታጣ ትችላለች። ምክንያቱ ደግሞ ከወደቀች በኃላ የሚያነሳት ስለሌለ።

የሴቶቹን ግለ ታሪክ ስንመለከት በተለይ በሴትነታቸው የሚደርስባቸው ችግሮች እና ተግዳሮቶች ሲጋፈጡ እንመለከታለን። ኢትዮጵያ ውስጥ ሴት ሆኖ መኖር ከባድ ነገር ነው። ሴት እንደ ሰው ልጅ የማይቆጠርባቸው ጊዜ አሉ። ሴቶች ትላልቅ ኃላፊነቶች እንዲወስዱ አይበረታቱም። ይሄ ደግሞ ጥንካሬአቸውና ልምዳቸውም የማሳደግ እድሎች ይነፈጋሉ። ለሴቶች የተቀመጠው ዝቅተኛ ግምት ልቀት ማለፍ እንደሚችል በተግባር በማሳየት እድሎች ሊሰጡን እንደሚገባ ለማስከበር በእጅጉ መታገል አለባቸው።

**ከዘረኝነት አንጻር**

ዘረኝነት አንድ የህዝብ ወገን በውጫዊ ማንነቱ ብቻ የሚገለጥ ከሌሎች ከሚበልጥበት ባህርይ አለው ብሎ የሚል አመለካካት ነው። ይህም ሌላውን ወገን በንቀትና በማጣጣል  የማራርቅ የሚቃረንና ብሎም እስከ ማጥቃት (ማጥፋት)የሚዘልቅ ነው። አሁን ያለው ዘረኝት የተመሰረተው በሰዎች ውጫዊ( ሥነ ሕይወታዊ) ልዩነት ላይ ነው። ለምሳሌ የቀለም ልዩነት የእነዚህ አመለካከቶች አራማጆች በዋናነት ይጠቀሙታል። ዘረኛው በማህበረሰብ ውስጥ በሁሉም መስክ የአንዱ ዘር ተፈጥሯዊ የበላይነት በሌላው የበታችነት ለማረጋገጥ ተረጋግጦ ይሰራል። ዊኪፒዲያ እንዲህ ብሎ ይበይነዋል። ትግስት የዓለም ጤና ድርጅት ስራዋን ከጀመረች በኃላ ስራዋን የጀመረችው በእስያ ኔፖል ከተማ ነበር። እስያዊን ደግሞ ራሳቸውን

የሚመለከቱት ልክ አውሮፓውያን ልዩ ፍጥረት እና የእውቀት ባለቤት እነርሱ ብቻ እንደሆኑ ነው፡፡ በተለይ ለአፍሪካውያን ያላቸውን አመለካካት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የሚያጋጥማት ተግዳሮት ትገልፃለች፡፡

> ኔፓል ደግሞ የባሰ ሆነ፡፡ ከነጭራሹ በየመንገዱም ጥቁር ጥቁር እያሉ ይከተሉኝ ጀመር፡፡ መስሪያ ቤትም ያሉት የሀገሩ ተወላጆች ሰላም አይሉኝም፡፡ (ትሙት፣107)

> በሥራዬም በጣም ስለተከበርኩ የኖርዎይ ተወላጅ አለቃችን ሲቀር የመጀመሪያ የሴት ሀገሩ የአለም የጤና ጥበቃ ልዩ ተጠሪ ሆኜ ተሾምኩ፡፡ አንድ አንድ ሴቶች እርሷን ማየት አለብን እያሉ ቢሮዬ ድረስ ይመጡና በጣም አድንቀውኝ ይመለሳሉ፡፡ ጥቁር መሆኔ ደግሞ በጣም ያስገርማቸዋል፡፡(ትሙት፣109)

አውሮፓውያን ለአፍሪካዊያን ያላቸው አመለካካት አሁን ድረስ የተሸረረ ነው፡፡ በተለይ በትምህርት ከፍ ብለው በኃላፊነት ደረጃ ሲይዙ እንዴት ቻላችሁት የሚል አመለካካት አላቸው፡፡ በአፍሪካዊ ሆነው እንዲያው ሴት ሲሆን ደግሞ ግርምታቸው ሲጨምር የምንመለከት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የአውሮፓ ሕብረት መሰረታዊ መብቶች ኤጀንሲ ባወጣው ዘገባ አፍሪካውያን ላይ የሚደርስ የዘረኝነት ጥቃት እየጨመረ መመጣቱን ገልፀው ጥናቱ ከ6700 በላይ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ትውልድን ጥቁር ዜጎችን የተካካቱበት ሲሆን ውጤቱም 39% የነበረው ወደ 45% ማደጉን ቢቢሲ ኒውስ ያወጣው ዘገባ ያመለከታል፡፡ ትግስትም በግለ ታሪኳ ይህ ተግዳሮት እደገጠማት እናያለን፡፡

## 3.5. የወላጅ ፍላጎት በልጆች ላይ

የባለ ታሪኮቹን የቤተሰብ ሁኔታ ስንመለከት ሶስቱም ከተለያዩ የኑሮ ሁኔታ ካላቸው ቤተሰቦች የተገኙ ናቸው፡፡

**የውብ ድንበር**

የውብ ድንበር እናት ወ/ሮ ለጥ ይበሉ እናቷ ትምህርት ቤት እንድትማር ቢጠይቋት መማር እንደማትፈልግ ማግባት እንደምትፈልግ ትገልፃለች፡፡ እናትና አባቷ  በሶዶ ጉራጌ ባህል መሰረት የተጋቡት፡፡ የውብ ድንበር አባት አቶ ነጋሽ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ሲሆን በሻሸመኔ የእርሻ መሬት፣ መቂ የከሰል መሬት እንዲሁም አላባ ቁሊቶ ቤትም አላቸው፡፡ እናትና አባቷ ተጋብተው አምስት ልጆች ቢያፈሩም ሁሉም ሴቶች በመሆናቸው ምክንያት ትዳራቸው ሊፋቱ ችለዋል፡፡ ከኢኮኖሚ አንፃር ስንመለከት አባቷ በወቅቱ ባለ ሀብት ሲሆኑ እናቷም ከእናቷ

በወረሱት ውርስ መሰረት የሚተዳደሩበት ጠጅ ቤት አላቸው፡፡ እናትና አባቷ ከተፋቱ በኋላ ሁለቱም ያገቡ ሲሆን ወንድ ልጅ መውለድ ችለዋል፡፡ እናቷ ከእናታቸው በወረሱት ጠጅ ቤት በማስቀጠል ይሰሩ ነበር፡፡ የራሳቸው የሆነ የገቢ ምንጭ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ልጆችን ማሳደግ ሐላፊነት የወሰዱት አባትየው ነበሩ፡፡

**ፀሀይ ይትባረክ**

በእናቷም ሆነ እንዲሁም በአባቷ በኩል የሚገኙት አያቶቿ ካህንና የካህን ዘሮች ናቸው፡፡ አባቷ መምህሬ ይትባረክ ተገኝ በድቁና በነበሩበት ወቅት እናቷን ወ/ሮ አበራሽ ገብረ ሥላሴን አገቡ፡፡ ሁለቱም ሲጋቡ ወጣቶች ነበሩ፡፡ በተለይ እናቷ በአስራ ሰባት ዓመቷ ነው ያገቡት፡፡ በትዳር ዘመናቸው አምስት ልጅ አፍርተዋል፡፡ አቶ ይትባረክ ፀሐይን ከወለዱ ከስድስት ወር በኋላ በሞት ተለዩ፡፡ የልጆችን የማሳደግ ሐላፊነት የወደቀው እናታቸው ላይ ሲሆን በወቅቱ የሚተዳደሩት የእርሻ መሬት ስለነበራቸው ከእርሱ የሚገኘው ምርት ተሸጦ ከሚገኘው ገቢ የሚበቃ ባለመሆኑ ጨው በኩንታል እየገዙ ለነጋዴ እና ለቸርቻሪ ያስረክቡ ነበር፡፡ የወንዱንም ሴቱን የሥራ ድርሻ በመወጣት ልጆቻቸውን አሳድገዋል፡፡ በተለይ የልጆችን አስተዳደግ የሚፈጥረውን የስነ ልቦና ጫና ለመቅረፍ በማሰብ ልጆቼን የእንጀራ አባት ፊት አላሳይም በማለት ሌላ ባል ሳያገቡ ቀርተው፡፡ ልጆቻቸውን በሥነ ምግባር አንፀው አሳድገዋል፡፡

**ዶ/ር ትግስት ግርማ**

የትግስት ቤተሰቦች አባቷ መቶ አለቃ ሲሆኑ አባቷ አራት ወንድሞችና አንድ እህት ሲኖራቸው ቤተሰባቸው በፋሽት ኢጣሊያን ወረራ ጊዜ ተገድለውባቸው ብቻቸውን ነው ያደጉት፡፡ በእናቷም በኩል ሶስት እህትና አንድ ወንድም አላቸው፡፡ እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነትም የጠበቀ ነው፡፡ እናቷ በወጣትነታቸው ነርስ መሆን ፍላጎት ቢኖራቸውም አባታቸው ትምህርት አስቁመው ዳራቸው፡፡ ስለዚህ ሴት ልጆቻቸው ሐኪም እንዲሆኑ ይመኙ ነበር፡፡ በኢኮኖሚ ደረጃ የእናቷ አባት ለቤተመንግስት ሰው ቅርበት ስላላቸውና አባቷም መቶ አለቃ በመሆናቸው ደህና ቤተሰብ ቤተሰብ መሆናቸው እርግጥ ነው፡፡ የትግስት ልጆችን በማስተማር የሚያምኑ ቤተሰብ ነው ያላት፡፡ በተለይ በትምህርት ጎበዝ ለሚሆን ልጆች ደግሞ አስፈላጊውን ነገር ያሟላሉ፡፡

የግለ ባለታሪኮች ቤተሰብ ሁኔታዎች ስንመለከት ልጆቻቸውን ለማሳደግ በኢኮኖሚ እጦት ሲቸገሩ አንመለከትም፡፡ የአኗኗር ዘይቤአቸው ቢለያይም ከባለ ታሪኮቹ ወላጆች የመጡበትን

ማህበረሰብ ስንመለከት በስርአት እና በባህል ማደጋቸውን እንመለከታለን፡፡ የሶስቱም ሴቶች እህቶችና ወንድሞች አላቸው፡፡ ይህ የሚያመሳስላቸው ነው፡፡

የሴቶቹ ቤተሰቦችን ሥራ፣ አመለካካት፣ አኗኗር ዘይቤ፣ የትውልድ ቦታ ሲለያይ እንመለከታለን፡፡ በተለይ ከመጡበትና ማህበረሰብ እና ቤተሰብ አንፃር እናቶቹ ጋር ለሴት ልጆቻቸው ያላቸውን አስተሳሰብ ሲመሳሰል እንመለከታል፡፡

የውብ ድንብር በልጅነቷ ባል ሲመጣላት እናቷ ደስተኛ ነበሩ፡፡ እሳቸው በልጅነታቸው ስላገቡ ልጃቸውን በልጅነት ድረዋት ቤተሰብ እንድትመሰርት ይፈልጋሉ፡፡

> እሁድ እሁድ ሽማግሌ ተቀብላ ማነጋጋር የዘውትር ተግባሯ እየሆነ መጥቷል፡፡ ቤት አጽዱ ሽማግሌ ሊመጣ ይችላል በማለት ትዕዛዝ ትሰጣለች፡፡ እናቴ ከዚህ በፊት በሽማግሌዎች የወደፊት ጋብቻ ጠያቂዎች ቢኖሩም ይህ ጋብቻ እንዲያመልጠኝ አልፈለገችም እሺ እንድል አጥብቃ ለመነችኝ ለማሳመን ካቀረበችው ምክንያት አንዱ እነርሱ ሶዶ ጉራጌዎች፣ እኛም ሶዶ ጉራጌዎች ነን፡፡ በሀብትም ተመጣጣኝ ነን እነርሱ ቤተሰብ አንድ ድሃ አለ እኛም ቤት አንድ አለች ብላ ብትለምነኝ እሺ ማለት አልቻልኩም፡፡(የውብ ድንበር፣76)

በተመሳሳይ የፀሐይ እናትም ሴት ልጆቻቸውን በልጅነታቸው ድረዋል፡፡ ለፀሐይ በልጅነቷ የመጣላትን ባል ሲቃወሙ አናይም (ኂላም በተደረገባቸው ጫና ሀሳባቸውን ቢቀይሩም) የትግስት እናትም ራሳቸው መሆን የሚፈልጉትን የሕይወት መስክ ልጃቸው ላይ ሲያንፀባርቁ ይታያል፡፡ እናታችን በወጣትነት ዘመኗ ነርስ መሆን ፈልጋ አባቷ ትምህርት አስቁመው ስለዳሯት ሴት ልጆችዋ ሐኪም እንዲሆኑ ትመኝ ስለነበረ ከቴአትርና ከሥነ ጽሁፍ እንድርቅ አጥብቃ ትከታተለኝ ነበር፡፡ (ትሙት፤76)ምን አልባት ትግስት እናትየዋ ለጥበብ ያላትን ተሰጥኦ ባይከለክሏት ኖሮ የተዋጣላት ተዋንያን፣ፀሀፊ ተውኔት አልያም ደራሲ ትሆን ነበር፡፡ ግን እናቷ እንድትሆን የሚፈልጉትን ሆናለች፡፡ በዚህም የቤተሰብ ተፅዕኖ በልጆች ላይ ከፍተኛ ነው፡፡

## 3.6. ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ቅርርብ

በግለ ታሪክ አፃፃፍ ልማድ ከዋናው ባለ ታሪክ ውጭ ሌሎች ሰዎች ወይም ታሪኮች ከባለ ታሪኩ ጋር ባላቸው ቅርበትና አግባብ መሰረት ይጠቀሳሉ፡፡(ዘሪሁን፤65) ይህንን መሰረት አድርገን በሴቶቹ ግለታሪክ ውስጥ በመነሳትና በመውደቃቸውም፤ የሕይወት አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ

ያደረጉ ግለሰቦች እና አጋጣሚዎች እና ከግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጋር የነበረውን ቅርርብና ወዳጅነት ይተነተናል፡፡

## የውብ ድንበርና ተካልኝ

የውብ ድንበር ወደ አባቷ ሄዳ ትምህርቷን ለመከታታል ብትፈልግም በእንጀራ እናቷ እቢተኝነት ምክንያት ከድሬደዋ በመቅረት የወላጅ እናቷ ጋር ወደ አሰላ በመምጣት ትምህርቷን መከታታል ጀመረች፡፡ በልጅነቷ ብዙ አፍቃሪ እና ልጃችሁን ለልጃችን የሚል ጠያቂ በሚበዛበት ወቅት በአባቷ እቢተኝነት ትምህርቷን ብትቀጥልም የሚቀርብላት የፍቅር ጥያቄዎች ግን አልቀረላትም ነበር፡፡ ከአፍቃሪዎቿ አንዱ ተካልኝን ነበር፡፡ ተካልኝ ወደ አሰላ የመጣው በትምህረት ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን የውብ ድንበር በማፍቀሩ የተነሳ የፍቅር ደብዳቤዎች፣ የፍቅር ግጥም እየፃፈ ይሰጣት ነበር፡፡ ፍቅሬን ይገልጽልኛል የሚለውን የዘፈን ካሴት እየገዛ ይሰጣት ነበር፡፡ በጣም ስለሚያፈቅራት እሱን ካላገባች እሷንም ያገባቻውንም ራሱን እንደሚጠፋ ይዝትባታል፡፡ በዚህ ሁኔታ እያሉ ነበር በህብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ ሲመጣ ከአስረኛ ክፍል ያሉ ጀምሮ ሲዘመቱ እርሱም የመዝመት እጣ ደረሰው፡፡ ዘምቶም ደብዳቤ ይጽፋላት ነበር፡፡ የውብ ድንበር ምንም ምላሽ አትሰጥም፡፡ ከዘመቻ በኂላ ወደ አሰላ በመመለሱ ለእሷ ያለው የፍቅር ስሜቱ አይሎበት ቀንም ማታም እርሷን መከታተል ጀመረ፡፡ ከሚያናግራትና ከእርሷ ጋር ቅርርብ ከሚፈልግ ሰው ጋርም ይጣላ ነበር፡፡ ጓደኛዋ የሃብታም ልጅ እጮኛ በመያዟ እሷም የሚከታተላትን ሰው እልባት ለመስጠት ስትል ፍቅረኛ ያዘች፡፡ ነገር ግን

> እጮኛዬ ብዬ ያቀረብኩትን ሰው ከእነ እንግዳሸት ጋር እየመጣ ቢሸኘኝም ተካልኝ መውጫ መግቢያችንን እየተከታታለ ለእጮኝነት ያቀረብኩትን ሰው አንገቱን አንቆ ወይ ከነፍስ ወይ ከነፍሴ መፍረድ ነው እያለ ሲተናነቀው ፈርቶ ቀረ፡፡( ፀሐይ፣123)

ተካልኝ በዚህ አይነት የፍቅር እያለ ነበር፡፡ አንዴ ሲያስፈራራ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቢለምናት አልፎ አልፎ ሲመታት፣ ሲለማመጣት እያለ ነበር የከተማው ባለስልጣን ሊያገባት የቻለው፡፡ በዚህ ድርጊት ተካልኝ በብስጭት ከተማውን ለቆ ለመውጣት ተገዷል፡፡

## የውብ ድንበር እና ሠመረ

ሰመረ የውብ ድንበርን አብሮ አደረጎች ባይሆኑም የውብ ድንበር ሰባተኛ ክፍል ስትደርስ እናቷ ጋር ስለተማረች የጎረቤታሞች ልጆች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤት እና የክፍል ደረጃቸው ተመሳሳይ ስለነበረ ያስጠናትም ነበር፡፡ በዚህ የተጀመረ ቅርርብ ገና ሰባተኛ ክፍል እያሉ ያፈቅራት ነበር፡፡ የሰመረ እናት ደግሞ ለልጃቸው ሚስት የምትሆን ልጅ ያሳድጉለት ነበር፡፡ የሰመረ ልብ ግን ወደ የውብ ድንበር ስለነበረ ልጅቱን እንደማይፈልጋት ተናግሮ ተለያየ፡፡ ሠመረ የውብ ድንበርን

በመውደዱ ብዙ መከራ ደርሶበታል፡፡ በተለይ እናቱ እያሳደጉለት የነበረችውን እጮኛው ትቶ ከልጅነታቸው ጀምረው እያጠኑ ከሚደጋገፉ ጓደኛውን ብሩክ የሚያፈቅራትን ማፍቀሩ ከጓደኞቹ እንዲነጠል አድርጎታል፡፡ ከአስረኛ ክፍል በነርሲግ ለመሰልጠን ወደ ጎንደር ቢሄድም ልቡ ግን ፍቅሩን ከመግለጽ ወደ ኋላ አላለም እዛ ሆኖ ደብዳቤ ይልክላት ነበር፡፡ በሱዳን አድርጎ ወደ አሜሪካ ገባ፡፡ የውብ ድንበር የመጀመሪያውን ትዳሯን ፈታ አዲስ አበባ ብቻዋን ስራ በመስራት ላይ ትገኝ በነበረ ጊዜ በደብዳቤ መገናኘት ቻሉ፡፡ለመጋባት ተስማምተው መፃፃፍ ጀመሩ፡፡ ለአምስት ዓመት ደብዳቤ ይፃፃፉ ነበር፡፡ ነገር ግን የእሷ ፍላጎት እና ውሳኔዋ መኖር የምትፈልገው ኢትዮጵያ ስለሆነ አሜሪካ ለጉብኝት እንጂ ለመኖር እንደማትፈልግ ገለፀችለት፡፡ ሰመረ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ መጀመሪያ ትምህርቱን መጨረስ እንዳለበትና ከሀገር የወጣውም በስደት ስለሆነ ያለው መንግስት ካወደቀ አልያም የውጭ ጉዳይ ካፈቀደለት ወደ ሀገር ቤት መግባት እንደማይችል ቢገልጽላትም ዋናው ምክንያቱ ግን ከሱዳን አብራው የተሰደደች እና በአሜሪካን አገር ሲማር እሷ እየሰራች የምትረዳው ሴት በነበረው የፍቅር ግንኙነት ትዳር ባይመሰርቱም ሁለት ልጅ በማፍራታቸው  የሠመረ እና የውብ ድንበር የፍቅር ግንኙነት ሊቋረጥ ችሏል፡፡

**የውብ ድንበርና ብሩክ**

ብሩክና እና ጓደኞቹ በአካባቢያቸው የሚሰጠው ትምህርት እስከ ስድስተኛ ክፍል በመሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ነበር ወደ አሰላ የመጡት፡፡ የሚኖሩበት ዘመድ ባለመኖራቸው ምክንያት ቤት ተከራይተው ነው የሚማሩት፡፡ የተከራዩት ደግሞ የእነ የውብ ድንበር ቤት ነበር፡፡ የውብ ድንበር በብዙ ወንዶች ተፈቃሪ ልጅ ስለነበረች በብሩክ ዘንድም ተፈቅራለች፡፡ ታዲያ በወቅቱ ደግሞ ተካልኝ ስለሚከታተላት የብሩክ ማፍቀር እንዳይሳካ ስለሚደርግ እያበሳጨው መጣ፡፡ በዚህ የተጀመረ ፀብ በብሩክ ጓደኞችና ተካልኝ ጓደኞች መሀል ቢሆንም ቀጠሮ ተይዞ ለፀብ ቢቀጣጠሩም የእድገት ህብረት የእውቀት ዘመቻ ስራ መጥቶ በታተናቸው፡፡ ሠመረ እና ብሩክ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ በትምህርታቸው እየተፎካከሩ ጓደኛሞች ነገር ግን ሁለቱም አንድ ሰው አፍቅረው ጓደኝነታቸው ቢቋረጥም ከአመታት በኂላ ሁለቱም በአሜሪካ በተለያየ ግዛት ትምህርታቸውን ሲማሩ በደብዳቤ ይገናኙ ነበር፡፡ ሠመረ የውብ ድንበር ከባላ ተፋታ ከእርሱ ጋር እጮኛሞች መሆናቸውን ይነግረዋል፡፡ ብሩክ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሀገር ቤት ከተመለሰ በኂላ ወደ አሰላ በመሄድ እናቷ የት እንዳለች ጠይቆ አድራሻዋን ቢያውቅም አልተገናኙም ነበር፡፡ የሚሰሩበት መስሪያ ቤት አንድ

አካባቢ በመሆኑ መንገድ ላይ በአጋጣሚ ተገናኙ፡፡ ከሠመረ ጋር ያላትን ግንኙነት ግዜው ከመርዘሙ የተነሳ ጋብቻቸውን እንደተወቸው ነገረችው፡፡ የውብ ድንበር እና ብሩክ ከጥቂት ጊዜአት በኋላ ትዳር መስርተው አንድ ሴት ልጅ ቢያፈርሩም ከአመታት በኋላ ትዳራቸው ሊፈርስ ችሏል፡፡

**ፀሐይ እና ሚስስ ሔለን ካስቴል፤**

ፀሐይና ሚስስ ሔለን ካትሪል በማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ክፍል ፋኩሊቲ ዳሬክተር በመሆን የሚሰሩ ሲሆን በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት በመገኘት ስለ ማህበራዊ አገልግሎት ትምህርት ክፍል እንዲያዘነብሉ ገለፃ አደረጉላቸው፡፡ ፀሐይ በትምህርቷ ጎበዝ ብትሆንም ፍላጎቷ የነበረው ማህበረሰቡን ለማገልገል በሚቻልበት የሙያ አይነቶች ላይ ትኩረት ታደርግ ነበር፡፡ እኚህ ታላቅ ሴት ከህልሟ ጋር አገናኛት፡፡ በእቴጌ መነን አስራ ሁለተኛ ክፍል ማትሪክ ብትፈተን ውጤት እንደምታመጣ እያወቀች ለዝንባሌዋ እና ለዓላማ ስታገኝ ከአስራ አንደኛ ክፍል በአሁኑ አጠራር አዲስ አበበባ ዩኒቨርስቲ በመግባት ለሁለት ዓመት በዲፕሎማ በማህራዊ አገልግሎት ዘርፍ ትምህርት ከተመረቀች በኋላም ከአመታት በኋላም በጋራ ለሚሰሩት ስራ ተገናኝተዋል፡፡ በዚህ እንደ መምህር ሳይሆን እንደ ቤተሰብ ይተያዩ ነበር፡፡

**ፀሐይና ሌሎች**

ፀሐይ ያላት ቅርርብነት ከአብሮ አደጎቿ አብሮ አደግ አልማዝ ኃይለ ሥላሴ፣አምሳለ አለሙ፣ አበበች በንቲ ጋር ነው፡፡ በትምህርት ክፍሉ ከሚሰጡት ከመደበኛው እውቀት ውጪ ከማህበረሰቡ ጋር በቅርበት በመሥራት ልምድ እንድያካብቱ ስለሚደረግ አምስት ሴቶች ቤት ተከራይተው በመካከላቸው ምንም አይነት ልዩነት ሳይከሰት ለመኖር በመቻላቸው የነበራቸውን ቅርርብ በማጠናከር ከትምህርት ቤት ውጪም አብሮነታቸው ቀጥሎ ከወጣትነታቸው እስከ እርጅናቸው ድረስ ማስቀጠል ችለዋል፡፡ ፀሐይ ይትባረክና መብርኸቱ ዮሐንስ ትውውቃቸው የሚጀምረው ሁለቱም በዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ አገልግሎት በምርቃታቸው እለት ከፍተኛ ውጤት እንዳላችወ በተገለፀው ጊዜ ነበር፡፡ የሁለቱም ለወጣት ጥፋተኞች አስተዳደር መስሪያቤት ለስልጠና ወደ እንግሊዝ ተልከው በከፍተኛ ውጤት በመኮንንነት ከተመረቁ በኋላ ወደ አገራቸው በመመለስ በወኒህ ቤት አገልግለዋል፡፡ የፆታ ልዩነት ሳይገድባቸው ቤተሰባዊ ግንኙነት መፍጠር ችለዋል፡፡

## ትግስት ግርማ የልጆቿ አባት

ትግስት ለትምህረት በወጣትነቷ ነበር ከሀገር የወጣችው፡፡ በዳካር በምትማርበት ጊዜ ሚማር ሚሼል በማዳጋስካር ከፍተኛነት ከሚሰማቸው ሜርን ከሚባሉ ማህበረሰቦች ዘር ያለው ሲሆን ከእርሷ ጋር በጀመረው ፍቅር ለመጋባት ቢወስኑም እናትየው ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ እንዳውም ሁለቱን በማለያየት በፈረንሳይ ሀገር ሊዮን በሚባል ከተማ እንድሄድ አደረገችው፡፡

> እኔስ ከናቱ ጋር ሳልስማማ እንዴት ልኖር ነው ብዬ ከርሱ ጋር ተለያየሁ፡፡ ይህ ውሳኔ ግን በጣም ጎዳን፡፡ ስለዚህ ፈጽሞ ተለውጬ የሱን ነገር ለመተካት ሌላ አቅጣጫ ያዝኩኝ(ትሙት፣68)

ትግስት በፍቅረኛዋ ባሳደረባት የስሜት መጎዳት ምክንያት የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ትገባለች ለዚህም የሕይወቷ አቅጣጫ ሲቀየር እንመለከታል፡፡ በነበራት እንቅስቃሴ ውስጥ መንግስትን ተቋውሞ ውስጥ ተሳታፊ ነበረች፡፡ በዚህ ድርጊቷ ከትምህርት ቤት ለመባረር የሚያበቃት ቢሆንም ጎበዝ ተማሪ ስለነበረች ድጋሚ እንዳትሳተፍ በማስጠንቀቅ ልትታለፍ ችላለች፡፡ ሌላው ትግስትን የሕይወቷን መስመር ካስቀየሯት አጋጣሚዎች አንዱ ብሩዲያዊው ባለቤቷ የባህል ተፅዕኖ ምክንያት ነው፡፡ ሴቶች ተማሩም አልተማሩም ሁሌ ጊዜ የባላቸው ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡ በብሩንዲ የቤተሰብ ኃላፊነት በተመለከተ ከወንዶች ይልቅ በሴቷ ብቻ የተተወ ነው፡፡ ወንድ ለቤተሰቡ ከሚጠበቅበት ገቢ ምንጭ ከማቅረብ ውጪ ልጆች አስተዳደግ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደ አብዛኛው አፍሪካ አገራት የሴቶች ተግባር ሆኖ ይታያል፡፡ ሌላው አጋጣሚ ደግሞ የሌላ ዜጋ ስለሆነች ብቻ የዩኒቨርስቲ መምህርነት በመከልከሏ የሕይወት አቅጣጫዋን እንድትቀይር አድርጓታል፡፡

ባለ ታሪኮቹን ስንመለከት የግለ ታሪክ ይዘት ማተኩሪያ ከሆኑት ነጥቦች አንዱ በሕይወት ታሪክ ውስጥ በመነሳትና በመውደቅ የሕይወት አቅጣጫ እንዲለውጡ ያደረጉት ግለሰቦችና አጋጣሚዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡( ዘሪሁን ፣176) በሴቶቹ ግለ ታሪክ ስንመለከት ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ባላቸው ቅርብርብ እና ያጋጠማቸው አጋጣሚዎች በሙሉ ሆነ በከፊል የሕይወት አቅጣጫዎቻቸውን ሲያስለውጣቸው እንመለከታለን፡፡ የውብ ድንበር የፍቅር ሕይወት በአፍቃሪዎቿ ብዛት ሳታፈቅር፣ የምትመኘው የምትወደው፣የምትሳሳለች፣ ሕይወቷን የምትሰጠው ፍቅር ሰጥታ ፍቅር ስትቀበል አንመለከትም፡፡ የእኔ ሆኚ በሚሉ ወንዶች ፍላጎት እንጂ የራሷ የፍቅር ሕይወት የላትም፡፡ ፀሐይ በልጅነቷ የሚስስ ብሩንስኪ አስተዋጽኦ እና

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለች ያጋጠሟት ሚስስ ሔለን መሆን የምትፈልገውን እንድትሆን አግዘዋታል። በተለይ የትምህርቱ አሰጣጥ ከቲዎሪ ተግባርም ስለነበረው የግል ባህሪን ታጋሽነት፣በንግግር ማመን፣ ሰውን ማክበር እና ለለውጥ ሁል ጊዜ መትጋትን ቀርፆ ከማውጣት አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ መኖሩን እንመለከታለን። በተለይ ለመሰረተችው ቤተሰብ በልጆች አስተዳደግ ላይም የራሷን አሻራ እንድታኖር አድርጓታል። ትግስትን ስናይ የባህል ተጽኖዎች ምክንያት የነበራት አቅም፣ችሎታ፣እውቀት በመጠቀም አለማቀፋዊ እውቅና እንድታገኝ ረድቷታል። ትግስት ከግለሰቦች ጋር ያላትን ቅርርብ ስንመለከት ከግለሰቦች ይልቅ ቡድኖች ላይ ያተኩራል።

## 3.7 እናትነት በግለ ታሪኮች ውስጥ

የግለ ታሪኮቹ ከእናትነት ሚና አንፃር እንደሚከተለው በትንታኔ ቀርቧል።

**ፀሐይ ይትባረክ**

በወታደራዊ ደርግ ሀገሪቱን በሚመራበት ጊዜ የወንዶች ልጆቷ የወደፊት ሁኔታዎች በጣም ያሰሳስባት ነበር። ምክንያቱ ደግሞ በወቅቱ የነበረው መንግስት ወንድ ወጣቶችን ያለፍላጎታቸው በውትድርና በመመልመል ለጦርነት የሚያሰልፍበት ጊዜ ነበር። የመጀመሪያ ልጇ ደግሞ እድሜው አስራ አራት ዓመት ሲሆነው ቁመቱ ደግሞ የሃያ ዓመት ያስመስለው ነበር። ታዲያ የወቅቱ ፖለቲካ ሁሉ ነገር ወደ ጦር ግንባር ስለነበረም በቀበሌ ውስጥ ከባድ ሥራ ያሰሯቸው ነበር። ልጆችን ወደውጭ ሀገር ወስዶ ማስተማር የገንዘብ አቅም እርሷም ሆነ ባለቤቷ አቅም አልነበራቸውም። ከዚያ በመነሳት ወደ ጦር ግንባር ሲላክ እድሜው እንዳልደረሰ በብዙ ውጣ ውረዶች በማሳመን ከሀገር ውጪ ሄዶ እንዲማር የአለቃዋ ሚና ከፍተኛ ነበር። ልጆች ወደ ሀገር ከወጡ በኋላ እናትም የተሻለ ሥራ ለመስራት ልጆችን ለማስተማር ሲባል እናት ወደ እስያ አባት ሀገር ውስጥ በመቅረት ኑሮአቸውን ጀመሩ። የፀሐይ ባለቤት ከሀገር ውጪ መኖር የማይፈልጉ በመሆናቸው ከሁለት አንዱን መምረጥ ስለነበረባቸው በስደት ልጆችን ማስተማር ላይ ትኩረት አደረጉ። እናት የምትኖረው ለልጇ ነው። ልጅን ከማሳደግ አንጻር እናቶች ልጆቻቻውን ብቻቸውን ተንከባክበው የሚያሳድጉና የሚመሩ ናቸው።

> በሕይወት መንገድ ላይ ካሳለፍኳቸው ፈተናዎች ሁሉ እጅግ ከባዱ አራት ልጆቼን በአብዛኛው ለብቻዬ የማሳደጉ ሂደት ነው። ሥራ ተመድቤ ወደ ፓፓዋ ጊኒ ስሄድ፣ ባለቤቴ እዚሁ ቀርቶ ቤቱን ለማስተዳደር ወሰነ። ልጆቼን በኢትዮጵያ ውስጥ

> ለመተው ግን ጊዜው አስተማማኝ አልነበረም። ፓፓዋ ኒው ጊኒ ደግሞ፣ ለሁለቱ ትላላቅ ልጆች አደገኛ ነበር። እናም አንድም የማውቀው ሰው ወደ ሌለበት ህንድ አገር የሚገኝ አዳሪ ትምህርት መላክ ነበረብኝ። እንደ እናት ልጆቼን ራቅ ወዳለ አገር ለብቻቸው መላክ በጣም ከባድ ነበር። በፓፓዋ ጊኒ አጠገቤ ሆነው ከአደጋ እንዲጠበቁ ለማድረግም በቂ ገንዘብ አልነበረኝም። የልጆቼ ደህንነት ለእኔ ትልቁ ጉዳዬ ነውና በኂላ ኒውዮርክ ሳለሁ በታመምኩ ጊዜም ያሳሰበኝ የልጆቼ ነገር ነበር። እኔ በሕይወት ከሌለሁ ልጆቼን ምን ይውጣቸው እያልኩኝ ተጨነኩኝ። (ፀሐይ፤135)

ፀሐይ በተለይ ለልጆቿ በጣም የምትሳሳ፣ ሩሩ፣ መስዋት ለመክፈል እናት ከራሷ ሕመምና ስቃይ ለልጆቿ የምታስብ እናት ናት። በመሆኑም የሰው ልጅ በተለይ ሴቶች እናት ከሆኑ በኂላ ለልጆቻቸው ያላቸውን ስሜት እና ፍቅር እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ እንደሚከተል ነው። በተለይ ባለ ታሪካችን ታማ አልጋ ላይ በነበረችበት ጊዜ ከእራሷ ሕመምና ስቃይ የበለጠ የሚያስጨንቃት የነበረው የልጆቿ ጉዳይ ነው።

*ዶ/ር ትግስት ግርማ*

ትግስት ባለቤቷ በሞት ከተለየችው በኂላ ሁቱንም ሴት ልጆቿን ማሳደግ ጫንቃዋ ላይ ወደቀ። የባለቤቷ ዘመዶች ባለቤቷ ከሞተ ከሁለት ሳምንት በኂላ የቤቱን እቃ ለመከፋፈል ስለወሰኑ በሀዘኑ ጊዜ ለእርሷ እና ለልጆቿ ምንም አይነት የገንዘብና የሞራል እርዳታ ስላላደረጉላት የንብረቶቹ ወራሾች እርሷ እና ልጆቿ መሆናቸውን በፍርድ ቤት አስመስክራ ነገር ግን ከልጆቿ ውጪ ሌሎች ንብረት እንደማትፈልግ አሳውቃ ንብረቱን ለዘመዶች አከፋፈለች። በተለይ ሁለቱም ሴቶች በመሆናቸው እና ከሀገሯ ውጪ ማንም የቤተሰብ ሆነ የዘመድ እርዳታ ማግኘት በማትችልበት ወቅት ልጆችን ለማሳደግ ኃላፊነቱን ወሰደች። ለልጆቿ ስትል "እኔ የትም ሄጄ እሰራለሁኝ። ሁለት ሕፃናት ልጆቼ ብቻዬን ማሳደግ አለብኝ" በሚለው እምነቷ እና የእናትነት ፍቅሯ ለልጆቿ መስዋትነትን ለመክፈል ቁርጠኝቷን እንመለከታለን። እናትነት የቤተሰብ የጋራ ኃላፊነት የሆነውን ልጅ የማሳደግ ጫናን ወደ ራስ የመውሰድ ድፍረት ነው። እናትነት የጠነከረ ምሰሶነት ነው።(እናት፤19) በሀገራችን አባባል ጎሽ ለልጆቿ ስትል ተወጋች እንደሚባለው ትግስት ልጆቿን ለማሳደግ ከባድ የሚባሉ ውሳኔዎችን እና ችግሮችን ፊት ለፊት ለመግጠም አቅም እንዳላት እንመለከታለን።

ትግስት ጋቦን በስራ በነበረችበት ወቅት የኮንጎ ብራዛቪል ጦርነት ተባባሰ። እንዲህ አይነት ጦርነት በአፍሪካ ሲነሳ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና ዲፕሎማቶች እና ሌላ አገር ዜግነት ያላቸው ሰዎች በፍጥነት ጦርነቱ ከተነሳበት ሀገር እንዲወጡ ይደረጋል። የኮንጎ ብራዛቪን ጦርነት የተከሰተው ደግሞ ትግስት ልጆቿን ጥላ ለስራ ከሀገር ውጪ በነበረችበት ወቅት ነበር። የሌሎችን ነፍስ ለማዳን በምትሰራበት ወቅትም የሯን ልጆች የምታጣባቸው ክስቶች የተፈጠረ ቢሆን ውጤቱ ደግሞ በተቃራው ስለነበረ ከሞት ሊያመልጡ ችለዋል። ነገር ግን ይህ ድርጊት ትግስት የመጀመሪያ ልጇ ትምህርት ላይ ተጽኖ ነበረው። ነገር ግን በእናቷ ብርታት እና ለልጆቿ በከፈለችው መስዋትነት ይህንን የሕይወት ትግል ሲያልፉ ይታያል።

> በተለይ እኔ ባለመኖሬ ዋና ዋና ወረቀቶችና ባለማውጣቴ የመጀመሪያው ልጄ ሕሊናን የማስገባበት ትምህርት ቤት አጣሁ። በመጨረሻም አሜሪካ አገር ወስጄ ከርስዋ ጋር ቁጭ ብዬ ስድስተኛ ክፍል ማለፊያ ፈተና አስጠርቼ ስለአለፈች ቺካጎ አጠገብ ባለ አዳሪ ትምህርት ቤት አስገብቼ ለአንድ ዓመት እዛ እንድትማር አድርጌ የትምህርት ሬከርድ እንድታገኝ አደረኩኝ። ይኼ ጨርሶ ቀላል ጉዳይ አልነበረም። የልጄ እድሜ በዚያን ጊዜ 13 ዓመት ነው። መጥፎ ጊዜ ነው። በዚህ ዕድሜዋ እርሷን አሜሪካ ወስዶ አዳሪ ቤት ማስገባት ግድ ባይሆንብን ኖሮ መቼም የማላደርገው ድርጊት ነበር።(ትሙት፣116)

> ሁለቱም ሴት ልጆቼን እንደማንኛውም እናት ከራሴ አብልጬ ነው የምወዳቸው። በራሴ ሕይወት ላይም በነርሱ ላይም ጉዳት እንዳይደርስባቸው ስል ብዙ መስዋትነት ከፍያለሁኝ። ትልቋ ልጄ ሕሊና በአባቷ ሞት ምክንያት ስለተጎዳች ብዙ ፍቅር ትፈልግ ነበር። ስለዚህ የበለጠ ጊዜዬን በእርስዋ ላይ አጥፍቻለሁኝ። ልጆቼ የሴት ልጅ እንዳይባሉም በተቻለኝ መጠን በሥርአት እንዲያድጉ አድርጌለሁኝ። የአባታቸውን ባህልና ቋንቋ ስላልተማሩ በሰው አገር አማረኛ ቋንቋ የኢትዮጵያን ባህል አስተምራቸዋለሁኝ። (185)

ትግስት ልጆቿን ለማሳደግ ብዙ መስዋትነት ከፍላለች። በተለይ በሀገራችን አንድን ሰው የሴት ልጅ ተብሎ መሰደብ የተለመደ ነው (ስድቡን ብዙም ባልደግፈውም)። ትርጉሙ ደግሞ ፈሪነት፣ አለመቻል እና ደካማነትን ለማሳየት ተደርጎ ይተረጎማል። ነገር ግን አሁን አሁን ግን የሴት ልጅ የሚባለው አባባል ካለመቻል ጋር ሳይሆን እንደ ጀግንነት ሲጠቀስ እየተመለከትን ነው። ኤፍሬም ግጥም ላይ እንደሚለው "የሴት ልጅ ነኝ ብለህ የሴት ልጅ መባልን ክብር

አድርግላት" በማለት ማህበረሰቡን ሲማፀን እንመለከታን፡፡ በዚህም እሳቤ የሴት ልጅ ነኝ የሚሉ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ግለሰቦች በአደባባይ ላይ ሲናገሩ እየሰማን እንገኛለን፡፡

**የውብ ድንብር**

የውብ ድንበር የመጀመሪያ ትዳሯን ለመመስረት ያበቃት ልጅ በሆዳ በመያዟ ምክንያት ነበር፡፡ ታዲያ ከጓደኝነት ወደ ትዳር ያደገው የብዙአየሁና የውብ ድንበር ግንኙነት ረጅም እድሜ አላስቆጠረም፡፡ ትዳሩ ከፈረሰ በኋላ እናት ልጇን ለእናቷ ሰጥታ ወደ ከአዲስ አበባ ብትመጣም ልጅ ከአያቷ ብዙም ሳትቆይ ወደ አባቷ ተወሰደች ይህ ክስተት ደግሞ የውብ ድንበር ልጇን በፈለገችው በናፈቀች ጊዜ ለማየትና ለመጠየቅ አቃታት፡፡ ስለዚህ የግድ አሰላ እየተገኘች ወደ ትምህርት ቤት ስትገባ እና ስትወጣ በመጠበቅ  ብቻ ትጠይቃት ነበር፡፡ ይህም ቀላል አልነበረም ምክንያቱም ባሏ ባለው ኃላፊነት ከፍተኛ ስለነበረ እና ከቤተሰቡ የባሏ ደጋፊዎች ስለነበሩ ነው፡፡

> ከአባቴ ጋር ትዳሬን አልፈልግም በማለቴ ለሰባት ዓመት ያልተገናኘን ሲሆን ልጄን እናቴ ቤት አሰላ አስቀምጬ ብመጣም ነጥቆ ስለወሰዳት እሷን ለማየት አሰላ እየሄድኩ እናቴ ቤት ሆኜ የምትማርበት ትምህርት ቤት ሄጄ ስጠይቃት ልጅቷን ልትወስድ መጣች ይባልና ወዲያው ትምህርት ቤት ድረስ ወታደሮች ይመጣሉ፡፡ ጎረቤቶቹ ከትምህርት ቤት አጠገብ ስለነበሩ ወታደሮቹ እና በእኔ መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ጣልቃ በመግባት በገዛ ልጇ እናንተ ምድናችሁ በማለት ምላሽ በመስጠት ልጄን እንደፈለኩኝ ጠይቄ ሲበቃኝ ጎረቤቶች አጅበውኝ እናቴ ቤት ያደርሱኛል፡፡(የውብ ድንበር፣176)

የባለታሪኮቹን ሴቶች ከእናትነት ስዕብናቸው አንፃር ለልጆቻቸው ያለውም አመለካካት ስንመለከት ለልጆቻቸው ጥበቃ የማይለያቸው እናቶች መሪ እና ዋና ግብ መልካም ወደ ሆነው አደጋ አልባ ተምኔታዊ መልካም ሕይወት ላይ ለማድረስ ነው፡፡ እናት ያለማንም ድጋፍ ልጆቿን ምንም ሳይጎድልባት በሥነ ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ በማድረግ ሚናዋን በሚገባ በመወጣት ያሳደገቻቸው፡፡ በልጆቿ የእናታቸውን ጥንካሬና ታታሪነት እያዩ ስላደጉ በራሳቸው የሚተማመኑ ልጆች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ እናት ለልጆቿ የመጀመሪያ የሕይወት ተምሳሌት ነች፡፡

**የባህርይውርሶች**

ዶክተር ይሁኔ አየለ እናት በሚለው መጽሀፍታቸው ላይ እናቶች ለልጆቻቸው ባህሪ የመጀመሪያው ቀራጭ ናቸው ይላሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ ሲያስረዱ በሀገራን የልጆችን ባህርያት ቀራፂ እናት ለመሆኗ በ19ኛ ምዕተ ዓለም መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ፈረንሳዊው አገር አሳሽ አርኖ- ሚሼል ዳባዲ፤በኢትዮጵያውያን ላይ የምናየው ዋና ዋና መገለጫዎች የሚቀሰሙት ከእናቶቻቸው ነው፡፡ ዘዴና ብልሃት፣ መለይነትና ርህራሔ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በተቃራኒው መናኛነታቸውንና ተንኮልንም፡፡ ሽማግሌዎችንና ካህናትን ስለምታከብር ልጆቿን ትህትና ተላብሰው ያድጋሉ፡፡ ባሏን አንተ አትልም፡፡ ሁሌ አንቱ ነው፡፡ ጌቶች እያለች ነው የምትጠራው፡፡ መከባበርንና ትህትናን ከዚህ ይማራሉ፡፡ ልጆቿን ስታናግር በማቆላመጥና በፍቅር ነው፡፡ በማለት ይገልፃሉ ይሉናል፡፡ አገር አሳሹ በትዝብቱ እንደሚነግረን የአገራችን እናቶች ሁለንተናዊ ቀራፂ መሆናቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያን እናቶች ታላቅ አስተማሪዎች መሆናቸው መስክሮላቸዋል፡፡ (እናት፤22)ታዲያ ይህ ግለሰብ ስለ ሀገራችን እናቶች የተናገረው ሀሳብ እውነት ነው፡፡ በሴቶቹ ግለ ታሪክ ውስጥ የምናገኘው እውነት በሕይወት ዘመናቸው ለቤተሰቦቻቸው እና ለልጆቻቸው መክፈል ያለባቸውን መስዋትነት ሲከፍሉ ይታያል፡፡ እንደ እናት ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ ለልጆቻቸው መስዋትነት ሲከፍሉ እናያለን፡፡ እድሜአቸውን እውቀታቸውን፣ ጊዜአቸውን፣ ሕይወታቸውን ሲገብሩ እናያለን፡፡ ሴቶቹ የሄዱበት የሕይወት መስመር እና የሚያጋጥማቸው ተግዳሮች ድል በማድረግ ለልጆቻቸው የተሻለ እድል በማማቻቸትና የሄዱበትን ጉዞ ጥንካሬአቸውን እንዲመለከቱ እና መንገዳው እንዲቀና አድርገዋል፡፡ በተለይ የመልካም ባህርይ ወራሾች እንዲሆኑ አድርገዋል በዚህም መልካም ስዕብና ያላቸው እና በልጆቻቻው ባህሪያቸው (ስዕብና ) ላይ ታይተዋል፡፡

> ሕሊና የመጀመሪያ ልጄ ከፍተኛ ትምህርቷን በኒው ዮርክ ጨርሳ ማስተርሷን ደግሞ ከማጊል ዩኒቨርስቲ ካናዳ አግኝታ ጥሩ ሥራ እየሰራ ትገኛለች፡፡ ናታሊም እንደ እህቷ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በኒው ዮርክ ጨርሳ እርሷም ጥሩ ስራ ትሠራለች፡፡ ከሁሉም የሚገርመው ግን ሁለቱም ኢትጵያዊ ባህል ማወቃቸው ነው፡፡ (ትሙት፣186)

> በጤናዬ በኩል በየጊዜው መሻሻል ይታይና ይሰማኝም ነበር፡፡ ከብዙ የሥራ ውጣ ውረድና የጤና ችግር በኂላ በሕይወት ቆይቼ ልጆቼ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት ማጠናቀቃቸውን ለመመልከትና በተጨማሪም ትልቁ ልጄ እስክንድር ለአካለ መጠን ደርሶ በኒዮርክ ትዳር ሲመሰርት ለማየት በመቻሌ ተደስቻለሁኝ፡፡( ፀሐይ፣179)

## 3.8 ግለታሪኮች ከእንስታዊ ንድፈ ሀሳብ አንፃር ፍተሻ

እንስታዊ ሴትነት ጽንሰ ሀሳብ ሰፊ የሆነ ጽንሰ ሃሳብና አቀራረብ ያለው ሲሆን ጾታ መሰረት (ሴትነትና ወንድነት)እኩልነት ለማምጣት ያለመ ነው። ቁልፉ ጽንሰ ሀሳቦች ማለትም በእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሚካተቱት አባታዊ ማለትም ወንዶች የመጀመሪያ ረድፍ መያዝ አለባቸው። የሚለው ሃሳብ ነው። ሁለተኛው ቁልፍ ፅንሰ ሃሳብ አንተር ሴክሽንሊቲ( በማህበራዊ መደቦችን መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ መድሎዎች ለመቋቋም መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችል ፅንሰ ሃሳብ ነው።

የሥርአተ ፆታ አፈፃፀም ይህ ቁልፍ ፅንሰ ሃሳብ የጾታ ሚናዎች እና ምንነቶች ሳይሆን ማህበራዊ ሂደቶች የሚፈጥረው ልዩነቶች ነው። የሚል ሃሳብ ያለው እና ሌላኛው የእንስታዊነት ጽንሰ ሀሳብ የወንዶች እይታ የሚባለው ሲሆን በዘመኑ ጥበብ በሥነ - ጽሁፍ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች አንፃር የሚገለጽበትን መንገድ የሚተርክ ጽንሰ ሀሳብ ነው።

አባዊ ጽንሰ ሃሳብ በትሙት ግድ የለም በሚለው ዶ/ር ትግስት ግርማ ግለ ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ከሞት ስለተረፈችና ቤተሰቧ ስለተደሰቱ አሞላቀቋት የቤታቸው አይንም አደረጓት። ወንድ ልጅ ተወለደ። በጣም ቆንጆ ልጅ ሆነ። ቁርጥ አባቱን መሰለ በኢትዮጵያዊያን አስተያየት አባታችን ቆንጆ የሚባል በመሆኑ አዲሱ ልጅ ቆንጆ ሆነ። እየቆየ የትግስት ቤተሰብ ፍቅር ሁሉ ወደ እርሱ ዞረ። ትግስት ተረሳች። በአንድ ጊዜ የቤቱ ዓይን የነበረች ልጅ ከነመኖሯ የሚያስታውሳት ጠፋ እና ትኩረት ወደ ወንድም መንክር ሆነ። ይህ ሁኔታ ለወንድ ከፍ ያለ ቦታ መስጠትን የሚያሳይና የእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ ትኩረት ያደረገበትአባዊ ያለውን መልክ በዶ/ር ትግስት ግርማ ግለታሪክ ውስጥ የሚገኝ ነው። ሌላው የአባዊ ጽንሰ ሃሳብ መገለጫ (አስረጅ) የሆነው ትግስት አራት ዓመት ሲሞላት መንክር ደግሞ ሁለት ዓመት ሲሞላቸው አሁንም ወላጆቻቸው ለመንክር የተለየየ እንክብካቤ ማድረግ ጀምረዋል። ይህ አባዊ ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጽ ጽንሰ ሃሳብ ነው።

አባዊ ሥርአት ወንድ ልጅ ቅድሚያ የሚሰጥ ጽንሰ ሀሳብ  በዶ/ር ትግስት ቤተሰብም ወንድ ልጅ በመወለድ ለእሷ ይሰጧት የነበረው ቦታ እየቀነሰ መምጣቱን ባለ ግለ ታሪኳ ትተርካለች። በዚህ የተነሳ አባዊ ሥርአት ጽንሰ ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ተግባር ይሆናል።እዲሁም ለወንድሟ የሚሰጠውን የነበረውእንክብካቤ የወንድ የበላይነትን የሚንፀባርቅ በመሆኑ

ለወንድሟ መንክር የሚደረገውን የተለየ እንክብካቤ በዶ/ር ትግስት ግርማ ላይ የውስጥ ቅናት ማሳደር እና በጣም በመቅናቷ የተነሳ የወላጆቿን ቀልብ ለመሳብ የተለያዩ ትፋቶችን ለማጥፋት የተያያዘችው፡፡ ቤተሰቦቿ በባሰ ሁኔታ እሷን መቆጣትና መደብደብ ጀመሩ፡፡ ይህ ተግባር የእንስታዊ ፆታ ጽንሰ ሀሳብ ቁልፍ ሃሳቦች አስረጂ ናቸው፡፡ (ትሙት፣21)

ትግስት በባለቤቷጓደኞችይደርስባት የነበረውን ትችት የወንድን የበላይነት የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይ ወንዶች ተሰብስበው በጋራ አጀዳዎች ላይ ውይይት እና ከመዝናናት ውጪ በቤት ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴዎችን የሴቶች ብቻ አድርጎ መውሰድ የሴቶች ግዴታ ተድርጎ ይታያል፡፡ እንደውም ሴቶችን የወንዶች አገልጋይ አድርጎ ይመለከታል፡፡ እንደ አገላላጽ ተቋማዊአለመመጣጠን፡ፓትርያርክነትእንደቤተሰብ፣መንግስት፣ትምህርትእናየስራቦታባሉተቋማት ውስጥተካቷል፡፡ለምሳሌ፣ባህላዊየቤተሰብአወቃቀሮችብዙውንጊዜወንዶችንየቤተሰብአስተዳዳሪአድር ገውያስቀምጣቸዋል፣(Crenshay,1989) በመሆኑም ወንዶች የውጭውን ስራ ሰርተው ለቤተሰቡ መተዳደሪያ ገንዘብ ካመጡ በቂ ነው፡፡ በቤት ውስጥ የሚሰሩ ስራዎችን ላይ መሳተፍ አስፈላጊ አይደለም ከዚህ ጋር በተያያዘ ማህራዊ የጾታ ክፍፍል የሚያሳይ በመሆኑ የሥርአተ ጾታ ማህበራዊ ግንባታ ጽንሰ ሀሳብ ጋር ግንኙነት ያለው በሆኑን ያሳያል፡፡

ትግስት አንድ ቀን ባለቤቴ እንደ ሌሎች ወንዶች እንደ ማይሆን ተስፋ አለኝ፡፡ እያልኩ ኑሮዬን ቀጠልኩ፡፡ ባለቤቷም አብረን እናምሽ ከሚሉ ጓደኞቹ ጋር በየማታው ማምሸት መጠጣት ጀምሮአል፡፡ ከእርሷ ጋር በየቀኑ ንትርክ ሆኗአል፡፡ እንደዚህ እንዲያደርግ ያደረጉት በየቀኑ እየመጡ አንተ ቤት ሚስት ናት ሱሪ የታጠቀችው፡፡ እሷ ናት የምታዝህ አሁንስ አበዛችው ወንድ ሁን እንጂ(ትሙት፣

ከላይ የሚለው አገላለጽ ከእንስታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ቁልፍ ሃሳቦች ጋር የሚገናኝ አባዊያን ጽንሰ ሀሳቡን የሚያንጸብርቅ ሆኖ ይገኛል፡፡

ትግስት ግለ ታሪክ ውስጥ በተለይ የአፍሪካዊያን ባህል ብዙውን ጊዜ ሴትን ወደ ታች ስለሚያደርግና የቤተሰብም ጫና ስላለበት "ከሁለቱ ውጭ የሆነው ሀገር እየኖሩ እየተመላላሱ ዘመድ መጠየቅ ሳይሻል አይቀርም"(ትሙት፣86) የሚለው አገላለጽ ይገኝበታል፡፡ ይህ አገላላጽየሥርዓተ-ፆታ ማህበራዊ ግንባታን ስንመለከት በአንድየተወሰነማህብረሰብውስጥለእያንዳንዱጾታተቀባይነትያለውወይምዓይነተኛባህሪየሚባሉትንየ

ሚገልጹደንቦችእናደረጃዎች፡፡(Butler,2004)በመሆኑን በፓፓኦ ጊኒ ማህብረተሰብ ውስጥ ወንዶች የበላይ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡

በዶ/ር ትግስት ግርማ ግለ ታሪክ ከእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ ጋር የሚያዛመድ ቁልፍ ሃሳብ እንደሚከተለው ተገልፃል፡፡

> "ሴቶች በኑሮ ውስጥ በእውነት ጠንክረው ከታገሱ ሁሌም በመጨረሻ ድል እንደሚያደርጉ ሴት ልጅ ከወንድ እኩል ታግሳ የፈለገችውን ቦታ ለመድረስ እንደምትችል በሕይወት አጋጣሚ ተገንዝቤአለሁ" የሚል አገላላጽ ነው፡፡ ሌላው ከእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ የሚገልፀውና በዶ/ር ትግስት ግርማ ታሪክ ውስጥ የሚከተለው ነው፡፡ "እየቆየሁ ነገሩ ሲገባኝ ወንዶች በሙሉ ማታ እየተገናኙ በቡሩንዲ ቡዥንብራ ከተማ ቢራ መለጋት ነው ሥራቸው ሴቶችም በበኩላቸው እርስ በእርስ እየተገኛኙ በመሃል ልጆች መንጫጫት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በየቤቱ እየዞሩ ስለ ባሎቻቻው ማውራት ነው ሥራቸው፡፡ (ትሙት፣88)

እንደ(Butler) አገላለጽ ሥርአተ ጾታ አፈጻፀም ከውስጣዊወይምቋሚማንነትሳይሆንበተደጋገሚድርጊቶች፣ ባህሪያትእናየማህበረሰብደንቦችየተገነባነገርነው፡፡ በመሆኑም በቡሩንዲ ቡዥንብራ የሚገኙ ሴቶች የተደጋጋሚ ድርጊታቸው ሴቶቹ ለቁም ነገር ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪ ተደርገው አይታዩም፡፡ በመሆኑም ሴቶች ከራሳቸው ይልቅ ስለ ባሎቻቸው ወይም ስለ ወንዶች የሚወሩ ተደርገው ተስለዋል፡፡

> በአፍሪካ የሚገኙ ሴቶች ከሚደርስባቸው የባህል ተጽዕኖ እና ከወንዶች የበላይነት እና የሴቶችን ተገዢነት ነጻ መውጣት የሚችሉት የገጠማቸውን ፈተናዎች ትግል ሕይወታቸውን መለወጥና እና ልጆችም እንዴት እንዳገኘች ያገኘችውም እውቀት ለማግኘት በውጣ ውረድ የተማረችው ማንኛው ሴት ልትሰራው የምትፈልገውን ለማግኘትና በነፃነት ለመኖር መታገልና መልፋት እንዳለባት (ገጽ፣88)

ከላይ በተገለፀው መሰረት ሴት ልጅ መዝናናት ሊኖርባት አይገባም፡፡ የሚል አድማታ ሲኖረው ምክንያቱም ባለታሪክ በነበረችበት ውጭ ሀገር ባልና ሚስቶች በጋራ ሆነው መጠጣጥ እንደ ጥፋት የተቆረበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን ያደገችበት ቦታ ግዜ ከነበረችበት ውጭ ሀገር የተለየ

በመሆኑም የስርአተ ጾታ አፈጻፀም በባህል በሥርአት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ግምት ውስጥ ባለማገባት በግለ ታሪኳ ውስጥ ልታሳይ ችላለች፡፡

የፀሐይ ጉዞ ግለ ታሪክ ውስጥ የእንስታዊ ጽንሰ ሃሳብ ቁልፍ ሃሳብ የሚንፀባረቀው ሃሳብ እንደሚከተለው ይገለፃል፡፡ በወንዶችና ሴቶች ማህበራዊ መስጋብር መፍጠር አለባቸው፡፡ በዚህ ምድር ህይወት ሲጋፋ መተባባር መተጋገዝ ከሌለ የሰው ልጅ ባህርያት ጋር የሚያጋጭ በመሆኑ ወንዶችና ሴቶች በጋራ መማራቸው መበላለጥ ደግ የተፈጥሮ ህግ መሆኑን ተዘንግቶ ማንኛውም ሰው መበለጥን (ሽፈትን) አሜን ብሎ የሚቀበል አይደለም፡፡ ለሽፍትም ሆነ ለመበለጡ ምክንያቶች ያደረድራል፡፡ስለዚህ በሴቶች መበለጥ  ያለ እና የሚኖር ሆኖ ሳለ በፀሐይ ግለ ታሪክ ውስጥ ግን ሰው ለሽንፈቱ የሚለቀምጠውን መከላከያ ሴትን የበታች የማድረግ አድርጋ አቅርባዋለች፡፡ ይህ ደግሞ ሊስተካካል የሚችለው የሥርአተ ፆታ አፈጻፀምን ሰው ግንዛቤእና እውቀት ሊኖረወቅ በመሆኑ መመከት ተችሏል፡፡

> *ወንዶችም ሴቶችም ሆነን ተቀላቅለን ስንማር እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ ከአንደኛው እስከ ሶስተኛ ያለውን ማዕረግ ስናገኝ እንዴት በሴት እንበለጣለን የሚል ቅናት ከወንዶች ተማሪዎች ይታይ ነበር፡፡ በምንማርበት አንደኛ ደረጃ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ወንዶች በሴቶች መበለጥ አይፈልጉም ፡፡ በሴት መበለጥን የተዋረዱ አድርገው ነበር የሚመለከቱት ነበር፡፡* (ፀሐይ፣25)

ሌላው ከእንስታዊ ጽንሰ ሀሳብ ጋር ተዛማጅነት ያለው ገለፃ የባለታሪኳ ወደ አዲስ አበባ ለትምህርት የሄደችበት የነበረ አገላለጽ ነው፡፡ “በነበርበት የእድሜ ክልል በተለይ በሴትነታችን ጋር ተደማምሮ ቤተሰቦቻችን ሃሳብ ቢገባቸው አይገርምም” (ፀሐይ፥ 26) ይህ አገላለጽ ሴት ልጅ በራሷ አቅምና ሁኔታ የሚያጋጥማ አዳዲስ የሕይወት ክስተት በራሷ መወጣ እዳለባትና የእውቀትና የግዛቤ በመሆኑ ከቤተሰብ ተለይታ ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ ቤተሰቿ ሃሳብ እደገናቸው ትተርካለች በመሆኑም ሴትን ህይወትንን መጋፈጥ እዳለበትና የህይወት አፈጻፀሟ ትኩረት ሊደረግበት በሚገባ ስለሆነ የስርአተ ጾጳ አፈጻጸም ጽንሰ ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ሁኔታ አለው፡፡

> *ሥራ ላይ ስመደብ እድሜ በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከእድሜዬ በተጨማሪ ከጾታና ከቁመቴ ማጠር ጋር ተደምሮ በተቀሩት የድርጅቱ ወንድ ሰራተኞች ዘንድ በመጠኑም ቢሆን የማጎረምረም ስሜት መታየቱ አልቀረም ይህ እንዴት ይህችን*

> የመሰለች ወጣት ያውም ሴት እና አለቃ ሆና ትመደባለች በማለት መሆኑ ነው።(ፀሐይ፣74)

የአካል ገጽታ (physical apperance) መስሪያ ቤት ውስጥ ሊኖረው የሚችለውና ሴት መሆኑ ምም አይት ዝምድና የሌለውን እና አንድ ሰው ጥንካሬና ድክመቱን የሚለካው በስራ አፈጻጸም መሆኑ ይገባዋል። የወንድ ፈርጣማ መሆን ዌም ረጅም መሆን በሥራ አፈጻፀም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ነገር ግን በፀሐይ አገላላጽ የአካል ገጽታን ከአፈጻፀም ጋር በሥራ ቦታ የሚሰጠውን ትችትና አስተያየት ለመግልጽ ሞካራለች ይ ደግሞ የወንድ እያታ ጽን ሰ ሃሳብ ተዛማጅነት አለው።

> …….. የነበሩት ታራሚዎች በሙሉ ወንዶች ሲሆን አልፎ አልፎ ወጣት ሴቶች ብቅ ሲሉ ጉዳያቸውን እኔ ነበር ኃላፊነት ወስጄ የምከታታለው። ሴት ወጣቶች ጠቅላላው ወደ ማእከሉ እንደ ወንዶች አልገቡም። እነኝህ ወደ ማዕከሉ የሚመጡትን ወጣት ሴት ታራሚዎች በተመለከተ ጥረት ያደረግ የነበረው በምክር አገልግሎት ላይ ከወላጆቻቻው ጋር በመሆን በጋራ በምናደርገው ጥረት ነው። (ፀሐይ፤ 5)

ይህ አገላለጽ ሴት ልጅ የሕይወት የዕለትተዕለት መስተጋብር ወንጀል ነክ ነገር ውስጥ እዳማትገባ አድርጎ ማስቀመጥ ሴት ልጅ በማህራዊ ኢኮኖሚያዊና ውስጥ ሚና ያላት በመሆኗ ለወንጀል እና ለሕግ ውጭ የሆነ ነገር ውስጥ አትገባም የሚል አገላለጽ ያዘለ በመሆኑ ምንም እንኳ ወንጀል መስራት ትክክል ባይንም የሴቶች ታሪክ መሆን ግን በጣም አስገራሚ እና አደገኛ አድርጎ ማቅረብ ሴቶች ያላቸውን ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሚና የሚያሳንስ በመሆኑ አገላላጽኢንተር ሴክሻሊቲ ነው።

> ወንድ የሥራ ባልደረቦች ሴትን በአለቃነት ለመቀበል ብዙም ፍላጎት እንደሌላቸው ሁሉ በታራሚዎችም ዘንድ አመለካካት ለማየት ችያለሁ ከዚህ በተጨማሪ ጠባያቸው በተበላሸ ወንዶች መካካል እንዴት ለመገመት አደጋ ሊደርስብኝ እንደሚችል በማሰብ ሥራውን ለቅቄ ወደ ሌላ እንድሄድ ምክራቸውን የሚለግሱ የዘመዶችን ቁጥር ብዙ ነበር። (ፀሐይ፣75-76)

ይህ አገላለጽ ሴት ልጅ ሃላፊነትን መሸከም እንደማትችል አድርጎ የሚገነዘበው የማህብረተሰብአመለካካት ማዕበል ሊወስዳት ስለሞከረ ሀላፊነትን መወጣቷ አስገራሚ አድርጋ አቅርባለች ይ ደግሞ አሁንም የወንድን የበላይት የሚቀበለው ማህብረተሰብ አመለካካት ጋር ተዛማጅ የሆነ እሳቤ በመሆኑ አባዊ ስርአቶችን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ያስረዳል።

በእኔ በኩል በወለደችና በልጆች በተለይ በሴት ልጆች መካካል የሚከሰተው ችግር ለመርዳት ተረድቶም መፍትሔ ለመቀየስ ሴት መሆኔ የራሱ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ (ፀሐይ፣77)

ሴት ልጅ በማህረተሰብ በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠር ችግር የመፍታት ግዴታ የሕይወት የእለት ተዕለት ተግባሯ ሆኖ እያለ ችግርን ለመፍታ ወይም መፍትሔ መቀየስ አለባት፡፡ ነገር ግን ሴት ልጅ ችግር መፍታትና መፍትሔ መሻት አትችልም የሚል ዝንባሌ ያው አገላላጽ በመሆኑ ሴት ልጅ የሚኖራት የሥርአተ ጾጣ አፈጻፀም የሚያመለክት አገላላጽ ነው፡፡

በሌላ በኩል ከድጃ የተባለች የአስራ አንድ ዓመት ወጣት በዚሁ ሥራ ላይ እያለሁ ከአጋጠመኝ ወጣት አጥፊዎች አንዷ ነበረች፡፡….. አለባበሷ እንዲሁም የፀጉሯ አሠራር እንደ ወንድ በመሆን ሴትነቷን ለመለየት ያስቸግራል፡፡ ለምን እንደዚህ እንደምታደርግ ስትጠየቅ በጎዳና ላይ የሚሆኑ ወንዶች የሚያደርሱባትን የመደፈር ሙከራ ለመሸሽ እንደሆነ ተናግራለች(81)፡፡

ይህ አገላለጽ አለባባስና የፀጉር ስታይ ወደ ባለቤትና ልምድና መስተጋብር ካው ግለሰብ ጋር ሆኖ ስለ ስታይሎች ላይ አስተያየት መስጠት የወንድ የሴት ብሎ የሚካፈለውን ሥርአት ጾታ ጋር ተዛማጅ የሆነ አገላጽ በመሆኑ ማህብተሰብ ለወንድ የሚሰጠውን ለሴት የሚሰጠውን የማህረተሰብ ክፍፍሎች የሚገልጽ በመሆኑን የአለባባስና የፀጉር እስታይ ለወንዱ መሥጠት ከወንድ እይታ ጽንሰ ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ነው፡፡

ሴተኛ አዳሪነት በግልጽ በህግ እንዲከለከል ስለ ሴተኛ አዳሪነት ያለው ሕግ በቂ ስላልሆነ አንድ የተጠቃለለ ህግ ወጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ሕጉንም የተላለፈው የሚገኙ እድሜአቸው ሃያ አንድ ያልሞላቸው ወጣት ሴቶች ተይዘው ልዩ ልዩ የእጅ ሥራ የሚማሩበትን ድርጅት ህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስተር እንዲቋቋሙ (83)

ይህ አገላለጽይህ አገላላጽ ሰው በፈለገው ሥራ መሰማራት ሕይወትን መግፋት የሚገባው ሰው ወደ ተለያዩ ሕይወት የሚገባው ሕይወት ለመግፋት በመሆኑ ሴተኛ አዳሪነት ለምን ሆኖ ማለትም ሳይሆን ማህረተሰብ ስ አዳሪ ለም ሆኖ ማለት ሳይን ማህረተሰቡ ስለ ሴት ልጅ ያውን አመለካካት ሥራ መፍጠር ያለበት መሆኑ ሲገባ የዚህ አገላላጽ የሥርአተ ጾታ አፈጻፀም ነው፡፡ ምክያቱም ወንዶች ወደ ሴተኛ አዳሪ መሄድ እንደ መብት የሚቆጠር ነው፡፡ ማለት ወንዶች ተጠቃሚ በይሆኑ ሆኖ ሴቶች በዚህ አይት ሥራ ውስጥ ባልተሰማሩ ነበር፡፡

እኔ በተመደብኩበት የሥራ ኃላፊነት ሴት እንዴት የሚለው አመለካካት በተለያዩ መልኩ ይገልጽ ነበር፡፡ ለምሳሌ ስሜ ፀሀይ ሆኖ ከተያዩ መሥሪያ ቤቶች ደብዳቤ ሲጽፍልኝ አቶ ፀሐይ ተብሎ የሚደርሰኝ ጊዜ የነበረ ሲሆን ይህም በመሰሉ ኃላፊነት እንዴት ሴት ልትሆን ትችላላች በሚል በኩል ሴት በመሆኔ አሸነፉኝ...........

በነበርኩበት መስሪያ ቤት ያጋጠመኝን በመሥሪያ ቤታችን ለሰራተኞች ደሞዝ ተጨማሪ ተደረገ፡፡ የተደረገው ጭማሪ በተመሳሳይ የሥራ መደብ በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘመን ከወላጆቼ እኩል ቢኖርም ለሴቶች የተደረገው አነስተኛ ሆነ፡፡ ይህንን በተመለከተ አራት የምንሆንና በተለያየ ምድብ ሥራዎች ላይ የምንሠራ ሴቶች ተሰበሰበን አቤቱታችንን ለማስማት ጉዳዩ የሚመለከተው መሥራቤት ጉዳዩ ከፍተኛ ኀላፊነት ዘንድ ቀረብ፡፡ ጉዳያችንን ያስረዷቸው አለቃ አሁን እናንተ የሚከፈላችሁ መቼ አነሳችሁ የሚያስፈልጋችሁን ባሎቻችሁ ያመጡላችኂል እናንተ ብሎ ደሞዝ ጠያቂ ብለው ተቆጡ፡፡ (ፀሐይ 85)

በማንኛው ሥራ በተሰማሩበት ሙያ ተመጣተን ክፍያ ሊኖረው ግድ ይላል፡፡ ነገር ግ ሴት ስለሆነች በቦጣው( ነበሥራ መደቡ) የጠቀመጠውን ክፍያ ልታገኝ አይገባምብ ብሎ መከራከር ወንዶች የበላይ አድርጎ ማስቀመጥ ነው፡፡ በግለ ታሪክ ውስጥም የአባዊያን ሥረአት ተንፀባርቋ፡፡

በሴቶች በኩል ያለው ሁኔታ ሲታይ እንዲሁም የሰራው ጫና የበዛበት ከድህንነት አረንቋ እነርሱም ሆነ ቤተሰቦቻቸን ሊያቀና ያልቻለ ኑሮ እየጨመሩ መሆኑንም መመልክት ችያለሁ፡፡ ሴቶች በቤት ውስጥ ከቤት ውጭ ጉልህ በሆነ የማምረት ተግባር ላይ ቢሳተፉም ባሎቻቸውም ሆነ አጠቃላይ ህብረተሰቡ ለሚያደርጉት ከፍተኛ የስራ እውቅና የሚሰጥበት አይደለም፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በንብረት ባለቤትነት ላይ ያላቸውን ውሳኝነት ዝቅተኛ መሆኑ ሌላው ቀርቶ ከባሎቻቻው ወይም በአጠቃላይ ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም፡፡ በዚህ መልኩ ሴቶች በውሳኔ ሰጭነት ያላቸውን ሚና ዝቅተኛ መሆኑና በሌሎችም የሕይወት መስተጋብር በሚደርስባቸው ጫና ምክንያት ሊያከናውኑት ከሚችሉት በላይ አስከፊ ኑሮ እየመሩ መሆኑን ለመረዳ የተወሰኑ ተግባሮቻቸውን በመጥቀስንና በመግለጽ ለመረዳት ይቻላል፡፡(ፀሐይ፤88)

ከላይ የጠቀመጠው አገላለጽ የሰው ልጆች እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሴት በመሆኗ ብቻ እኩልንት የሚነፍጉ በመሆን ያለበትም ነገር ግን የባለ ታሪኳ አገላለጽ

የወንድ የበላይነት የሚያሳይ በመሆኑ ይህ አገላለጽ አባዊ ሥረአት ጽን ሰ ሃሳብ ጋር ተዛማጅ ነው፡፡

በፀሐይ ይትባረክ ግለ ታሪክ ውስጥ የወጣቶች ሴቶችና ክርስቲያናዊ ማህበር (ወኬክማ) ለድርጅቱ ይመጥናሉ ተብለው ከተመረጡትና ድርጅት ያቀደውን ሥራ ለማስፈፀም የትምህርት የስራ ልምድ ተመራጭ እንድትሆንና የቀረበላትን ድርጅቱን የመምህርነት ሚና ተቀብላላች የማህበሩን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን የተለያዩ የአሰራር መርሆች ውስጥ ከእንስታዊ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ተዛማጅት የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

> በሴቶችና ልጃገረዶች መካከል እህትማማችነት ስሜትን ይፈጣራል፡፡ በጾታ መካካል እኩልነት የሚኖረው ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ የኢኮኖሚ የባህራዊ የባህልና የፖለቲካ ነፃነትን ያራምዳል፡፡ ከቤተሰብ ተለይተው ለሚኖሩ ሴቶች ልጃገረዶች የመኝታ(ሆስቴት) አገልግሎት በተቻለ መጠን ያዘጋጃል በሴቶችና ልጅገረዶች ላይ የሚካሄደው ማንኛውም አይነት ማህበራዊ ባህላዊ መድሎዎችንና አካላዊ ሥነ ልቦናዊ መጎሳቆልን ለመከላከል የበኩሉን እገዛ ያደርጋል፡፡ በአባልነት በኩል እድሜዋ አስራ ስምንት ዓመት ያላነሰ ምግባር መልካም ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ዜጋ የሆነች ማንኛውም ሴት ወይም ልጃገረድ በማኀበረሰቡ ሕግ ሥነ ስርአት ለመተዳደር ፍቃደኛ ሆነው እስከ ተገኙ ድረስ የማህበሩ ሙሉ አባል ለመሆን ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ከአስራ አራት እስከ  አስራ ስምንት መካከል የሚገኙ ልጃገረዶች ወይም ሴቶች ለወጣት አባልነት መሳተፍ እንዲችሉ መተዳዳሪያ ደንቡ ደንግጓል፡፡ (ፀሔይ፣92)

ከላይ እንደተገለጸው የሰው ልጅ ጾታ ሳይገድበት መስተጋብ የሚፈጥር ሁኔታ እያለ በማብረተሰብ ሂኔታ ባህል ምክንያት በኢኮኖሚና በማህራዊ እና በፖለቲካዊ ሥራ ላይ በእኩል የመሳተፍ የመተግር እድል ሊኖረውይባል፡፡ ይህ ደግሞ በተግባር አለመኖር ባለታሪኳ ታትታለች፡፡ ይህ ደግሞ የሥርአተ ጾታ ማህበራዊ ግንባታ ባለመኖሩ በመሆኑ ይህ አገላጽ የስርአተ ጾታ ማህበራዊ ግንባታ ጋር ተዛማጅት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

> …………የወሊድ ቁጥጥር መድሃኒቶች ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለወንዶችም ያለ መሆኑ ጭምር ይነገራቸዋል፡፡በሴቶቹ በኩል በአብዛኛው የሚነገረን ይህንን ባሎቻችን ብንነግር ፍቃደኛ ስለማይሆኑ ከአገልግሎቱ እንዲጠቀም አያደረግም እንድያውም ወደዚህ ቦታ እንድንመጣ አይፈቅዱልንም በማለት ችግራቸውን ሲገልፁ እንደነበር አስተውያለሁኝ የሚል አገላላጽ ይገኛል፡፡ (112)

ከላይ ያለው አገላላጽ ትዳር ውስጥ መተባባር መተጋጋዝ መወያየት ወሳኝ ተግባር ነው። ባለታሪኳ ከላይ የጠቀሰችው ግን ይህ ማህበራዊ መስተጋብር ተገቢ ተግባርን የሚያንፀባርቅ ሳይሆን አባዊ ሥርአትን የሥርአት ጾታ አፈጻፀም ጽንሰ ሃሳብን የሚገልጽ ሆኖ ይታያል።

> በተሰማራውባቸው ሥራዎች በሴትነቴ ብዙ ችግሮች አጋጥሞኛል ሴት ሆኖ በተለይም በባለሙ መሰረት ብዙ ፈተናዎች አሉት። ብቻዬን ውጭ ሀገር በነበርኩበት ጊዜ ባልሽ የለም ምን አለበት በማለት ሆነ ማስፈራራት በሴትነት ለመጠቀም ሞክሩ አልጠፉም ይህ ሁሉ ተቋቁሞ ለማለፍ መቻል ትልቁ ፈታና ነው። ከተመደብኩበት ከምሰራው ሥራ ይልቅ ሴትነት ጉልቶ የታየበት ጊዜም አጋጥሞኛል። (ፀሐይ፣ 134)

ይህ አገላለጽ ሴትነት የተለያዩ ፈተናዎች ያሉት መሆኑ ቁልፍ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጆች አባዊ ሥርዓት ወይም የወንድ የበላይነት የሚያጎሉ ተጋባራቶች በርካታ በመሆናቸው ነው። በመሆኑም ባለታሪኳ ሴትነትን ና ወንድነትን ክፍፍል በረጅም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ፈታ በመሆኑም የገጠማቸውን የሕይወት ገጠመኞች ወይም ችጋሮች በመፍትሄ የመሆን ነገር መዘየድ ሲገባ ፈተኛዎች ላይ ትኩረት አድርጋለች። በመሆኑም አባዊ ሥርአት፣የሥርዓተ ጦታ ማህራብዊ ግንባታ ጽንሰ ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ነው።ባለታሪኳ በዩኒሴፍ ድርጅት በልማታዊ ዘርፍ ድጋፍ ከተደረገላቸው የእኔም ተሳትፎ ከነበራቸው ድርጅቶች የየትኖራ የገበሬዎች አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበር አንዱ ነው። ማህበሩ 1200 የነበሩ ሲሆን ሴቶቹም 400 ይሆናሉ፥ (136) የሚለው አገላለጽ የማህሩን አባት 1200 ነበሩ ካለች በኋላ የሴቶች ብቻ አህዝ ነጥላ ቸውጣታለች። ሴቶች 400 ነበሩ በማለት ገልጻለች። ሴቶች ማበራዊ ፣ኢኮኖሚያዎ እናፖለቲካዊ አውዶች ላይ ተሳታፊ መሆን እዳባቸው እሙን ነው።ባለታሪኳ ግን 400 ሴቶች ግን የማህር አባላት መሆናቸው ለማጎላት የሚከረችውን አገላላጽ የሥርዓተ ጾታ አፈጸጸም ጽንሰ ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ነው።

> ከዚህ ባሻገር ከሁሉም በላይ የሴት አባላት በሥራ በሚመደቡበት ጊዜ አንዱ ማናቆ የልጆቻቻው ሚያቆዩበት ቦታ ያለመኖር በመሆኑ የዩኒሴፍ መዋለ ህፃናት እንሰራ አድርጓል። ይህ ቀደምት ተቋም አስፈላጊ በመሆኑ መገልገያ እንዲሟላ በማድረግ ህፃናት ያሏቸው የማህበሩ ሴት አባላት ሥራቸውን በሙሉ ተሳትፎ ያለ ሀሳብ እንዲያከናውኑ ትልቅ ሚና ተጫውቷል የሚለው ይገኝበታል። (ፀሐይ፣137)

ቤትና ኑሮን መምራ ማስተዳደር የባልና የሚስት የጋራ ተግባራቸውን ነው፡፡ ነገር ግን የሕጻናት መቆያ እና መዋለ ህጻናት መቋቋሙ ለሁለቱም ያጠቅማል እንጂ ለሴቶች ብቻ ኤደለም በመሆኑም ባታሪኳ በጽሁፍ ውስጥ የሚያመለክተው የሥርአተ ጾታ አፈጻፀም ጽንሰ ሀሳብን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

> ፀሐይ ይትባረክ በፓፓዎ ኒው ጊኒ ያለውን ሁኔታ ከእንስታዊ ጽንሐ ሃሳብ አንጻር የተገለፀበት አግባብ እንደሚከተለው ነው፡፡ ....... በሌላ በኩል በጥቂት የተማሩ ሴቶች የፓርላማ ተመራጮች የሆኑ አሉ፡፡ ከእነዚህ ሴቶች ጋር ለመተዋወቅ በመቻሌ ሴቶች የመሩትን ሕይወት ለመመልከት ችያለሁኝ፡፡ በዚ ጊዜ ሴቶች ሕይወት የሚመለክቱ በመጀመሪያ ሴት ወንድ የበታች እንደሆኑት አምነውና ተቀብለው ነው፡፡ ይህ እምንት እነዚህ ተምረዋል የተባሉ የፓርላማ አባላትና ሌሎች ያጠቃልላል፡፡ በባሎቻቸው ይደበደባሉ የሚደርስባቸውም የጾታ ትንኮሳ አንዳንድ እንደ የሕይወት ትክክለኛ ገጽታ ተቀብለው ኑሮን ይመራሉ፡፡ ፓፓዎ ኒው ጊኒ ከሚታወቅበት አስከፊ ልማድ በአለም ላይ ከሚጋሩ ሀገር ሁሉ ሴቶች ላይ በሚደርሰው ጾታዊ ጥቃት በቡድን ሆነው ሴቶችን የሚደፍሩ ይህ ድርጊታቸው ፓክድ ሬፕ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህም አገራቸው ከዚህም በላይ ቁጥር ያላቸው ወንዶች አንዲት ሴት ይደፈራሉ፡፡ ይህ እንስሳዊ የሆነ ድርጊት በሀገሩ እንደ ልምድ የተወሰደ በመሆኑ ተጠቂዎች ይበዛል ቢባል የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ከመሞከር በስተቀር ፍትህ ለማግኘት ሙከራ ማድረግ ብዙ ያልተለመደ ሲሆን ቢሞከርም ውጤት አይኖረውም ፡፡(ፀሐይ፣ 149)

ከላይ በተገለፀው የተቀሰችው ሀገር የወንድ የበላይነትን ተቀብሎ መኖር የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ከአባዊያን ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብና የሥርዓተ ጾታማህበራዊ ግንባታ ጽንሰ ሀሳብ ጋር ተዛማጅነት ነው፡፡

> በፓፓዎ ኒው ጊኒ ለሥራ በቆየሁበት ጊዜ አብዛኛው ጊዜ የምቀርበው ከሴቶች ጋር ሲሆን ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለኝ ግንኙነት ከሥራ ባላፈ እገታ ነበር፡፡ ሴቶችም ወንዶችን እንደ ልምድ አድርገው ጫት የመሰለ ቅጠል ያመነዥጋሉ.....ከሴቶች ጋር በማደርገው ውይይት ግልጽ ሆነው አግኝቻቸዋልሁኝ፡፡ የተረጋጉ በመሆናቸው የመናደድ ወይም በጣም የመደሰት ስሜት አይታይባቸውም(ፀሐይ፣150)

ማህበራዊ ሕይወት ያለማጋራት አዝማማያ ባለታሪኳ ገልፃለች ፡፡ይህ አገላላጽ የሥርዓ ፆታ ማህራዊ ግንባታ ጽንሰ ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ምክያቱም ሴት በመሆን ብቻ እንደ ባህል የሚቆጠር ተግባር ላይ አተረሳረፍም ማለት የማህበራዊ መስተጋብ ለመፍጠር አስቸጋሪ

ይናል፡፡ ራስን ከተለዩ ማህራዊ ተግባት ፣ግታት የራስ ምርጫ ሆኖ ሳለ ሴቶቹም ወንዶችም በህይወት ተጋባር ውስጥ መገኘታው ሸበማህር እንደ ባህል ላይ ባለ ታሪኳ የገለጸችበት መንገድ የሥርዐተ ፆታ ማህራዊ ግንባታ ጋር ይዛመዳል፡፡

> በፓፓዎ ጊኒ በሰራሁባቸው ጊዜአት በነበረው የወንጀል ብዛትና ዓይነት በተለይም በሴቶች ላይ በሚደርሰው ጾታዊ ጥቃት ምክንያት ነጻነት አይሰማኝም ነበር፡፡(151)

የሴቶች ጾታዊ ጣቃት መንስኤ አባዊ ሥርዓት መስፋፋትና የሥርዓተ ፆታአፈጻፀም ላይ ትኩረት ተደርጎ ባለ መሰረቱ እውቅና ግንዛቤ አለመኖር ነው፡፡ በመሆኑም ባታሪኳ የገለፀችበት መንገድ አባዊ ሥርዓት የሥርዓተ ፆታ አፈጻተም እና የወንድን እንደ ደፋር አድርጎ የሚሳል እያታ ያው ነው፡፡ በመሆኑም የባታሪኳ አባዊ ሥርዓት የሥርዓተ ጾታ አፈጻፀም የሚያሳይ ነው፡፡

> አንዲት ሰራተኛ ሴት ኑሮዋን በስራዋ መደገፍ ሳያንሳት በቤት ውስጥ ረዳትም ቢኖር የቤቱን ሥራ እንድታከናውን ይጠበቅባታል፡፡ ይህ የእኔ ተከታይ በሆነው ትውልድም ተግባራዊ ሆኖ በማየቴ በጾታዊ የስራ ክፍፍል ብዙ መስራት እንዳለበት ለመጠቆም እወዳለሁኝ፡፡ ነገሩ በይበልጥ ለማብራራት አሜሪካን በምሄድባቸው እና በልጆቼ ቤት በማሳልፍባቸው ምክንያት የወንድ ልጆቼ ሚስቶች ከዚሁ የስራ ጫና በመጠኑ የተላቀቁ ቢሆንም ነገሩ በትኩረት ስመለከት አሁንም ማናቸውንም የቤት ሥራ የወንድና የሴት ሳይሉ በእኩል ደረጃ ሁሉንም የሚካፈሉበት ጊዜ ገና አጥጋቢ ውጤትና ደረጃ አማሳየቱ እውን ነው፡፡ ሆኖም አሁን የምንገኝበት ዘመን የሚገኙ ወጣት ወንዶች የሚየሳዩት ጥረት ተስፋ ሰጪ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ (ፀሐይ፣154)

ፀሐይ ከሥራ ከአጋጠማት የሥራ ልምዶች ውስጥ አንዱ በሴቶች ላይ የሚታዩ ጭቆናዎችን ያነሳለች፡፡ በተለይ በአፍጋኒስታል የሚኖረው በሴቶች ላይ የሚታየው ጭቃናን ትተርካች፡፡ እዲሁም የታሪኳ ውስጥ የሚታየው ሴቶችን ወንዶች ፍላጎች ሚሚያ እንጂ የራሷ እውቀት፣ፍልጎት፣ስሜት፣አስተሳሰብ፣ስዕብና ፍልስፍና ያላት እዳለሆነች እና እንደ ቁስ ስትቆተር እንመለከታለን፡፡ በተለይ እንደ Sandarbem እሳቤ ሴቶችን ወንዶች ለሴቶች ጥቅሞች ተግዳሮቶች መሆን የለባቸውም ይላል:: በመሆኑም በግለ ታሪክ ውስጥም የሚታየው አድምታ ይህንን እሳቤ የሚያንቀባርቅ ነው፡፡ በተለይ በሴቶች ላይ የሚታየውን ጭቆና ጉልቶ እዲወጣ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

> …..ባል ሚስቱ በተለያየ ምክንያቶች በፈለገ ጊዜ ፍላጎቱን ልታሟላ ካልቻለች ወይም በሌላ ምክንያት ትዳሩን ለማፍረስና ሚስቱን ማባረር መብት አለው። በትዳር በቆዩባቸው ጊዚአት ባፈራቸው ልጆች ላይ እናት ምንም አይነት መብት የላትም። ልጆቹን የማቆየት መብት ያለው የባል ወይም የወንድ አያት ነው። ከሁሉም የሚገርመውና እና የችግሩን ጥልቀት ይበልጥ የሚገልፀው የፓርላማ አባላት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል እና ለማስወገድ የሚችሉ የሕግ ረቂቆች ሲቀርቡላቸው ተግባራዊ እንዳይሆን በግልጽ ይቃወማሉ። ሴቶች የሚደርሱባቸው አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና እያስመረራቸው እንዲሁም ከሚችሉት በላይ እየሆነባቸው ራሳቸውም የሚያጠፉ ወይም ለማጥፋት ሙከራ የሚያደርጉ በብዛት ይገኛሉ። (ፀሐይ፣162)

ሌላው በፀሐይ ግለ ታሪክ ውስጥ የሚታየው የአባዊያንን አመለካካት በደንብ የሚገልጽ አገላላጥ ተጠቅማለች ። በተለይ ሴቶች የራሳቸው ፍላጎትና እዲሁም በትዳር መስርተው በሚኖሩበት ግዜ ከትዳር አጋሯ ጋር ቤቷን የመምራና የማስተዳዳር መብት እና ግዴታ እንዲሁም የልጆችን ቁጥር (ብዛት) መወሰን መብት ቢኗራትም በባህሉ ምክንያት ይህንን ስትነፈግ ስንመለከታን። ይህ ብቻ ሳይሆን በትዳር አጋሯ ካልፈደቀ በስተቀር ከሰው ጋር መነጋጋርም ሲነፍጋት እንደመለከታን። በተለይ አገላላጽ (Crenshay,1989) ስለአባዊውያንሥርዓትወንዶችበአጠቃላይበፖለቲካ፣በኢኮኖሚናበማኅበራዊጉዳዮችየሥልጣንናየሥ ልጣንቦታዎችንይይዛሉ።ይህብዙውንጊዜወደአለመመጣጠንየሀብቶች፣እድሎችእናየውሳኔሰጪሃይ ልተደራሽነትይተረጎማል።

> …. ባለትዳር የሆነች ሴት ለማነጋጋር ከሁሉ በፊት የባሏን ፍቃድ ማግኘት ግዴታ ነው። ሚስትም የባሏን ፍቃድ ካላገኘች ለማነጋገር በፍጹም ፍቃደኛ አትሆንምቤት፤ ቤት እየሄድን በምናደርገው ጉብኝትና ውይይት አንዲት ያገባች ወጣት ለማነጋጋር እቤቷ ተገኘን። ይህች ሴት አምስት ልጆች አሏት። ባለችበት እድሜ ገና ብዙ ልትወልድም የምትችል ናት። ሁለቱ ልጆቿ ትምህርት ቤት የገቡ ሲሆን የተቀሩት ሴት ልጆቿ ግን ከትምህርት ተገለው እቤት ይገኛሉ።(ፀሐይ፣165)

ሌላው በግለ ታሪክ ውስጥ የምናገኘው የሥርአተ ፆታ ማህራዊ ግንባታ የሚንፀባረቅበት ነው። ይህም ሴቶችን የበታነት የሚያሳይ እና የወንዶችን የበላይነት የሚያሳይ እንደሆነ የተገለጸበት አግባባነት አለው። ሴቶቹም ፍፁም ተገዢነት እና የወንዶች አገልጋይ ተደርጎ የቀረቡበት አለው። እንደ በጁዲትበትለርየሥርዓተ-ፆታአፈፃፀምስርዓተ-

ያታውስጣዊወይምቋሚማንነትሳይሆንበተደጋገሙድርጊቶች፣ ባህሪያትእናየማህበረሰብደንቦችየተገነባነገርነው፡፡

> …… ውይይቱ ላይ በማካሄድ ላይ እንዳለን ባል ከውጭ ወደ ቤቱ መጣ፡፡ በሩን ከፍቶ ሰውነቱ ሙሉ በሙሉ ሳይገባ ከነበረችበት ቦታ ሹልክ ብላ እግሮቹ ላይ ተጠምጥማ ሁለቱምን እግሮችም ሳመች፡፡ ይህ የመሰለ ሠላምታዋ ባሏ በገባ እና በወጣ ቁጥር የምታደርገው የተለመደ ተግባሯ እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁኝ፡፡ ይህ የመሰለው የባልና የሚስት ሰላምታ ከዚህ በኋላ በተዘዋወርኩባቸው ቤቶች በመደጋገም ለመመልከት ችያለሁኝ፡፡(165) አባዊ ሥርት፣ የስርአተ ጾታ ማህበራዊ ግንባታን የሚመለክት ነው፡፡

እንደMulvey አገላለጽ የሴቶችንተጨባጭነትእናየአካሎቻቸውንውክልናየወንድፍላጎትእናቁጥጥርንያካትታል፡፡በተለይ ሴቶ ችን ለፆታ ፍላጎት እና አካላን ብቻ ሲመኝ እንመለከታለን፡፡ ሰውዬው ስርአት የሌለውና የሚናገረውን የማያውቅ በመሆኑ ልክ እኔን እንዳየ ኦ ይሄው ሚስቴ መጥታለችበማለት ጮሆ ተናገረ፡፡(ፀሐይ፣134)ይህ አገላጽ ከጽንሀሳብ አንፃር ስንመለከት የወንድ እይታ የሚመለከት ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# 4 ማጠቃለያ እና ይሁንታ

## 4.1 ማጠቃለያ

ግለ ታሪክ በኢ- ልብ ወለድ (non fiction) ዘርፍ የሚካተት የስነ ጽሁፍ ውጤት ነው፡፡ ግለ ታሪክ ሥነ ጽሁፍ ከጥበባዊ ፋይዳ ባለፈ የዘመኑ የሕዝቡን አኗኗር እና አስተሳሳብ ባህል ወግ ፖለቲካ እንዱሁም ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እውነቶችንለትውልድ የምታስለላልፍ የታሪክ ማህደር ጭምር ናት፡፡ ከሴቶች ግለ ታሪክ መረዳት የሚቻለው ውጣ ውረድ ባህላዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥነ ልቦናዊ ሥነ ሕይወታዊ እና የጤና እንክብካቤ ጋር ተዳብሮ የሚኖራቸው ጫናዎች ሴቶች ለጭንቀት ለድብርት ለሀዘን የሚያጋልጡ መሆናቸው ልብ ይላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ከግል ታሪካቸው መረዳት የሚቻለው የሰው ልጅ በታሪኩ በተለያዩ የማከፋፈያ ልዩነት መፍጠሪያ ግድግዳዎችን (እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ልማዶችን፣ ባህሎችን) እንደሚገኙ በግል

ታሪኮች በሰፊው ተብራርተዋል፡፡ ብዙ ለውጥ ካልተካሄደባቸው የተዛቡ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ በጾታ ልዩነት ላይ የተመሰረተ አድላዊነት በግል ታሪኮች ውስጥ ተጠቃሏል፡፡

በግል ታሪኮች ውስጥ ልጆች ለወላጆቻቸው ውድ ስጦታዎች መሆናቸውንም አባት እና እናት ልጆቻችን ለማሳደግ ያሳዩት ፍቅር እና እንክብካቤ መሆኑ በስፋት ተተርኳል፡፡ በሴቶች ላይ መጮህ ማፍጠጥ ወ.ዘ.ተ የብዙ ወንዶች ተግባር መሆኑን በግል ታሪኮች ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የሕይወት አጋር ከምንም በላይ ቅድሚያ ሰጥቶ አክብሮ መንከባከብ ትልቅ የደስታ ምንጭ መሆኑ በስፋት ተካቷል፡፡ ለግል ታሪኮች ታሪካቸው የሴትነት (feminism) ትግል እንዲስፋፋ ሴቶችን ለማንቃት ትኩረት ባደረገ መልኩ የቀረቡ ናቸው፡፡

ከግለ ታሪኮች በተሞክሮ የተመሰረ ከግለሰቡ በፊት በነበሩት ሰዎች ሀሳብ ሥራ እና እውቀት መሆኑን ማረጋገጫ የሰጡ ስራዎች ናቸው፡፡

ግለ ታሪኮች ውስጥ ሰው ሲወለድ በሕይወት ጉዞ ውስጥ ሊወዳደርባቸው የሚችሉባቸው የማሰብም ሆነ ከፍ ካለ የማወቅ ብቃት ላይ ለመድረስ የሚያበቃው እኩል ኃይል ይዞ ቢወለድም አካባቢ እና አስተዳደግ ልዩነቶች መፍጠራቸው እውን መሆኑን አካቷል፡፡ በተጨማሪም የሁለቱ ጾታዎች መስተጋብር የሰመረ እንዲሆን የጾታ እኩልነት ፍትሃዊነት ከአድሎ ነጻ የሆነ ምቹ ሁኔታ ለማመቻቸት በማህበረሰብ በትምህርትና በጥበብ ማነጽ ተገቢ መሆኑን ግለ ታሪኮች ሃሳብ ይሰነዝራሉ፡፡

## 4.2 ይሁንታ

የተመረጡት የግል ታሪኮች ለዚህ ጥናት አራት ቁም ነገሮች ለመገብየት የሚያስችሉ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡ በቅድሚያ ትላንትን ያሳዩንን ለዛሬ መስራት የጣሉ ፈር ቀዳጅ ሴቶች ግለ ታሪክ ለስነ ጽሁፍ እድገት ማህበራዊ ግንኙነት የፆታ እኩልነትና መስተጋብር ግንዛቤ ለመጨመር ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ሁለተኛው የግል ሕይወት እና የስራ ጉዞ ምርምር መጽሀፍ ማውጣት ከመጽሃፍቱ የግልና የስራ ሕይወት ሌሎች ሊማሩ የሚችሉባቸውን በርካታ ፍሬ ነገሮች አካቶ የያዘ ስለሆነ ጠቀሜታው በርካታ ነው፡፡

ሌላው የስራ የሕይወት ታሪክ መጽሃፍ መዘከር ስለ ግለሰቡ መረጃ የሚያስፈልግ የመረጃ መጣረስና መዛባት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ የደራሲያኑን ስራዎችን ይዘትና ጥልቀት እንዲሁም የሕይወት ጉዞ በስፋት ለመዳሰስ ለሚፈልጉ ሌሎች ፀሐፊያን ምናልባትም እንደ መነሻ ይሆናል በሚል እምነት ያሳድራል፡፡

ከዚህ ባሻገር በግለ ታሪክ በሚፃፍበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ አስተያየቶች ከዚህ ቦታ ለመዘርዘር ተሞክሯል፡፡

ትረካውን ለማራመድ በፀሐፊው በጥንቃቄ የተመረጡ ርእሰ ጉዳዮች መካተት ተገቢ ይሆናል፡፡ አስፈላጊው ዝርዝር ሃሳቦች ብቻ በቅደም ተከተል ማካተት ተገቢ ነው፡፡ ማለትም ልዩ ስኬቶች ፈጠራዎች ወይም አስተዋጽኦዎች ላይ ማተኮር፣ ያጋጠማቸውን ልዩ መሰናክሎች እንዴት እንዳሸነፉት ማካተት፣ የተለያዩ ሚማዎች ላይ አስተዋጽኦ መስጠት፡፡ የግል እና ማህበራዊ አውድ ልምድ ከግምት ማስገባት የሥርአተ ጾታ ወጎችን ልምዶችን መዳሰስ ተሰማሚ ወይም ተፅዕኖ ፈጣሪ የቤተሰብ አባል የህብረተሰብ አካል ጋር ግንኙነት መፍጠር የመረጃ ምንጭ ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ጥልቅ ምርምር ማካሄድ ተገቢ ነው፡፡ ግለ ታሪክ በሚፃፍበት ጊዜም የሚፈጠረው ተፅዕኖ ለሚቀጥለው ትውልድ ላይ የሚያሳረፈው አሻራ ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡ መፍትሄታዊነት ለማስወገድ አክብሮትን ማጎልበት ተገቢ ይሆናል፡፡ ባለሙያዎች ጋር መስራት ማመካከር አሳታፊ የአፃፃፍ ቴክኒኮች መጠቀም ውጤታማ የግል ታሪክ መጽሃፍት ለህብረተሰብ ማበርከት ይቻላል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብታሙ ግርማ፡፡ <u>*የስነ ፅሁፍ ሰዎችና ስራዎቻቸው*</u>፡ **ጅግጅጋ ኢትዮጵያ**፤2008፡፡

ሐረገወይን ሸዋረጋ፡፡ "በባህርዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የሕይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ 2004፤ ያልታተመ

ማርቆስ የሻው፡፡ "የኮሪያ ዘማቾች ግለ ታሪኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ 2000፤ ያልታተመ

**ፀሐይ ይትባረክ፡፡ <u>*የፀሐይ ጉዞ*</u>፡ አዲስ አበባ**፤ ጃጃው አታሚዎች እና ዴቨሎፐርስ፤ 2009፤ **የታተመ**

**ትግስት ግርማ፡፡ <u>*ትሙት ግድ የለም*</u>፡** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ጃጃው አታሚዎች እና

ዴቨሎፐርስ፤ 2012፤ የታተመ

**የውብ ድንበር፡፡** ***የውብ ድንበር እውነተኛ ታሪክ*** **፡፡ አዲስ አበባ፤ ፍሪስት ትሬዲኒግ ኢትዮጵያ፤ 2009፡፡ የታተመ**

***ያለው እዳወቀ፡፡*** ***የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር***፡፡ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፤ተፈራ ስሙም ፐሪት ፐሬስ፤2009፡፡ የታተመ

**ይሁኔ አየለ፡፡** ***እናት*** **፡፡ አዲስ አበባ፤** ጃጃው አታሚዎች እና ዴቨሎፐርስ፤ **2015፤ የታተመ**

ዘሪሁን አስፋው፡፡ *የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን* ፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ 2000፡፡ የታተመ

ዘሪሁንአስፋው፡፡ *ከበዓሉ ግርማእስከ...አዳሙ ረታ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ጃጃው አታሚዎች እና ዴቨሎፐርስ፤ 2013፤ የታተመ

**Bell hook.** "Writing Autobiography in "Remembered Rapture: The Writer at Work", An essay.1999

**Bem, S. L.** *The Lenses of Gender: Transforming the Debate on Sexual Inequality*. Yale University Press, **1993.**

**Butler, J.** *Gender Trouble: Feminism and the Subversion of Identity*. Routledge, **1990.**

**----------.** *Bodies That Matter: On the Discursive Limits of Sex*. Routledge**, 1993.**

**----------.** *Undoing Gender*. Routledge. **2004.**

**Collins, P. H.** *Black Feminist Thought: Knowledge, Consciousness, and the Politics of Empowerment*. Routledge, **1990.**

**Connell, R. W.** *Masculinities*. University of California Press**, 1995.**

Crenshaw, K. "Demarginalizing the Intersection of Race and Sex: A Black Feminist Critique of Antidiscrimination Doctrine, Feminist Theory and Antiracist Politics." *University of Chicago Legal Forum*, (1), 139-167. 1989

Dan P. McAdams. "The Stories We Live By: Personal Myths and the Making of the Self" 1997.

Davis, A. Y.*Women, Race, & Class*. Vintage Books,1981.

Doane, M. A."The Woman's Film: Possession and Address." *Screen*, 28(2), 43-53,1987.

Gloria Anzaldúa . "Borderlands/La Frontera: The New Mestiza" ,1987.

Jacques Derrida. "Archive Fever: A Freudian Impression" . An exploration of autobiographical writing,1995

Jacques Lacan ."The Mirror Stage as Formative of the I Function" An essay, 1949.

Lorber, J. *Paradoxes of Gender*. Yale University Press, 1994.

**McCabe, J., & Akass, K. (Eds.).** *Quality TV: Contemporary American Television and Beyond*. I.B. Tauris. **2007.**

Mulvey, L. "Visual Pleasure and Narrative Cinema." *Screen*, 16(3), 6-18. 1975.

-------------. "Visual Pleasure and Narrative Cinema." *Screen*, Identity Politics, and Violence against Women of Color." *Stanford Law Review*, 43(6), 1241-1299, 1975.

Philippe Lejeune."On Autobiography",1989.

Paul de Man. "Autobiography as De-Facement".An essay, 1979.

Sidonie Smith and Julia Watson. "Women, Autobiography, Theory: A Reader" Edited volume,1998.

Stanley Fish. "Interpreting the Variorum" in "Is There a Text in This Class?The Authority of Interpretive Communities" .A essay,1980.

West, C., & Zimmerman, D. H."Doing Gender." *Gender & Society*, 1(2), 125-151,1987.

Wolfgang Iser. "The Act of Reading: A Theory of Aesthetic Response" 1978.